# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

83ኛ ዓመት ቁጥር 144 ጥር 24 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)

የሁሉም ባንክ
Bank for all !

የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ !

በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia


# መከላከልና አክሞ ማዳን የሚችል ጠንካራ የጤና ሥርዓት ለመገንባት እየተሠራ ነው

- ከ13 ቢሊዮን ብር በላይ የሚያወጣ መድኃኒትና የሕክምና ግብዓት ለጤና ተቋማት ተሠራጭቷል
- በጤና ተቋማት የሚወልዱ እናቶች ምጣኔ 63 በመቶ ደርሷል


ፎቶ ሀዳስ አብርሀ

ደረጀ ዱጉማ(ዶ/ር)

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- ተላላፊ የሆኑና ያልሆኑ በሽታዎችን መከላከልና አክሞ ማዳን የሚችል ጠንካራ የጤና ሥርዓት ለመገንባት በትኩረት እየተሠራ መሆኑን የጤና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የጤና ሚኒስትር ዴኤታ ደረጀ ዱጉማ(ዶ/ር) ለመገናኛ ብዙኃን በሰጡት ማብራሪያ፤ መከላከልን መሠረት ያደረገና ለአክሞ ማዳን ትኩረት የሚሰጠውን ፖሊሲያችንን መሠረት አድርጎ በየአምስት ዓመቱ የትራንስፎርሜሽን እቅድ ያዘጋጃል ብለዋል፡፡

በዚህም ተላላፊ የሆኑና ያልሆኑ በሽታዎችን መከላከልና አክሞ ማዳን የሚችል ጠንካራ የጤና ሥርዓት ለመገንባት በትኩረት እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

ተላላፊ የሆኑ በሽታዎችን ከመከላከልና ከመቆጣጠር አንጻር ባለፉት ስድስት ወራት ቲቢ ይኖርባቸዋል ተብለው ከሚገመቱ 66ሺህ387 በላይ ዜጎች 81 በመቶው ተለይተው ሕክምና እንዲያገኙ መደረጉን ጠቅሰው፤ ኤች አይቪ ኤድስን ከመከላከል አንጻርም 15ሺህ 58 ሰዎች ኤች አይቪ

መከላከልና አክሞ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል


አምባሳደር መስስ ዓለም (ዶ/ር)

# «የኅብረቱን ስብሰባ በስኬት በማጠናቀቅ ብሔራዊ ጥቅምን የሚያስጠብቁ ዕድሎችን ለመፍጠር ዝግጅት እየተደረገ ነው»

- የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

ቃልኪዳን አሳዬ

አዲስ አበባ፡- በየካቲት ወር የሚካሄዱትን የአፍሪካ ኅብረት ስብሰባዎች በስኬት በማጠናቀቅ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም የሚያስጠብቁ ዕድሎችን ለመፍጠር ጠንካራ

«የኅብረቱን ስብሰባ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል


ፎቶ፡ ዳኜ አበራ

ኢንጂነር አይሻ መሐመድ

# የኢትዮጵያ የአርብቶ አደር ፖሊሲ አህጉራዊ ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል ነው

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ የአርብቶ አደር ፖሊሲ አህጉራዊ ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል መሆኑን የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር አስታወቀ። «አርብቶ

የኢትዮጵያ የአርብቶ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# ከሕዝብና ከመንግሥት የተመዘበሩ ሀብቶችን ለማስመለስ ትኩረት ተሰጥቷል

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- በተለያዩ መንግሥታዊ እና ሕዝባዊ ተቋማት የሚፈጸሙ የሙስና ወንጀሎችን ምርመራ ቅልጥፍና እና ጥራት በማሳደግ የተመዘበሩ የመንግሥትና የሕዝብ ሀብቶችን ለማስመለስ ትኩረት መስጠቱን የፍትህ ሚኒስትሩ ጌዲዮን ጢሞቴዎስ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

ሚኒስትሩ ጌዲዮን (ዶ/ር) ትናንት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተቋማቸውን የግማሽ ዓመት የዕቅድ አፈጻጸምን ባስገመገሙበት ወቅት፤ ከሕዝብና ከመንግሥት የተመዘበሩ ሀብቶችን ማስመለስ በቀጣይ ትኩረት ይሰጥባቸዋል ካሏቸው መካከል ይጠቀሳል፡፡

የመንግሥትና የሕዝብ ሀብትን መዝብረው ከሀገር የሸሹ ወንጀለኞችን ተጠያቂ ለማድረግና ሀብቱን ለማስመለስ በትኩረት ከሚሠራው ሥራ መካከል በሕግና ፍትሕ ጉዳዮች ዓለም አቀፍ ትብብርን ማሳደግ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በዚሁ ተግባር በተሠራው ሥራም ከደቡብ አፍሪካ

ከሕዝብና ከመንግሥት ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል




AfriSky PLC
ETHIOPIA
REBAR | WIREROAD | RHS | TANKER | NAIL
0940 80 80 80 | 0940 90 90 90 | 0911 21 72 55 | 0940 50 50 50

AMG STEEL FACTORY
ኤኤምጂ ብረታ ብረት ፋብሪካ
AMG Steel Factory



# «ሉላዊነት በኪነ ጥበብና ማኅበራዊ እድገት ላይ እያደረሰ ያለውን ተግዳሮት ለመቋቋም ትልቅ ትጋት ይጠይቃል»

ቀጄላ መርዳሳ
- የባህልና ስፖርት ሚኒስትር

አዲሱ ገረመው

አዲስ አበባ፡- ሉላዊነት በኪነ ጥበብና ማኅበራዊ እድገት ላይ እያደረሰ ያለውን ተግዳሮት ለመቋቋም ትልቅ ትጋት እንደሚጠይቅ አቶ ቀጄላ መርዳሳ ገለጹ። ሦስተኛው «ክብር ለጥበብ» የእውቅናና አሰጣጥ መርሐ ግብር ከትናንት በስቲያ በብሔራዊ ቴአትር ተካሂዷል።

የባህልና ስፖርት ሚኒስትሩ አቶ ቀጄላ መርዳሳ በመድረኩ ባደረጉት ንግግር፣ የሉላዊነት ወይም ግሎባላይዜሽን መከሰት የኪነ ጥበብ፣ ሥነ ጥበብና የፈጠራ ሥራዎችን ታሪክ ፊት ለፊት የሚጋፈጥና የማኅበራዊ እድገት ተግዳሮት ሆኖ ይታያል ብለዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፣ የዓለማችን ሕዝቦች ከጊዜ ወደ ጊዜ ዘመኑ በወለዳቸው የቴክኖሎጂ ውጤቶች አማካኝነት እርስ በርስ እየተገናኙ ሲሄዱ ከተለያዩ ባህሎች ጋር የመተዋወቅ፣ የመለማመድ፣ የመዋጥ እና የራስ ማንነት መገለጫ የሆኑ ጥበባትን የመርሳት ብሎም የማጣት ፈተና ውስጥ ገብተዋል። ኢትዮጵያም ችግሩ ካስከተለው ፈተና ነፃ አይደለችም። በመሆኑም እንደ ሀገር የተጠቀሰውን ዘመን ወለድ ችግር ለመቋቋምም ሆነ ያለውን ጠብቆና አልምቶ እንዲሁም አዳዲስ ፈጠራዎችን አክሎ ለቀጣይ ትውልድ የማሸጋገር ሥራ ትልቅ ትጋትንና ብልሃትን የሚጠይቅ ነው።

ኢትዮጵያ የበርካታ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብዝኃ ባህል፣ ቋንቋ እና ሃይማኖት መገኛ ሀገር መሆኗን የገለጹት ሚኒስትሩ፣ የረጅም ዘመናት ሥልጣኔ እና የሀገር በቀል ዕውቀት፣ በተለይም የድንቅ ኪነ ጥበብ፣ ሥነ ጥበብና ፈጠራ ውጤቶች ባለቤት የሆኑ ሕዝቦች ሀገር መሆኗንም ጠቅሰዋል። በዚህም ከጥንት ጀምሮ የአስደናቂ ጥበባት መፍለቂያ ሀገር ሆና መቆየቷን አንስተዋል።

በኪነ ጥበብ፣ ሥነ ጥበብና ፈጠራ ሥራዎች ላይ የሚያጋጥሙ ፈተናዎችን በማሸነፍ እንደ ሀገር ለማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እመርታ ከሚሰጡት ጠቀሜታ አንፃር በተገቢው ሁኔታ ማደግ እንደሚኖርባቸው ሚኒስትሩ ተናግረዋል።

መንግሥት በሰጠው ልዩ ትኩረት በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ መዋቅር ውስጥ በሚኒስትር ዴኤታ የሚመራ የኪነ ጥበብ፣ ሥነ ጥበብና የፈጠራ ልማት ዘርፍ በማቋቋም ሰፊ ራዕይ ሰንቆ እየሠራ ይገኛልም ብለዋል።

«ለእውቅናው የታጩና ብቁ የሆኑ የጥበብና የፈጠራ ባለሙያዎችን ስንሸልም ከዚህ ቀደም ላበረከቱት አስተዋጽኦ እውቅና ከመስጠት ባሻገር ለወደፊቱም ይበልጥ እንዲሠሩና ተተኪዎችንም እንዲያፈሩ ታላቅ ሀገራዊ አደራ ለመስጠት በማሰብ ነው» ብለዋል።

በመርሐ ግብሩ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣ ሚኒስትር ዴኤታዎች፣ አንጋፋ የኪነጥበብ ሰዎችና ከሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች የተውጣጡ የጥበብ ባለሙያዎች የተሳተፉ ሲሆን፣ በተለያዩ የኪነጥበብ ዘርፎች አስተዋጽኦ ላበረከቱ 50 ያህል ባለሙያዎችም እውቅና ተሰጥቷል።

ገጣሚና ጸሐፊ ተውኔት አያልነህ ሙላቱ፣ ደራሲ ታደለ ገድሌ (ዶ/ር)፣ አርቲስት አልጋነሽ ታሪኩና ደራሲ አለማየሁ ዋሴ (ዶ/ር ) እውቅና ከተሰጣቸው ባለሙያዎች ውስጥ ይገኛሉ።

# ኃይሌ ሆቴሎች እና ሪዞርቶች በወላይታ ሶዶ ያስገነባው ባለአራት ኮከብ ሆቴል ተመረቀ

## - ሆቴሉ የከተማዋን የቱሪዝም ኢንዱስትሪ የሚያነቃቃ ነው

ዳግማዊት አበበ

ወላይታ ሶዶ፡- ኃይሌ ሆቴሎች እና ሪዞርቶች በአንድ ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር በወላይታ ሶዶ ከተማ ያስገነባው ባለ አራት ኮከብ ሆቴል ተመርቆ ሥራ ጀመረ። ሆቴሉ የወላይታ ሶዶ ከተማን የቱሪዝም ኢንዱስትሪ የሚያነቃቃ መሆኑን የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል አስታውቋል።

በሆቴሉ ምረቃ በወቅቱ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ተስፋዬ ይገዙ እንደገለፁት፣ ኃይሌ ወላይታ ሆቴል ደረጃውን በጠበቀ ጥራት ተገንብቶ ሥራ መጀመሩ የከተማዋን የቱሪዝም ኢንዱስትሪ የሚያነቃቃ ነው።

የወላይታ ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ ሳሙኤል ፎላ በበኩላቸው እንዳሉት፣ መንግሥት በአሁኑ ጊዜ የግሉ ዘርፍ ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ነው። በዚህም በዞኑ ለግል ኢንቨስተሮች ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

ዞኑ የተለያዩ ኢንቨስተሮችን መሳብ ችሏል ያሉት አቶ ሳሙኤል፣ ለዚህም የሚሆነው ኃይሌ ወላይታ ሆቴል በሶዶ ከተማ ተገንብቶ ሥራ መጀመሩ ማሳያ ነው ብለዋል።

የኃይሌ ሆቴሎች እና ሪዞርቶች ግሩፕ መሥራችና ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሻለቃ አትሌት ኃይሌ ገብረሥላሴ፣ ሆቴሉ በዋናነት የከተማዋን ቱሪዝም ለማነቃቃት እንዲሁም ወደ ከተማዋ ለሚመጡ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ጎብኚዎች ጥሩና በቂ ማረፊያ እንዲያገኙ ዕድል የሚፈጥር መሆኑን ተናግረዋል።

የኃይሌ ወላይታ ሆቴል ከአንድ ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ እንደወጣበት በመጥቀስ፣ ከ160 በላይ ለሆኑ የአካባቢው ነዋሪዎች የሥራ ዕድል መፍጠር መቻሉን አመልክተዋል። በቀጣይ በሙሉ አቅም ሥራ ሲጀምር 300 ለሚሆኑ ዜጎች ቋሚ የሥራ ዕድል እንደሚፈጥር ገልፀዋል፡፡

ሆቴሉ የተለያየ ዓይነትና ስፋት ያላቸው 107 የእንግዳ ማረፊያ ክፍሎች፣ ደረጃቸውን የጠበቁ የመመገቢያ አዳራሾች እንዲሁም ባሮች፣ ከ15 እስከ 600 ሰዎችን ሊያስተናግዱ የሚችሉ ሰባት ሁለገብ አዳራሾች፣ የበይነ መረብ (ኢንተርኔት) አገልግሎት፣ የእስቲም፣ የሳውና እና የማሳጅ አገልግሎት፣ የስፖርት ማዘወተሪያ ስፍራዎች (የመዋኛ ገንዳ እና ጂምናዚየም) ጨምሮ የተለያዩ አገልግሎት መስጫ ክፍሎችን የያዘ መሆኑ ገልጸዋል።





በቀጣይ አንድ ዓመት ውስጥ ሦስት ሆቴሎችን ለመክፈት መታቀዱን የተናገሩት ሻለቃ አትሌት ኃይሌ፣ ሆቴሎቹም በጅማ፣ ሻሸመኔ እና ደብረብርሃን የሚከፈቱ መሆናቸውን አብራርተዋል።

ኃይሌ ሆቴሎች እና ሪዞርቶች ሐዋሳ፣ አርባምንጭ፣ ጎንደር፣ ዝዋይ፣ ሱልልታ፣ አዳማ እና አዲስ አበባ ከተሞች ላይ ተከፍተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ሲሆኑ ግንባታቸው የተጠናቀቁ እና በሂደት ላይ ያሉትን ጨምሮ በቅርቡ በምሥራቅ አፍሪካ ሀገራትም ተጨማሪ መዳረሻዎችን ለመክፈት በሂደት ላይ መሆኑም ተገልጿል።

# የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና የሥርዓተ-ምግብ መቋቋሚያ ፕሮግራም ይፋ ተደረገ

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- ከአንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር በላይ የተበጀተለት የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና ሥርዓት-ምግብ መቋቋሚያ ፕሮግራም በይፋ መጀመሩን የዓለም ባንክ እና የምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት ድርጅት (ኢጋድ) አስታወቁ።

ፕሮግራሙ ይፋ መደረጉን አስመልክቶ በተጋጀው መርሐ ግብር ዓለም ባንክን ወክለው የተገኙትና የባንኩ ከፍተኛ የግብርና ስፔሻሊስት ቲሞቲ ሮበርትሶን እንደገለጹት፣ በአየር ንብረት ለውጥ፣ በግጭቶች፣ በሰብል አውዳሚ ተባዮችና በተለያዩ መንገዶች የአፍሪካ ሀገራት የግብርና ምርት ሥርዓት ላይ መጠነ ሰፊ ጉዳት እየደረሰ ይገኛል።

ችግሮቹን ተቋቁሞ የምግብ ሥርዓትን ለማሻሻል የሚረዱ ፕሮጀክቶች በተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት እየተከናወኑ ይገኛል ያሉት ቲሞቲ ሮበርትሶን፣ የምሥራቅ አፍሪካ የምግብ ሥርዓት መቋቋሚያ ፕሮግራም በመጀመሪያው ዙር ከአንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር በላይ (25 ሚሊዮን ዶላር) ወጪ እንደሚደረግበት አመላክተዋል።

ፕሮግራሙ ለቀጣይ ሰባት ዓመታት ተግባራዊ እንደሚደረግ ጠቁመው፣ በፕሮግራሙ መሠረት የግብርና ሥራዎችን የሚያሻሽሉ ቴክኖሎጂዎች፣ የውሃ አጠቃቀምን ለማሻሻል የሚረዱ አሠራሮች፣ ለአርሶአደሮች የምርጥ ዘር አቅርቦት፣ የግብርና ምርቶችን ወደ ገበያ የማቅረብና ተያያዥ ሥራዎች ይከናወናሉ ብለዋል።

በፕሮግራሙ መሠረት የኢትዮጵያ አርሶአደሮችም በሰፊው ተጠቃሚ የሚሆኑበት አማራጭ መኖሩን አንስተዋል።

የኢጋድ የግብርናና አየር ንብረት ዲቪዥን ዳይሬክተር ማኸር ኤልሚ በበኩላቸው፣ በምሥራቅ አፍሪካ በሚያጋጥሙ የተለያዩ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ችግሮች መካከል በየሀገራቱ ለምግብ ዋስትና አደጋ የተጋለጡ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች አሉ።

ይፋ የተደረገው ፕሮግራም በአነስተኛ የመሬት ስፋት ላይ ለሚከናወኑ የመስኖ ልማቶች የግብርና ግብዓት ድጋፍ ለማቅረብ፣ በበረሃ አንበጣ መከላከል ላይ ለመሥራትና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በጎ አስተዋጽኦ ያደርጋል ሲሉ ተናግረዋል።

በምሥራቅ አፍሪካ በቂ ውሃ፣ የግብርና መሬትና የሰው ኃይል አለ ያሉት ዶክተር ሞህየልደን፣ በግብርናና ምግብ ዋስትና ላይ የሚጋረጡ ችግሮችን እየቀረፉ መሄድ ከተቻለ የተሻለ ልማት በቀጣናው ማሳካት እንደሚቻል አስረድተዋል።

በአጠቃላይ በሦስት ነጥብ 63 ቢሊዮን ዶላር ወጪ በተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት የሥርዓተ-ምግብ መቋቋሚያ ፕሮግራሞች እየተከናወኑ መሆኑን የዓለም ባንክ አስታውቋል።



ማኸር ኤልሚ

ዜና

# በመዲናዋ 35 ሺህ ነጋዴዎች ወደሕጋዊ ሥርዓት እንዲገቡ ተደርጓል

## - በግማሽ ዓመቱ ከ74 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ ተሰብስቧል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ በ2016 በጀት ዓመት ስድስት ወራት 35 ሺህ ነጋዴዎች ወደ ሕጋዊ የንግድ ሥርዓቱ እንዲገቡ መደረጉን የአዲስ አበባ ከተማ ገቢዎች ቢሮ አስታወቀ። በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት ከ74 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ መሰብሰቡም ተገልጿል።

ቢሮው የግማሽ ዓመት ዕቅድ አፈጻጸሙን አስመልክቶ ከባለድርሻ አካላት ጋር የምክክር መድረክ ትናንት ሲያካሂድ የቢሮው ኃላፊ አቶ አደም ኑሪ እንደተናገሩት፤ በቅንጅት በተሠሩ ሥራዎች ባለፉት ስድስት ወራት 35 ሺህ ነጋዴዎች ወደ ንግድ ሥርዓቱ እንዲገቡ ማድረግ ተችሏል።

ወደሕጋዊ የንግድ ሥርዓቱ የማስገባት ሂደቱ የመዲናዋን የግብር አሰባሰብ አቅም እንደሚያሳድገው አመላክተው፤ ወደትክክለኛው ሥርዓት ከገቡ በኋላ ደረሰኝ እየቆረጡ እንዲነግዱ የሚያበረታታ ሥርዓት መፈጠሩንም አስረድተዋል።

የገቢ አሰባሰቡ፣ ሕግ የማስከበርና የአገልግሎት አሰጣጡን በቴክኖሎጂ የማስደገፍ ተግባር ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባም ጠቁመው፤ ከግብር ሥርዓቱ ጋር ተያይዞ ያለደረሰኝ ግብይት የፈጸሙ 679 ሕገ-ወጥ ነጋዴዎች ለሕግ ቀርበው ምርመራ እየተደረገባቸው እንደሚገኝ አስታውቀዋል።

እንደ አቶ አደም ገለጻ፤ ቢሮው በግማሽ ዓመቱ ለመሰብሰብ ካቀደው 78 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር 74 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር በመሰብሰብ የእቅዱን 95 በመቶ ማሳካት ችሏል።


ከእቅድ አንጻር አራት ቢሊዮን ብር ወደ ኋላ መቅረቱን ገልጸው፣ በቀጣይ ጉድለቱን ጨምሮ አጠቃላይ 65 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ በትኩረት ይሠራል ብለዋል።

በተለይ የመሬት ሊዝ አገልግሎት አሰጣጡን ዘመናዊ ለማድረግ በተጀመሩ ሥራዎች ምክንያት በተወሰኑ ክፍለ ከተሞች ሥራ በመቆሙ ለገቢው ማነስ እንደምክንያትነት አንስተዋል።

የቴምብርና የኪራይ ቤት ግብር አሰባሰብ አነስተኛ ከመሆኑም ባለፈ አጠቃላይ የስድስት ወራት የገቢ አሰባሰብ ከሌሎች ጊዜያት የተሻለ መሆኑን ጠቅሰው፣ በቀሪው ስድስት ወር ክፍተቶችን ለመቅረፍ ይሠራል ሲሉ ተናግረዋል።

በቀጣይ የማኅበረሰቡን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ፍላጎት ለማሟላት በትኩረት እንደሚሠራ አመላክተው፤ በአዲስ አበባ ከተማ የሚሰበሰበውን ገቢ ለማሳደግ የተሻለ አገልግሎት ከማቅረብና ሕግን ከማስከበር ባለፈ ቅንጅታዊ አሠራሮችን ማጠናከር ያስፈልጋል ብለዋል።

ከግብር ጋር ተያይዞ የሚታዩ የሥነ-ምግባር ግድፈቶችንና ብልሹ አሠራሮችን ለመከላከል ሁሉም ዜጋ ሊተባበር እንደሚገባ አቶ አደም ጥሪ አቅርበዋል።


አቶ አደም ኑሪ



# የሕዝብና ቤት ቆጠራ

## በ2018 ዓ.ም ይደረጋል

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- የሕዝብና ቤት ቆጠራ መርሐ ግብር በ2018 ዓ.ም እንደሚደረግ የፕላንና ልማት ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያን የስታትስቲክስ ሥርዓት በከፍተኛ ሁኔታ የሚለውጥ ነው የተባለለት «የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ ፕሮግራም» የተሰኘ ፕሮጀክት ትናንት ይፋ ሆኗል፡፡

ፕሮግራሙ ይፋ በተደረገበት መድረክ የተገኙት የፕላንና ልማት ሚኒስትር ፍጹም አሰፋ(ዶ/ር) በተያዘው ዓመት የዲሞግራፊ፣ የጤና ቅኝትና የቢዝነስ ተቋማት ቆጠራ መጀመሩን ተናግረው የግብርና ቆጠራ በሚቀጥለው ዓመት እንዲሁም የሕዝብና ቤት ቆጠራ ደግሞ በ2018 ዓ.ም ይደረጋል ብለዋል።

የሕዝብና ቤት ቆጠራ መንግሥት በከፍተኛ ቁርጠኝነት ማከናወን እንደሚፈልግ የተናገሩት ሚኒስትሯ፤ በአንዳንድ ቦታዎች የነበሩ የጸጥታ ሁኔታዎች ምቹ ባለመሆናቸው ምክንያት ቆጠራውን ሊያስተጓጉል ይችላል ወይም ከቆጠራው የሚገኘው መረጃ ተዓማኒ ላይሆን ይችላል በሚል ስጋት ሳይደረግ መቆየቱን ተናግረዋል፡፡

አሁን ላይ በሰሜኑ የሀገሪቷ ክፍል ያለው የጸጥታ ሁኔታ እየተሻሻለ በመምጣቱ በተያዘለት ጊዜ የሕዝብና ቤት ቆጠራውን ለማድረግ አስቻይ ሁኔታዎች መኖራቸውን ጠቁመው፤ በየአካባቢው ያለውን ሁኔታ በማጣራት ቆጠራውን በአዲስ ቴክኖሎጂ አግዞ ተግባራዊ ለማድረግ እቅድ መያዙን ገልጸዋል፡፡

«የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ ፕሮግራም» የተሰኘው ፕሮጀክት ከ2016 እስከ 2018 ዓ.ም የሚተገበር የሦስት ዓመት ፕሮግራም መሆኑን ተናግረው ፕሮግራሙ የሕግና የአሠራር ማዕቀፎችን ጨምሮ እስከ መረጃ መሰብሰብ ድረስ ያሉ ፕሮግራሞችን መያዙን ጠቁመዋል።

ፕሮግራሙ ተተግብሮ ሲጠናቀቅ፣ የኢትዮጵያን የስታትስቲክስ ሥርዓት በሙሉ በመለወጥ ሪፎርም የማድረግ ሥራ ማሳካት ዓላማው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ፕሮግራሙ የክትትል፣ የግምገማ፣ እቅድ ማቀድ እና ቅድሚያ የሚሰጠው ሥራ የቱ ነው የሚለውን ሁሉ ለመወሰን ትልቅ ሚና እንደሚጫወት የተናገሩት ሚኒስትሯ፤ ሴክተሮች እቅዶቻቸውን በትክክል እያሳኩ መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲሁም ተጠያቂነትንም ለማስፈን ጥሩ አቅም የሚፈጥር ነው ብለዋል፡፡

ግብርና ቆጠራ ከተደረገ 25 ዓመት እንደሆነው ተናግረው፤ በፕሮግራሙ በግብርና ቆጠራ በሁሉም አካባቢ፣ በሁሉም ዓይነት ምርት እና ወቅት ሙሉ ቆጠራ በሚቀጥለው ዓመት ይደረጋል ብለዋል።

ለፕሮግራሙ ከ34 ቢሊዮን ብር በላይ በጀት የተያዘለት መሆኑን የተነገረ ሲሆን፤ 50 በመቶ በመንግሥት፣ 40 በመቶ ከልማት አጋሮች እንዲሁም 10 በመቶ ከልዩ ልዩ የፋይናንስ ምንጮች እንደሚሸፈን በመድረኩ ተገልጿል።

በመድረኩ ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር በከር ሻሌ(ዶ/ር) በበኩላቸው ፕሮግራሙ እንዲሳካ የሁሉም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ወሳኝ መሆኑን ተናግረዋል።

በመርሐ ግብሩ የፕላንና ልማት ሚኒስትር ፍጹም አሰፋ (ዶ/ር)፣ የግብርና ሚኒስትሩ ግርማ አመንቴ(ዶ/ር)፣ የቱሪዝም ሚኒስትሯ ወይዘሮ ናሲሴ ጫሊ፣ የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር በከር ሻሌ (ዶ/ር) እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ተገኝተዋል፡፡

# ከ4 ነጥብ 2 ሚሊዮን በላይ እናቶች በጤና ተቋማት ከወሊድ ጋር የተያያዙ አገልግሎቶችን አግኝተዋል

**ማሕሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በ2016 ዓ.ም ስድስት ወራት ከ4 ነጥብ 2 ሚሊዮን በላይ እናቶች የቅድመወሊድ፣ የወሊድና ድህረወሊድ አገልግሎቶችን በጤና ተቋማት ማግኘታቸውን የጤና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

ጤናማ የእናትነት ወር በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ37ኛ ጊዜ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለ18ኛ ጊዜ «ፍትሐዊ ተደራሽነትና ጥራት ያለው የቅድመወሊድ ክትትል በወቅቱ በማስጀመር ጤናማ እናትነትን እናረጋግጥ» በሚል መሪ ቃል ከጥር 1 እስከ ጀምሮ እየተከበረ ይገኛል፡፡

በጤና ሚኒስቴር የእናቶች፣ ሕፃናት እና አፍላ ወጣቶች ጤና መሪ ሥራ አስፈጻሚ ዶክተር መሠረት ዘላለም ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በሀገሪቱ የሚገኙ የእናቶችን፣ ጨቅላ ሕፃናትንና ሕፃናትን ሞት መቀነስ በትኩረት እየተሠራ ነው፡፡

በስድስት ወራትም 4 ሚሊዮን 212 ሺህ 019 እናቶች በጤና ተቋማት አገልግሎት አግኝተዋል፡፡ ከዚህም ከ1ነጥብ 3 በላይ የሚሆኑት የቅድመ ወሊድ፣ ከ1ነጥብ 2 በላይ የሚሆኑት የወሊድ እንዲሁም ከ1ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑት እናቶች የድህረ ወሊድ አገልግሎት በሠለጠነ ባለሙያ በመታገዝ ያገኙ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በጥር ወር የሚከበረው ጤናማ የእናትነት ወር ዋነኛ ዓላማው የእናቶችን ሕመም እና ሞት ለመቀነስ በሚደረገው ሀገራዊ ርብርብ ባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን ድጋፍ እንዲያጠናክሩ ማድረግ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡


ዶክተር መሠረት ዘላለም

እንደ ዶክተር መሠረት ገለጻ፤ በሀገሪቱ ለእናቶች ሞት ሦስት መዘግየቶች መንስኤ ናቸው፤ የመጀመሪያው እናቶች የጤና ባለሙያ እርዳታ እንደሚያስፈልግ ለማወቅ በመዘግየት የሚመጣ ሲሆን ለዚህም የመረጃ ክፍተትና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ዋነኞቹ ምክንያቶች ናቸው፡፡

ሁለተኛው እናቶች ወደ ጤና ተቋም ለመድረስ በሚገጥማቸው መዘግየት የሚከሰት ሞት ሲሆን የትራንስፖርትና የመንገድ አለመኖር እና የጤና ተቋማት ተደራሽነት ተጠቃሽ መንስኤዎች ናቸው፡፡

ሦስተኛው መዘግየት እናቶች ጤና ተቋም ከደረሱ በኋላ አገልግሎት ለማግኘት በሚገጥማቸው መዘግየት የሚከሰት ሞት ነው፡፡ የሕክምና ግብዓት እጥረት፣ የመብራትና የውሃ አገልግሎት በጤና ተቋማት አለመኖርና የአገልግሎት ጥራት እንደችግር የሚነሱ ናቸው፡፡

በዚህም መሠረት በወሊድ ጊዜ እና ከወሊድ በኋላ የደም መፍሰስ፣ በእርግዝና ጊዜ የሚከሰት ከፍተኛ የደም ግፊት፣ ንጽህናውን ያልጠበቀ ፅንስ-ማቋረጥ፣ ኢንፌክሽን እና የደም ማነስ፣ ከወሊድ በኋላ የሚከሰት ከፍተኛ የደም መፍሰስና የደም አቅርቦት እጥረት ለእናቶች ሞት ከፍተኛውን ድርሻ እንደሚይዝ አብራርተዋል፡፡

ዶክተር መሠረት እንደገለጹት፤ በአሁኑ ወቅት ከ4 ሺህ በላይ የመንግሥት ጤና ተቋማት የወሊድ አገልግሎት የሚሰጡ ሲሆን ከ18 ሺህ በላይ ጤና ኬላዎች በተለያዩ አካባቢዎች ይገኛሉ፡፡ የጤና ሥርዓቱን ለማዘመንና ተደራሽ ለማድረግም ብቁ ባለሙያዎችን በማሰልጠን ሥራ ላይ ተሰማርተዋል፡፡

በመሆኑም ከቅድመ ወሊድ የሥነ ተዋልዶ ጤናንና መረጃን ተደራሽ ከማድረግ ጀምሮ ከወሊድ በኋላ ለእናት እና ለተወለደው ልጅ የጤናና የምክረሃሳብ አገልግሎትን በሠለጠነ ባለሙያ ማግኘት ወሳኝ ነው ብለዋል፡፡

እ.ኤ.አ በ2020 የሀገሪቱ የእናቶች ሞት መረጃ መሠረት በሕይወት ከሚወለዱ ከ100 ሺህ ጨቅላ ሕፃናት መካከል 267 እናቶች ሕፃናት ይሞታሉ፡፡ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱም ይህንን ቁጥር ከ140 በታች ለመቀነስ በትኩረት እንደሚሠራም ዶክተር መሠረት አስታውቀዋል፡፡

የእናቶችን፣ ጨቅላ ሕፃናትንና ሕፃናትን ሞት ለመቀነስ በጥር ወር በሚከበረው የጤነኛ እናቶች ወር ብቻ ሳይሆን በዘላቂነት ሁሉም የድርሻውን መወጣት አለበት ብለዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የ«ፀሐይ» ለሀገሯ መብቃት ትልቅ የዲፕሎማሲ ስኬት ነው!

ሀገራችን ጥንታዊ ከመሆኗ አኳያ፤ የረጅም ዘመናት የሀገረ መንግሥት ታሪክ፤ የብዙ ሃይማኖቶችና ባህሎች ባለቤት ናት። በዚህም ዘመናት ያስቆጠሩ፤ የብዙዎችን ቀልብ የሚስቡ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊና ማኅበራዊ ቅርሶችም ባለቤት ነች። በዚህም በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍያለ እውቅና አትርፋለች።

ሀገሪቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ በዩኔስኮ ከተመዘገቡ አስራ ስድስት ዓለም አቀፍ ቅርሶች በተጨማሪ፤ እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ቅርሶች ባለቤት ነች። እነዚህን ቅርሶች በአግባቡ አጥንቶ፤ አውቆ እና በተደራጀ መልኩ ለሀገር ገጽታ ግንባታ ለማዋል ገና ብዙ የቤት ሥራዎች እንደሚቀሩም የዘርፉ ባለሙያዎች የሚስማሙበት ነው።

በተለይም በተበታተነ መንገድ በየቦታው የሚገኙ ቅርሶችን ከተደቀኑባቸው አደጋዎች ታድጎ፤ ዘመኑን በሚዋጅ አስተማማኝ መንገድ ለትውልዶች የሚተላለፉበትን፤ ለሀገር ኢኮኖሚ የተሻለ አቅም የሚሆኑበትን መንገድ ማፈላለግ፤ የዚህ ትውልድ ትልቁ ኃላፊነት እንደሆነም ይታመናል።

ከዚህ ጎን ለጎን በተለያዩ ወቅቶች ያለአግባብ (በስርቆትና በዘረፋ) ከሀገር ወጥተው በተለያዩ ሀገራት ሙዚየሞች እና ግለሰቦች እጅ የሚገኙ የሀገር ቅርሶችን አፈላልጎ ወደ ሀገር የሚመለሱበትን ስትራቴጂክ ዲፕሎማሲ አቅሞችን አጠናክሮ መቀጠል፤ የመላው ሕዝብ በተለይም የመንግሥት ትልቁ የቤት ሥራ ነው።

ከዚህ ቀደም ባሉት ዓመታት ሰፋፊ ሥራዎችና ተስፋ ሰጪ ውጤቶች ተመዝግበዋል። በዚህም፤ ለገሐር ባቡር ጣቢያ ቆሞ የሚገኘው የሞአ አንበሳ ሐውልት፣ አጼ ቴዎድሮስ ስለንግሥት ቪክቶሪያ የጻፉላቸው ሁለት ደብዳቤዎች፣ «አፍሮ አይገባ» በመባል የሚታወቀው ከላሊበላ ቤተ-መድኃዓለም ውቅር ቤተክርስቲያን ተሰርቆ በሕገ ወጥ መንገድ ከሀገር የወጣ መስቀል፣ በጣሊያን ወረራ ወቅት ተወስዶ የነበረ «የአፄ ኃይለሥላሴ ዙፋን» ለሀገራቸው ማብቃት ተችሏል።

የአፄ ቴዎድሮስ ዳዊት፣ የዓለማየሁ ቴዎድሮስ ፎቶግራፍ፤ የእቴጌ ምንትዋብ ስንክሳር፣ ከ15 እስከ 19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደተጻፉ የተገመቱና የብራና መጻሕፍትና በዚሁ ዘመን እንደተሠራ የሚገመት ሰይፍ፣ መስቀሎችን፣ ሃይማኖታዊ ስዕሎች፣ የብራና ጽሑፎች፤ በመቅደላ ጦርነት ወቅት ከኢትዮጵያ ተዘርፎ የሄደ ጽላት፣ የአፄ ቴዎድሮስ አሸንክታብ ለታሪካዊ ባለቤታቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ተመልሰዋል።

የአክሱም ሐውልትን ጨምሮ የዐፄ ቴዎድሮስ የጦር መሣሪያዎች፣ በለንደን ለጨረታ ቀርቦ የነበረው የእቴጌ ምንትዋብ ድባብ ለንደን በሚገኘው በኢትዮጵያ ኤምባሲ በኩል ተገዝቶ ወደ ሀገሩ እንዲመለስ ተደርጓል። በኬንያ ብሔራዊ ሙዚየም የነበሩ፣ ከዝሆን ቆዳ የተሠራና በብር ያጌጠ ጋሻ፣ ሁለት ጐራዴዎች፣ አራት ጩቤዎች፣ አንድ ሳንጃ፣ የአፄ ቴዎድሮስ፣ ፀጉር፣ የተለያዩ መስቀሎች እና የብራና መጽሐፍትም ለሀገራቸው በቅተዋል።

ይህ ሀገራዊ ጥረት ከለውጡ ማግስት ጀምሮ በከፍተኛ ቁርጠኝነት ተጠናክሮ ቀጥሏል። በዚህም ብዛት ያላቸው ቅርሶች ወደ ሀገራቸው የተመለሱባቸው መልካም አጋጣሚዎች ተፈጥረዋል፤ ከእነዚህም ውስጥ የአፄ ቴዎድሮስ ወንድ ልጅ የልዑል ዓለማየሁ የፀጉር ዘለላ እና ከመቅደላ ጦርነት በኋላ በእንግሊዝ ጦር ተዘርፈው የተወሰዱ የተለያዩ ቅርሶች ተጠቃሽ ናቸው።

የልዑል ዓለማየሁ የፀጉር ዘለላ፣ የካፒቴን ስፒዲ ፀጉር፣ የጄኔራል ናፒር ፎቶግራፍ፣ ሁለት በብር የተለበጡ የቀንድ ዋንጫዎች፣ አንድ የቀንድ ዋንጫ፣ ስለ ልዑሉ የተፃፉ ደብዳቤዎች፣ ስለ መቅደላ የተፃፈ መጽሔት፣ በመቅደላ ጦርነት ጊዜ አገልግሎት ላይ የዋለ የጦር ጋሻ፣ ከመቅደላ የተዘረፈ የመድኃኔዓለም ታቦት ለባለቤቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተመልሷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ሰሞኑን ፤ በዘመናዊቷ ኢትዮጵያ የቴክኖሎጂ መነቃቃት ትልቅ ማሳያ ተደርጋ የምትወሰደው፤ በ1935 ዓ.ም ሄር ሉድዊግ ዌበር በተባለው ጀርመናዊ ኢንጂነር እና የንጉሡ ፓይለት በወቅቱ ከነበሩ ኢትዮጵያውያን ጋር በመሆን በኢትዮጵያ የተሠራችው የመጀመሪያዋ «ፀሐይ» በመባል የምትታወቀው አውሮፕላን ከ88 አመታት በባዕድ ሀገር ቆይታ በኋላ ወደ ሀገሯ ተመልሳለች፡፡

የአውሮፕላኗ ወደ ሀገር ውስጥ መመለስ እንደሀገር ቅርሶቻችንን ከያሉበት የማሰባሰብ ጥረት ትልቅ እመርታ ላይ እንዳለ አመላካችና ከፍያለ የዲፕሎማሲ ስኬት ማሳያ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ዶ/ር፣ ለታሪክና ለታሪካዊ ቅርሶች ያላቸውን ከበሬታ በተጨባጭ ያሳየ ጭምር ነው!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የምርት ብክነት- የወቅቱ አንገብጋቢ አጀንዳ

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

ወቅቱ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ወሳኝ የምርት መከዘኛ እና መሰብሰቢያ ወቅት ነው፡፡ በተለይም የሰብዕል እህሎች የሚታጨዱበትና ወደ አውድማ የሚወሰዱበት እና የሚወቃበት ነው። ይሁንና በአብዛኛው አሠራሩ ባህላዊ ከመሆኑ የተነሳም ምርት ለከፍተኛ ብክነት የሚዳረግበት ነው፡፡

በእርግጥ የምርት ብክነቱ በዚህ ወቅት ብቻ ሳይሆን የተመረተው ወደ ቤት ከገባ በኋላም ምርት በሚከዘንበት ወቅት አሠራሩ በተለመደው መንገድ ባህላዊ ከመሆኑ የተነሳ ተጨማሪ የምርት ብክነት ያጋጥማል። ይህም አርሶ አደሩን በየወቅቱ የሚፈትን መሠረታዊ ችግር ነው፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን አርሶ አደሩ የልፋት ዋጋውን በበቂ ደረጃ እንዳያገኝ እያደረገው ነው፡፡

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ ኢትዮጵያ 110 ሚሊዮን ሄክታር መሬት አላት፡፡ ከዚህ ሀብት ውስጥ ግማሽ የሚሆነው ለእርሻ መዋል የሚችልና ምርታማነትን በአግባቡ የሚሰጥ ነው፡፡ ይህም ሆኖ በአግባቡ ጥቅም ላይ የዋለው እጅግ በጣም አነስተኛ ነው፤ ቢበዛ ከ25 እስከ 30 ከመቶ የሚሆነው ነው፡፡

ሀገሪቱ ካሉት አጠቃላይ የእርሻ መሬት ውስጥ ደግሞ በመስኖ መልማት የሚችለው 10 ሚሊዮን ሄክታር ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ እየለማ ያለው ገና አንድ ሚሊዮን ነው፤ ዘጠኝ ሚሊዮን ሄክታር የሚሆነው መሬት በመስኖ ማልማት እየተቻለ አልለማም። በሀገሪቱ ከሚመረተው ዓመታዊ የሰብል ምርት ውስጥም በአማካይ ከ25 በመቶ በተለያየ ምክንያቶች ይባክናል።

መረጃዎቹ እንደሚያመለክቱት፤ ሀገሪቱ በአሁኑ ወቅት ማምረት ከምትችለው በታች እያመረተች ነው፤ ይህ ደግሞ ገበያን በማረጋጋት፣ የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ፣ ድህነትን እስከ ወዲያኛው ድረስ ተረት ለማድረግ በሚደረጉ ጥረቶች ላይ ከፍተኛ ፈተና እንደሚሆን ለመገመት የሚከብድ አይሆንም፡፡

በሀገሪቱ አሁን የሚስተዋለው የግብርና ሥራ በአብዛኛው በሚገባው መጠን በቴክኖሎጂ የታገዘ አይደለም፡፡ በተለምዶ አስተራረስ እና የምርት አሰባሰብ ላይ የተደገፈ ነው፡፡ ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት የነበረው የበሬ እና ገበሬ ቁርኝት አሁንም እንደቀጠለ ነው፡፡

ዘርፉን በቴክኖሎጂ ማዘመን የሚያስችል ሥራ በትኩረት ስላልተሠራ ዛሬም ድረስ የሀገሪቱ ግብርና ከእጅ ወደ አፍ ከመሆን የዘለለ ፋብሪካዎችን በሚፈለገው ደረጃ መመገብ አልቻለም፡፡ ሰፊ እና ለእርሻ ምቹ የሆነ መሬት ቢኖርም በታሰበው ልክ የተትረፈረፈ ምርት ማግኘት ሳይቻል ቀርቷል፤ ከዚህ የተነሳም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች በምግብ እህል እጥረት ውስጥ ይገኛሉ።

ሀገሪቱን ክፉኛ እየተፈታተነ ያለውን የምርት ብክነት ማስቀረት መቻል በሀገሪቱ የሚስተዋለውን የዋጋ ግሽበት ለመከላከል ለሚደረገው ጥረት ውጤታማነት ትልቅ አቅም እንደሚሆን ባለሞያዎች ይናገራሉ፡፡ ጉዳዩ በመንግሥት ፖሊሲ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶለት በሚገባ ሊሠራበት እንደሚገባም ምክረ ሃሳብ ያቀርባሉ፡፡

**ሀገሪቱን ክፉኛ እየተፈታተነ ያለውን የምርት ብክነት ማስቀረት መቻል በሀገሪቱ የሚስተዋለውን የዋጋ ግሽበት ለመከላከል ለሚደረገው ጥረት ውጤታማነት ትልቅ አቅም እንደሚሆን ባለሞያዎች ይናገራሉ**

የምርት ብክነት በሀገሪቱ ካለው የማክሮ ኢኮኖሚው ጋርም በቀጥታ የሚያያዝ እንደሆነ፤ በዚህ ደረጃ ከፍተኛ የሆነ ምርት እየባከነ ማክሮ ኢኮኖሚውን አያዛባውም ማለት እንደማይቻል ይናገራሉ፡፡ አስቸኳይ በጥናት ላይ የተመሠረተ መፍትሔ ሊፈለግለት እንደሚገባ ይመክራሉ።

በየጊዜው እየጨመረ ካለው የሕዝብ ቁጥር እና የዜጎች መሠረታዊ ፍጆታ በፍጥነት እየናረ ባለበት ሁኔታ የምርት ብክነት ፈጥኖ መከላከል ካልተቻለ፤ ሊያስከትከል የሚችለው ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ከፍያለ ይሆናል፡፡

ምርት ከተሰበሰበና ጎተራ ከገባ በኋላም በአይጥና ነብሳት እንዳይበላ የጥንቃቄ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ከአርሶ አደሮች ጋር የቀረበ ግንኙነት መፍጠርና ግንዛቤዎችን ማሳደግ ተገቢ ነው። የልፋቱ የተሻለ ተጠቃሚ የማድረግ ትክክለኛ መንገድም ነው።

አርሶ አደሩ ከቴክኖሎጂ ጋር ያለውን ቁርኝትና ልምምድ በማሳደግ የምርት ብክነት የሚቀንስበትን መሠረታዊ ግንዛቤ መፍጠር፤ በማንኛውም የሀገሪቱ ክፍሎች እንደ አስፈላጊነቱ እና እንደየምርቶቹ ሁኔታ የምርት ብክነትን ለመቀነስ ዘመናዊ የሰብል መሰብሰቢያ ማሽን በብዛት ጥቅም ላይ ማዋል ያስፈልጋል፡፡ እስካሁን ያለው የሚበረታታ ሆኖ መንግሥትም ለጉዳዩ የተለየ ትኩረት ሰጥቶ ሊንቀሳቀስ ይገባል፡፡

በዚህ ደግሞ በውጤታማነቱ በአፍሪካ ደረጃ እንደተምሳሌት የሚነገርለት የሀገሪቱ ግብርና ኤክስቴንሽንን እንደ አንድ ስትራቴጂክ ማስፈጸሚያ አቅም አድርጎ መውሰድ፤ የምርት ብክነት መከላከልን ተጨማሪ የትኩረት አቅጣጫው አድርጎ እንዲወስደው ማድረግም ይቻላል።

ከችግሩ አሳሳቢነት አንጻር የፖሊሲ ማዕቀፍ የሚያስፈልገው፤ ከዚያም ባለፈ የምሁራንን ወይንም በዘርፉ የሠለጠኑ ባለሙያዎች ንቁ ተሳትፎ በስፋት የሚጠይቅ ስለመሆኑም በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች ይመክራሉ፡፡

እንደ ሀገር በቅድመ ምርትና ድህረ ምርት ላይ የሚስተዋሉ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ማስተካከል ላይ ባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊ አሠራር ሊከተሉ ይገባል፡፡ በተለይም ምርትን ከብክነት ለመታደግ ቴክኖሎጂ እና የቴክኖሎጂ ሥርፀት ላይ በአንክሮ መሥራት ያስፈልጋል፡፡ የምርት ብክነትን በማስቀረት ውጤታማ የሆኑ ሀገራትን ምርጥ ተሞክሮ እና ልምድ መቅሰምም እጅግ አስፈላጊው ይሆናል የሚል እምነት አለኝ፡፡

ኢትዮጵያ ምርትን ከብክነት ለመከላከል ያላትን አቅሞች፣ በተለይ ጽንሰ ሃሳብ እና ተግባርን በማዛመድ ይህ ነው የሚባል ሀገራዊ ውጤት ማስመዝገብ አልቻለችም፡፡ ምርት ከተመረተ በኋላ የሚስተዋለው ከፍተኛ ብክነት በበቂ ደረጃ አልተገታም፡፡ በመሆኑም ችግሩን እንደ አንገብጋቢ ችግር ወስዶ ለመፍትሔ መትጋት ለይደር የማይተው የቤት ሥራ ነው። በዚህ ላይ ሁሉንም አማራጮች መጠቀም ይገባል፡፡

# በዩኒቨርሲቲዎች መካከል ኢትዮጵያዊ ትስስር የሚፈጥር የባህል ማዕከላት ፌስቲቫል ሊካሄድ ነው

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- በዩኒቨርሲቲዎች መካከል ኢትዮጵያዊ ትስስር የሚፈጥርና የባህል ማዕከሉ ከተቋቋመ ጀምሮ ባለፉት ሰባ አመታት ያልተከናወነ የመጀመሪያው ዓመታዊ የዩኒቨርሲቲዎች የባህል ማዕከላት ፌስቲቫል ሊያካሂድ መሆኑን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የባህል ማዕከል አስታወቀ። ተቋሙ ፌስቲቫሉን አስመልክቶ ትናንት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋዜጣዊ መግለጫ ተሰጥቷል።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የባህል ማዕከል ዳይሬክተር ተስፋዬ እሸቱ (ረዳት ፕሮፌሰር) እንዳሉት ፌስቲቫሉ ለመጀመሪያ ጊዜ የተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎችን ባህል ማዕከላት የሚያስተሳስር ነው። ኢትዮጵያዊ መተዋወቅ፣ መግባባትና መዋደድን የሚያበረታታም ጭምር ነው።

የፌስቲቫሉ ዋና ዓላማ በትምህርት ተቋማት መካከል የሚደረግ ትስስርን መፍጠርና ማጠናከር መሆኑን ያመላከቱት ዳይሬክተሩ፣ ባለመተዋወቅና ባለመናበብ የሚደርሱ ችግሮችን በመቅረፍ እውቀት መር አስተሳሰብ እንዲወጣ በማድረግ ሂደት ውስጥ የማይተካ ሚና እንዲኖረው ማድረግ መሆኑን ገልጸዋል።

በፌስቲቫሉ ላይ የባህል ማዕከላት ያላቸው ዩኒቨርሲቲዎች ብቻ ሳይሆኑ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኙ ሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ጥሪ ተደርጎላቸዋል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ፌስቲቫሉ የኢትዮጵያን ኪነጥበብ በማጉላት ዓለምአቀፍ ፌስቲቫል የመሆን እቅድ ሰንቋል ብለዋል።

በፌስቲቫሉ ሀገር በብዙ ታተርፍበታለች የተባሉ ጥናታዊ ጽሑፎች የሚቀርቡ ሲሆን ኮንሰርትና የጉብኝት መርሐግብሮች መካተታቸውም ተጠቅሷል። በጥናትና ምርምር ሲምፖዚየም ላይ ለተከታታይ ሦስት ቀናት ስምንት ጥናታዊ ጽሑፎች በስምንት የዩኒቨርሲቲው ፕሮፌሰሮች ይቀርባል።

ለሦስት ተከታታይ ቀናት የሚቆየው ፌስቲቫል በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ ውስጥ በሚገኘው መናፈሻ ፊትለፊት በልዩ ልዩ ዝግጅቶች እንደሚካሄድ ረዳት ፕሮፌሰር ተስፋዬ እሸቱ አመልክተዋል።

በኪነጥበብ ዝግጅቶች ደግሞ ከቀድሞ እስከ ዛሬ ያሉ ህብረ ዝማሬዎች፣ የዘመን ጨዋታዎች ፣ የግጥም መርሐግብር፣ ሰርከስ እንዲሁም አብዱ ኪያር፣ ሀና ግርማ፣ ጌታቸው ኃይለማርያም የሚሳተፉበት የሙዚቃ ኮንሰርት ስለመኖሩም በአዘጋጆቹ ተመላክቷል።

ከሲምፖዚየሙና ኪነጥበባዊ ዝግጅቱ በተጨማሪ ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የመጡ እንግዶች አዳዲስ የሥነጥበብ ማዕከላት ጉብኝትም ተካተውበታል።

የመጀመሪያው ዓመታዊ የዩኒቨርሲቲዎች የባህል ማዕከላት ፌስቲቫል ከጥር 27 እስከ 29/2016 ዓ.ም ለሦስት ቀናት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ በልዩ ልዩ ዝግጅቶች ታጅቦ በድምቀት እንደሚከናወን ታውቋል፡፡

# የኢትዮጵያ የአርብቶ አደር ፖሊሲ አህጉራዊ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

አደርነት - የምሥራቅ አፍሪካ ኅብረ-ቀለም» በሚል መሪ ሃሳብ በአዲስ አበባ ሚሌኒየም አዳራሽ ለሰባት ቀናት ሲካሄድ የቆየው የምሥራቅ አፍሪካ አርብቶ አደሮች ኤክስፖ ትናንት ተጠናቋል።

በኤክስፖው የማጠናቀቂያ መርሐ ግብር ላይ የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስትር ኢንጂነር አይሻ መሐመድ እንደተናገሩት፤ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የተካሄደው የምሥራቅ አፍሪካ አርብቶ አደሮች ኤክስፖ አርብቶ አደርነት ዓለም አቀፍ የኑሮ ዘዬ መሆኑን የታየበት ነው።

ኤክስፖው የምሥራቅ አፍሪካ አርብቶ አደሮችን በአንድ መንደር ያገናኘ፣ ትውውቅ የተደረገበት እና ይበልጥ ዝምድና የተፈጠረበት መሆኑን የጠቀሱት ኢንጂነር አይሻ፤ ኤክስፖው የቀጣና ትስስር በሚያጠናክሩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በጋራ የተመከረበት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

አርብቶ አደሩን እና ለአርብቶ አደሩ ጥቅም የሚታገሉ አካላትን እንዲሁም የዘርፉ ምሁራንን ያሳተፈው ኤክስፖ በበርካታ ሰዎች መጎብኘቱን ጠቁመው፤ ከሁሉም በላይ ኤክስፖው ለፖሊሲ መነሻ የሚሆኑ ሃሳቦች የተነሱበት፤ እንደ ሀገርም ትልቅ ስኬት የተገኘበት መሆኑን ተናግረዋል።

እንደ ኢንጅነር አይሻ አባባል፤ አርብቶ አደሩን በሁለንተናዊ መልኩ ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችሉ ፕሮግራሞችን ለመዘርጋት መሠረት የተጣለበት ነው። በዚህም እውነትም አርብቶ አደርነት የምሥራቅ አፍሪካ ኅብረ-ቀለም መሆኑን በዓይን የታየበት ነው፡፡

የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስትር ዴኤታ እንድሪያስ ጌታ (ዶ/ር)፤ ኤክስፖው የኢጋድ አባል ሀገራት ተወካዮች በተገኙበት መካሄዱን ገልጸው፤ በኤክስፖው የተለያዩ የፓናል ውይይቶች እና ኤግዚቢሽኖች መከናወናቸውን ተናግረዋል።

በኤክስፖው የክልል መንግሥታት፣ የልማት አጋሮች፣ መንግሥታዊ የሆኑ ድርጅቶች እና የግል ባለሀብቶች መሳተፋቸውን ጠቅሰዋል፡፡ በዚህም ዓለም አቀፍ የልማት ጸጋዎችን፣ የአርብቶ አደሩን እምቅ አቅም፣ የኢንቨስትመንት አማራጮችን እንዲሁም የፈጠራ እና የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ማሳየት መቻሉን አስረድተዋል።

ኤክስፖውን ከ20 ሺህ በላይ የሚሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች መጎብኘታቸውን የተናገሩት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በሌላ በኩል ከአራቱ የምሥራቅ አፍሪካ ክላስተሮች 250 የሚሆኑ ባለድርሻ አካላት በኤክስፖው መሳተፋቸውን ገልፀዋል።

የኢትዮጵያን የአርብቶ አደር ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ከምሥራቅ አፍሪካ ለመጡ ባለድርሻ አካላት የማስተዋወቅ ሥራ መሠራቱን ገልጸው፤ በዚህም ከኢጋድ አባላት ሀገራት ውስጥ የአርብቶ አደር ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ያላት ኢትዮጵያ ብቻ እንደሆነች ማወቅ መቻሉንም ተናግረዋል።

በቀጣይ በምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት ለአርብቶ አደርነት እውቅና ለመስጠት የሚያስችል የጋራ ስምምነት ለማጽደቅ እንደሚሠራ ከመግባባት መደረሱን አመልክተዋል፡፡ በአርብቶ አደር አካባቢዎች ባሉ የማዕድናት ሀብት ማኅበረሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ መሥራት እንደሚገባም ጠቁመዋል።

የምሥራቅ አፍሪካ የአርብቶ አደሮች ኤክስፖ «አርብቶ አደርነት - የምሥራቅ አፍሪካ ኅብረ-ቀለም» በሚል መሪ ሃሳብ ለ7 ቀናት በአዲስ አበባ ሚሌኒየም አዳራሽ መካሄዱ ይታወቃል።

# ከሕዝብና ከመንግሥት የተመዘበሩ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

መንግሥት ጋር በወንጀል የሚፈለጉ ሰዎችን አሳልፎ የመስጠት ስምምነት መፈረሙን፣ ከደቡብ ሱዳን፣ ከቦትስዋና እና ከቻይና መንግሥታት ጋር በወንጀል ጉዳዮች የሁለትዮሽ ትብብር ስምምነቶችን ለማድረግ ረቂቅ መዘጋጀቱን አንስተዋል።

በሴቶች እና ሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችና ወንጀሎችን መከላከልና ምርመራ ሥራውን ፈጣንና ውጤታማ ለማድረግም ትኩረት መሰጠቱን አንስተዋል።

ጉዳዩን የሚከታተል ክፍል መደራጀቱንም ተናግረዋል። በሴቶች እና ሕፃናት ላይ በሚፈጸሙ ወንጀሎች ጉዳይ በወንጀል ፈጻሚዎች ላይ የሚጣለው ቅጣት አስተማሪ እንዲሆን የቅጣት መመሪያውን መመልከት እንደሚገባም ጠቁመዋል።

በምስክሮችና ተከሳሾች አለመቅረብ የሚቋረጡ መዝገቦች የተለያዩ ምክንያቶች አሏቸው ያሉት ዶ/ር ጌዲዮን፤ ካለው የጸጥታ ሁኔታ ተጠርጣሪዎችን ለማምጣት የጸጥታ አካላትን ይፈታተናል፣ የሚሠሩት ባለሙያዎች በጣት የሚቆጠሩ ናቸው፣ የሥነ ምግባር ችግርም አለ፣ የፖሊስ የሰው ኃይልና አቅም ውስንነት፣ ምስክሮችን ማስፈራራት ከብዙ ጥቂቱ ተጠቃሾች መሆናቸውን ነው ያነሱት።

ችግሩን ለመቅረፍ የተቀናጀ ሥራ ይጠይቃል፤ ምስክሮችና ተከሳሾችን የሚያቀርቡ ክፍሎች በበቂ የሰው ኃይል መደራጀት አለባቸው ብለዋል።

የሕግና ፍትህ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይዘሮ እጸገነት መንግሥቱ በበኩላቸው፤ ቴክኖሎጂን በማስፋፋት ሥራዎችን ለማፋጠን እና የአገልግሎት አሰጣጥን ለማቅለል በፍትህ ሚኒስቴርና በተጠሪ ተቋማቱ የተጀመሩ ሥራዎች ሊጠናከሩ እንደሚገባ አሳስበዋል።

የፍትህ ትራንስፎርሜሽን እቅድ እውን ለማድረግ የሠራቸውን ሥራዎች፣ ክልሎች ተጠናክረው እንዲሠሩ፣ መሠረታዊና ማህበራዊ ፍትህ እንዲጎለብት የተሠራውንም በጥንካሬ አንስተዋል።

ሥራዎችን ዲጂታላይዝ የማድረግ ጅምር ተግባሩ እንዲፋጠን፣ የመንግሥት ሀብትን የሚያባክኑ አካላትን ተጠያቂ ማድረግ እንደሚገባም ነው ያነሱት።

በምስክሮችና በተከሳሾች አለመቅረብ የሚቋረጡ መዝገቦች በተለይም የሕዝብና የመንግሥት ጥቅም ያለባቸው የሙስና ወንጀሎች ጉዳይ ልዩ ትኩረት እንዲሰጥም አሳስበዋል።

በክርክርና በድርድር መንግሥት ያወጣ የነበረውን ሀብት በማዳን እንዲሁም የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ሰነድ፣ የግብዓት አሰባሰብ ሥራ እንዲሁም ኅብረተሰቡ ሃሳብ እንዲሰጥ የተደረገበት ተግባር አስተማሪ መሆኑም ነው የተነሳው።

የፍትህ ሚኒስትሩ ዶክተር ጌዲዮን ጢሞቴዎስ ባቀረቡት ሪፖርት በአጠቃላይ በግማሽ ዓመቱ በተቋሙ ከአንድ ቢሊዮን 347 ሚሊዮን ብር በላይ ተሰብስቧል። 168 የሕግ ማርቀቅ ሥራ ተሠርቷል ብለዋል።

ሰፊ ሕዝባዊ ውይይቶች የተሰባሰቡ ግብአቶችን በማካተት ረቂቅ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ መዘጋጀቱንም ዶክተር ጌዲዮን ጠቁመዋል።

ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ጋር በተያያዘም በባሕር ዳር፣ በጎንደር እና በኮምቦልቻ ከተሞች ባሉ ማቆያ ቦታዎች የሰብአዊ መብት አያያዝ ሁኔታ ተመርምሮ ለአስቸኳይ ጊዜ አስፈጻሚ ዕዝ ሪፖርት መቅረቡንም ነው ያነሱት። ምስክሮችና ተከሳሾች ባለመቅረባቸው ምክንያት በድምሩ ሦስት ሺህ 133 መዝገቦች ተቋርጠዋል ብለዋል።

# መከላከልና አክሞ ማዳን የሚችል ጠንካራ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በደማቸው እንዳለባቸው ተለይቶ ተገቢውን ክትትልና ሕክምና እንዲያገኙ ተደርጓል ብለዋል።

በወቅቱ ተገቢውን ክትትል ከተደረገ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን 87 በመቶ ማዳን እንደሚቻል ጠቅሰው፤ ባለፉት ስድስት ወራት አንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሰዎች ስኳር እንዳለባቸው ተለይተው ሕክምና እንዲጀምሩ ተደርጓል። ከ98 ሺህ በላይ ዜጎችም የደም ግፊት እንዳለባቸው ተረጋግጦ ሕክምና እንዲያገኙ ተደርጓል ብለዋል።

ካንሠርን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ጥረት እየተደረገ መሆኑን ጠቁመው፤ በተለይ በርካታ ሴቶች ላይ ጉዳት እያደረሰ ያለውን የማህጸን በር ካንሠር ለመከላከል አንድ ሺህ 300 የሚደርሱ ተቋማት የመለየትና የማከም አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ተችሏል ብለዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለጻ፤ መንግሥት ትኩረት አድርጎ ከሚሠራባቸው ጉዳዮች አንዱና ዋነኛው የእናቶችና ሕፃናትን ጤና ሽፋን ማሳደግ ነው።

በዚህም የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ሽፋንን 80 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ 72 በመቶ ማድረስ መቻሉን ጠቅሰው፤ በጤና ተቋማት የሚወልዱ እናቶች ምጣኔም 63 በመቶ ደርሷል ብለዋል።

ከ15 ዓመት በፊት የጨቅላ ሕፃናት ሞት ምጣኔ 700/100ሺህ እንደነበር አስታውሰው፤ አሁን ላይ ምጣኔውን 267/100ሺህ ማድረስ ተችሏል። በ2030 ደግሞ ወደ 70/100 ሺህ ዝቅ ለማድረግ ርብርብ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

በሌላ በኩል በግማሽ ዓመቱ ከ13 ቢሊዮን ብር በላይ የሚተመን ዋጋ ያላቸው መድኃኒትና የሕክምና ግብዓቶች ለጤና ተቋማት እንዲሰራጩ ማድረግ ተችሏል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በመደበኛ በጀት የሚገዙ መድኃኒቶች በ3ነጥብ6 ቢሊዮን ብር የተገዙ ናቸው። በአጋር ድርጅቶች ለሚደገፉ የተለያዩ የጤና ፕሮግራሞች በነፃ የሚሰራጩ መድኃኒቶችንና የሕክምና ግብዓቶች ከ9 ነጥብ4 ቢሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ ተገዝተው ለጤና ተቋማት እንዲሰራጩ ተደርጓል ብለዋል።

የፕሮግራም መድኃኒቶች አቅርቦት ሽፋን 87 በመቶ መድረሱን ጠቁመው፤ የመደበኛ መድኃኒቶች አቅርቦት ደግሞ 70 በመቶ ነው ሲሉም ገልጸዋል።

ሕይወት አድን የሚባሉ መድኃኒቶችን በተቻለ መጠን ለማቅረብ ጥረት ቢደረግም አጠቃላይ አቅርቦቱ መሻሻል ያለበት መሆኑን የጠቆሙት ሚኒስትር ዴኤታው፤ የሚስተዋለውን የመድኃኒት አቅርቦት ለማሳደግ የሀገር ውስጥ አቅራቢዎችን የመደገፍ ሥራ እየተሠራ እንደሆነም አብራርተዋል።

በተጨማሪም በዓለም ላይ ትልቅ አቅም ካላቸው ኩባንያዎች ጋር የሦስት ዓመት ስምምነት በመፍጠር በየዓመቱ የሚኖረውን መለዋወጥ ለማስቀረት ጥረት ተደርጓል ብለዋል።

በኢትዮጵያ 13 የሚደርሱ መድኃኒት ፋብሪካዎች መኖራቸውን አመልክተው፤ ለእነዚህ ፋብሪካዎች አስፈላጊው ድጋፍ ተደርጎላቸው 50 በመቶ የሚሆነውን መድኃኒት እንዲያቀርቡ እየተሠራ መሆኑን አስታውሰዋል።

# «የኅብረቱን ስብሰባ በስኬት በማጠናቀቅ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ።

«ዲፕሎማሲያችን ለብሔራዊ ጥቅማችን» በሚል መሪ ሃሳብ በሳይንስ ሙዚየም እየተካሄደ የሚገኘው የዲፕሎማሲ ሳምንት የፎቶግራፍ አውደ ርዕይ ላልተወሰነ ጊዜ መራዘሙም ተጠቁሟል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በቅርቡ የሚካሄደውን የአፍሪካ ሀገራት የመሪዎች ጉባኤ እና በሳይንስ ሙዚየም እየተካሄደ የሚገኘውን የዲፕሎማሲ ሳምንት አስመልክቶ ሳምንታዊ መግለጫ በትናንትናው ዕለት ሰጥቷል።

በወቅቱ የሚኒስቴሩ ቃል አቀባይ አምባሳደር መለስ ዓለም (ዶ/ር)፤ በመጪው የካቲት 6 እና 7 ቀን 2016 ዓ.ም የሚካሄደውን የአፍሪካ ኅብረት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ እንዲሁም በቀጣይ የሚካሄደውን የመሪዎች ጉባኤ ለማስተናገድ ከወዲሁ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ተናግረዋል።

ለስብሰባዎቹ ስኬት ብሔራዊ ኮሚቴ ተቋቁሞ የትራንስፖርት፣ የሎጂስቲክስ፣ የፀጥታ፣ የፕሮቶኮል ጉዳይና ሌሎችም ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ጠቁመው፤ ከመንግሥት ባሻገር የሚዲያው፣ የአገልግሎት ሰጪ ተቋማትና የሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ድጋፍ ወሳኝ ነው ብለዋል፡፡

ዓመታዊው ምክክር እንደከዚህ ቀደሙ በስኬት እንዲጠናቀቅ ማድረግ ቀዳሚ ተግባር ይሆናል ያሉት አምባሳደሩ፤ ኢትዮጵያ እንደ አስተናጋጅ ሀገርና ከሌሎች ሀገራት ጋር ያላትን ግንኙነት ለማጠናከርና ብሔራዊ ጥቅሟን ለማስጠበቅ ዕድሎችን የምትፈጥርበት አጋጣሚ መሆኑን አንስተዋል።

ከኅብረቱ ጉባኤ ጎን ለጎን ባለፈው ዓመት በተከናወነው የዲፕሎማሲ ሥራ ከ50 የሀገራት መሪዎችና ተወካዮች ጋር ስኬታማ ውይይት መካሄዱን አስታውሰው፤ ዘንድሮም ከስብሰባው በተጓዳኝ የሁለትዮሽ ውይይቶች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ አረጋግጠዋል።

የኅብረቱ ስብሰባ ከግብርና፣ ከአረንጓዴ ዐሻራና ከቱሪዝም ዘርፍ አንጻር የተሠሩ ሥራዎችን ለማስተዋወቅ ዕድል የሚፈጥር ነው ያሉት ቃል አቀባዩ፤ የአዲስ አበባን የዲፕሎማሲ ማዕከልነት ለማፅናትና ብሔራዊ ጥቅምን ማረጋገጥ የሚያስችሉ የሁለትዮሽና የባለብዙ ወገን ትብብሮችን ማሳደግ ዋነኛ የዝግጅቱ ተልዕኮዎች ይሆናሉ ብለዋል።

የኅብረቱ ስብሰባ በስኬት መካሔድ የኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ስኬት በመሆኑ ሁሉም ዜጋ የተለመደ ኃላፊነቱን እንዲወጣ ጠይቀዋል።

እንደ አምባሳደሩ ገለጻ፤ ከጥር 2 እስከ 24 ቀን 2016 ዓ.ም እንዲካሔድ ታስቦ በሳይንስ ሙዚየም የተከፈተው የዲፕሎማሲ ሳምንት የፎቶግራፍ አውደ ርዕይ የአፍሪካ ኅብረት ስብሰባን ተከትሎ የሚመጡ መሪዎችና ተወካዮች ለማስተናገድ ታስቦ ላልተወሰነ ጊዜ ተራዝሟል።

አውደ ርዕይው ላልተወሰነ ጊዜ የተራዘመው የኢትዮጵያን የዲፕሎማሲ ታሪክ በአውደ ርዕዩ ለማስመልከትና የዲፕሎማሲ ግንኙነት አማራጭ ለማስፋት ታሳቢ በማድረግ መሆኑን አስረድተዋል።

አውደ ርዕዩ የውጭ ግንኙነት፣ የዲፕሎማሲ እሴትና ዕድሎችን ለመጠቀም የዜጎች ድርሻን ማስገንዘብ የሚያስችል አጋጣሚን እየፈጠረ ይገኛል ብለዋል።

አምባሳደር መለስ አክለውም፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በጣልያን ቆይታቸው ያገኙት የፋኦ አግሪኮላ ዕውቅና እንዲሁም የ«ፀሐይ» አውሮፕላን ወደ ሀገሯ መመለስ በጎ የዲፕሎማሲና የገፅታ ውጤትን የሚያስገኝ መሆኑን በመግለጫቸው አንስተዋል።

በሌላ በኩል የኢትዮ-ሩሲያ የፖለቲካና የንግድ ምክክር ከዛሬ ጀምሮ በሞስኮ ከተማ እንደሚካሄድም አምባሳደር መለስ ገልፀዋል።





# “ስለ እናት” - እንደ እናት

**ማህሌት አብዱል**

በተለያዩ አበቦችና እፅዋት በተዋበውና በተንጣለለው ቅጥር ጊቢ ውስጥ የሚያማምሩ ሕፃናት ይጫወታሉ፡፡ ከውቡ መናፈሻ ትዕይዩ ተሰድረው የተሰሩት ቤቶች ጥግ ላይ የቆሙ ታዳጊዎች ደግሞ ያወካሉ፤ ይላፋሉ፡፡ አንድ የአዕምሮ እድገት ውስንነት ያለበት ጎረምሳ ደግሞ ዊልቸሩን እየገፋ ከወዲያ ወዲህ እየተዘዋወረ ከሚያየው ጋር ሁሉ ለማውራትና ለመጫወት ይሞክራል፡፡ ከፊሎቹ ታዳጊዎች ደግሞ ከሳሎናቸው ሆነው ቴሌቪዥን ይመለከታሉ፤ ዳቧቸውን እየገመጡ ይዝናናሉ፤ አንዳንዶቹም ከትምህርት ቤት መልስ መኝታ ክፍላቸው ሆነው ጋደም ብለው እረፍታቸውን ያጣጥማሉ፡፡

በሌላኛው ጊቢ በኩል ደግሞ ነርሶችና ሞግዚቶች ጨቅላና የጤና እክል ያለባቸውን ሕፃናት በመንከባከብ ስራ ተጠምደዋል፤ ሌሎች የሕፃናቱን ልብስ ያጥባሉ፤ ያጣጥፋሉ፡፡ ከወደ ማዕድ ቤቱ በር ስር ደግሞ እድሜያቸው በግምት 14 ዓመት የሚሆኑ ሁለት ልጃገረዶች አቀርቅረው ምስር ይለቅማሉ፤ እየለቀሙም በለሆሳስ የሆድ የሆዳቸውን ያወጋሉ፡፡

የወጥ ቤቷ እመቤትም ከረዳቶቿ ጋር በመሆን የልጆቹ የመመገቢያ ሰዓት ከመድረሱ በፊት ምግባቸውን ለማድረስ በሚመስል ሁኔታ ጉድ ጉዷን ተያይዛዋለች፡፡ ይህ ሁሉ ማራኪና ቤተሰባዊ ትዕይንት ታዲያ በሩህሩህ እናቶች የታጀበውና በጎ ፈቃደኞች የሚመራው የስለ እናት በጎአድራጎት ድርጅት የዘወትር እንቅስቃሴ ነው፡፡

በማሳደጊያው ድጋፍ ለቁምነገር ከበቁ አምስት ሺ ወላጅ አልባ ሕፃናት መካከል መሃሪ ጉተማ አንዱ ነው፡፡ በሃያዎቹ እድሜ መጀመሪያ ላይ የሚገኘው ይህ ወጣት የተወለደው በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሸዋ ዞን ቢሾፍቱ ከተማ ሲሆን፣ በስምንት ዓመቱ ወላጆቹን በሞት ሲያጣ ነው ከታላቅ ወንድሙ ጋር ማሳደጊያውን የተቀላቀለው፡፡

በ11 ዓመቱ የማሳደጊያው ቆይታ ሲያበቃ አሳዳጊ ቤተሰቦች አግኝቶ ወደ ውጭ የመሄድ እድል ገጥሞትም ነበር፡፡ ይሁንና አጎቱ ኃላፊነት ወስደው ሊፈርሙለት ባለመቻላቸው ጉዞው ተሰናከለ፡፡ በመሆኑም ወደ ሁለተኛውና ግሩፕ ሆም ወደተባለው የተቋሙ የማሳደጊያ መርሃ ግብር በመግባት እሱና ወንድሙ ከሌሎች ታዳጊዎች ጋር በመሆን አብረው ወደ ሚኖሩበት ቤት አቀና፡፡

በዚያም ሁሉም ነገር ተሟልቶለትና አሳዳጊ እናት ተመድቦለት እስከ 10ኛ ክፍል ደረሰ፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን በዓለምአቀፍ በጎአድራጊዎች ድጋፍ የስነ-ስዕል ስልጠና የወሰደ ሲሆን፣ በሂደት ለጥበቡ ልዩ ፍቅር እያደረበትና ችሎታውን እያዳበረ መጣ፡፡ ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ገብቶም በሳይኮሎጂ ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪውን አግኝቷል፡፡ በአሁኑ ወቅት ደግሞ ወደተቋሙ ተመልሶ እንደ እናት ተንከባኮቦ ያሳደገውን ተቋም መልሶ በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡

ይህ ተቋም የተመሰረተው በ1994 ዓ.ም ወይዘሮ ሃና ብርሃኑ በተባሉ በጎ አድራጊ እናት አማካኝነት ነው። በወቅቱ ግለሰቧ ጥቁር አምበሳ ሆስፒታል በማኅበራዊ ጉዳይ አገልግሎት ዘርፍ ይሰሩ ስለነበር በኤች.አይ.ቪ ቫይረስ የተያዙ ወላጆች ልጆቻችን ጥለው ሲሞቱ የነበረውን አሳዛኝ ሁኔታ በእየለቱ ይመለከታሉ፡፡ በዚህ ችግር ምክንያት አሳዳጊ የሌላቸውን ሕፃናት ወደ ጎዳና ሲወጡ መመልከቱ ልባቸውን በእጅጉ ነካው፡፡

አንድ ቀን ግን “ዝም ብሎ ከመመልከት ይልቅ ለምን የበኩሌን አስተዋፅኦ አላበረክትም?” የሚል ጥያቄ ለራሳቸው ያነሳሉ፡፡ ለተወሰኑ ጓደኞቻቸውን ጉዳዩን ሲጫውቷቸው ቀና ምላሽ አገኙ፡፡ እናም ቤት ፈለጉና ስለእናት የተባለች አንዲት ጨቅላ ሕፃን ከጎዳና ላይ ማሳደግ ጀመሩ፡፡ በዚህች ሕፃን አማካኝነት የበጎ አድራጎት ሥራቸውን አሃዱ ብለው የጀመሩት እኚህ እናት፣ የድርጅቱንም ስም ለልጅቷም ማስታወሻ ምግባሩም እንደእናት ይሆናል በሚል “ስለእናት” አሉት፡፡

ወይዘሮ ሃና በርካታ ችግረኛና ወላጅ አልባ ሕፃናትን ከጎዳና እያነሱ፤ እንዲሁም በያሉበት ቤት አስፈላጊውን ድጋፍ እያደረጉ አስተምረው ለወግ ማዕረግ አብቅተዋል። በብዙ ውጣ ውረድ ሆነው ለዘጠኝ ዓመት ከመሩ በኋላ በወቅቱ በነበረባቸው ቤተሰባዊ ጫና ምክንያት ተቋሙን ለቀጣይ ትውልድ ማስተላለፍ ይገባል የሚል ውሳኔ ላይ ደረሱ፡፡ እናም ራዕያቸውን የሚጋራና በጎ ትውልድ የመገንባት ህልም ሰንቆ በራሱ መንገድ ጥረት ሲያደርግ ለነበረው ወጣት ያሬድ አብዱ አስተላለፉ፡፡ ያሬድም የእኚህን እናት አደራና እምነት በከንቱ አላስቀረም፤ ራዕያቸውንም ሆነ ድርጅቱን ተረክቦ ላለፉት 21 ዓመታት በስኬት ጎዳና እየመራ ቆየ፡፡

የድርጅቱ ዋና ስራአስኪያጅ ያሬድ አብዱ ተቋሙን በኃላፊነት ተረክቦ ለመስራት ጥያቄያቸውን የተቀበለው የእሱም የልጅነት ራዕዩ ስለነበር እንደሆነ ያነሳል፡፡ ይሁንና ዋና ምክንያት የሆኑት ግን በኤች አይ ቪ ኤድስ ወላጆቻቸውን ያጡ ያጎቱ ልጆች እንደሆኑ ይጠቅሳል። ‹‹በጎነትን የተማርኩት ከእናቴ ነው፤ አራት የአጎቴን ልጆች የሙት አደራ ተቀብላ ለማሳደግ ሞክራለች፤ ይሁንና ከራሷ ልጆች ጋር ተዳምሮ አቅም ቢፈትናት በእኛ ወትዋችነት ለማሳደጊያ ለመስጠት ተገደደች፤ ያ አጋጣሚ ነው፤ እኔም ወደፊት እንደ አጎቴ ልጆች ወላጅ ያጡ ሕፃናትን ሕይወት መታደግ አለብኝ የሚል ውሳኔ ላይ ያደረሰኝ›› ሲል ያብራራል።

እንደ እድል ሆኖ የሚሰራበትም ዓለምአቀፍ የበጎአድራጎት ድርጅት ስለነበርና በልቡ ለዘመናት ያቆየው ሕልሙን እውን ለማድረግ በግሉ በሚጣጣርበት ወቅት ከወይዘሮ ሃና ጋር ተቀራረበና እቅዱ እንደ ሰመረለት ይናገራል፡፡

ለላፉት 12 ዓመታት ተቋሙን በመምራት ላይ የሚገኘው አቶ ያሬድ በተቋሙ የሚያድጉ ሕፃናት ቁጥር ከመጨመር በዘለለ መሰረታዊ ፍላጎታቸው እንዲሟላ፤ ከሁሉም በላይ ተቋማዊ ቅርፅ ከመያዝ ይልቅ ማኅበረሰቡን መስለውና ከማኅበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው እንዲያድጉ ጥረት ይደረጋል፡፡ በተለይም ከተቋሙ ሲወጡ የሚያጋጥሟቸውን ፈተናዎች በብቃት መወጣት ይችሉ ዘንድ ከ11 ዓመት በኋላ ሁሉም ወጪያቸውን በመሸፈንና ቤት በመከራየት እንዲሁም የምታሳድጋቸው እናት በመመደብ የሚያድጉበትን ስርዓት ማዘጋጀቱን ይገልጻል፡፡

እንደዋና ስራ አስኪያጁ ማብራሪያ፤ ስለእናት በተለያዩ የሕፃናት እንክብካቤ አማራጮች ሁሉ የሚሰራ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ሕፃናቱ በቤተሰባቸው ውስጥ እያሉ ወጪያቸውን በመሸፈን፤ በተለያየ ምክንያት ከቤተሰባቸው የጠፉ ሕፃናትን በማቀላለቀል ከኅብረተሰቡ ጋር እንዲኖሩ ማድረግ፤ የሕፃናቱ ቤተሰቦች ራሳቸውን እንዲችሉና ልጆቻቸውን እንዲረዱ መልሶ ማቋቋም፤ ሕፃናት የጉዲፈቻ ቤተሰብ እንዲያገኙ ማድረግ፤ አማራጭ ሲጠፋና ሌሎች እድሎች እስኪገኙ ድረስ በተቋም ውስጥ አስፈላጊውን ድጋፍና እንክብካቤ የማድረግ ሥራ ይሰራል፡፡

በአሁኑ ወቅት ከአንድ ሺ 560 በላይ ሕፃናት እንደሚደግፍ ጠቅሶ፣ ከእነዚህ ውስጥ ከአንድ ሺ 300 በላይ የሚሆኑት በውጭ ሆነው የትምህርት ቤት ወጪያቸው የሚሸፈንላቸው መሆኑን ያስረዳል። በተቋሙ ውስጥ ሆነው የሚያድጉት ደግሞ 59 መሆናቸውን ገልጾ፣ ከእነዚህ ውስጥ ከፊሉ የአዕምሮ እድገት ውስንነት እንዳለባቸው ነው የጠቆመው፡፡

‹‹ይህ ተቋም ጊዚያዊ ማረፊያቸው እንጂ የዘላለም መኖሪያቸው እንዲሆን አይፈልግም›› የሚለው አቶ ያሬድ፣ ይልቁንም ትክክለኛ ትውልድ ማፍራት ይቻል ዘንድ ከተቋማዊ አስተሳሰብ የተላቀቀ፤ ማኅብረሰቡን መስሎና ወዶ የሚኖር፤ በውጣ ውረዶች የማይፈተን ጠንካራ ትውልድ እንዲሆኑ ከፍተኛ ጥረት እንደሚደረግም ያብራራል። ‹‹በተቋሙ ከሁሉም በላይ ትኩረት የሚሰጠው ሕፃናቱን ማሳደግ ብቻ ሳይሆን ከማኅበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው በመኖር ማኅበራዊ ሕይወት ኖሯቸው፤ ተግዳሮትን በራሳቸው መጋፈጥ የሚችል አቅም አዳብረው እንዲያድጉ ማድረግ ላይ ነው›› ይላል፡፡

እንደ ስለእናት በመሰሉ ተቋማት ትክክለኛ ሃገር ተረካቢ ትውልድ ማፍራት የሚቻለውም ሕፃናቱ የመጡበትን መንገድ በማየትና የቱ አማራጭ ለእነሱ ይሻላል? ብሎ በመለየት ዘላቂ መፍትሔ የሚያመጣውን መምረጥ ሲቻል እንደሆነም ያስረዳል። በዚህ ረገድ እሱ የሚመራው ይህ ተቋም ከሌሎቹ በተለየ ጤነኞቹን ብቻ ሳይሆን ከተለያየ አይነት ሕመም ጋር የሚኖሩትንም አብሮ የሚያሳድግ እንደመሆኑ ለእያንዳንዱ ልጅ እንደየእድሜውና የጤና ሁኔታው የሚበጀውን የድጋፍ አማራጭ በመለየት እንደሚሰራ ነው ያስታወቀው፡፡

‹‹አቅም እስካለ ድረስ የተሻለ ነገር ማበርከት እንችላለን ብለን እናምናለን፤ መርዳት ስለሚለው ሃሳብ ኅብረተሰቡ ግንዛቤ እንዲኖረው እንፈልጋለን›› የሚለው አቶ ያሬድ፣ በዚህ ረገድም ትልቅ ኃላፊነት ያለባቸው የመንግስት ተቋማት በሚገባቸው ልክ እያገዙ አለመሆኑን አስታውቋል፡፡ በተለይ የእነሱ ድርጅትም ሆነ ሌላው የሚሰራውን በጎ ስራ በመረዳት ውስብስብ አሰራሮችንና ቢሮክራሲዎችን በማስቀረት ረገድ ድጋፍ ሊያድርጉልን ይገባል የሚል እምነት አለው፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ ያጋጠመውን ችግር አብነት ሲጠቅስም ‹‹በጉዲፈቻ ወደ ውጭ የሄዱ ሕፃናት አዋጥተው እዚህ ላሉት ሕፃናት ሁለት ዊልቸርና ከ50 በላይ ካርቶን የሚሆን የተለያየ ችግር ላለባቸው ሕፃናት የሚውል የአዋቂዎች ዳይፐር ልከውልን ነበር፤ ይሁንና የኢትዮጵያ አየር መንገድ ቢተባበረንም ጉምሩክ በነፃ ሊያስገባልን ባለመቻሉ ምክንያት ብዙ መንገላታት እየደረሰብን ነው›› ሲል ያመለክታል፡፡

በተለይ ዳይፐሩ ገንዘቡም ቢኖርም እንኳን እዚህ ሃገር እንደልብ የማይገኝ በመሆኑ እጅግ እየተንገላታን ስለመሆኑ አስታውቋል፡፡ በተመሳሳይ በርካታ ተቋማት ከአንድ ብር ጀምሮ ድጋፍ የሚያደርጉበት፤ ስምና ዝናቸውን በመያዝ ሥራቸውን ማስተዋወቅ የሚችሉበት እድል እንዲፈጥሩላቸው ጠይቋል፡፡

‹‹በተለይም የመንግስት ተቋማት ኃላፊዎች ስለእናትን እንዲጎበኙና ስራውን ተረድተው እገዛ እንዲያደርጉለትም ጥሪ አቀርባለሁ›› ያለው አቶ ያሬድ፣ በተመሳሳይ የሚዲያ ተቋማት ድልድይ በመሆን ማኅበራዊ ኃላፊነታቸውን መወጣት እንዳለባቸው አስገንዝቧል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ ብዙ የግል ተቋማት መስጠት ቢፈልጉም አስገዳጅ ሕግና ደንብ ባለመኖሩ ምክንያት ከድጋፍ የሚታቀቡበት ሁኔታ መኖሩን ዋና ስራአስኪያጁ አመልክቷል፡፡ ‹‹ከትርፍ ላይ የተወሰነ በመቶኛ ለማኅበራዊ አገልግሎት እንዲሰጡ የሚያስገድድ ሕግ ቢኖር የበርካታ ሕፃናትን ሕይወት መታደግ ይቻላል›› ሲልም ይገልጻል፡፡

‹‹እንደ ማኅብረሰብ እኛ ኃላፊነታችንን እየተወጣን ነው፤ ያገባናል ብለን በርካታ ችግረኛ ሕፃናትን እየረዳን ነው፤ ከችግሩ ስፋት አንፃር እንደኛ ያሉ ተቋማት ብቻቸውን የሚወጡት አይሆንም›› ይላል፡፡ በተለይ እንደ ኢትዮቴሌኮም ያሉ ትልልቅ ተቋማት የድጋፍ እቅዳቸውን ከባዕላት ባለፈ ቀጣይነት ያለው፤ የሚታይና የሚዳረስ ስርዓት ቢያበጁለት መልካም ባይም ነው፡፡

ወይዘሮ እመቤት ክብረት ልጆቻቸው በድርጅቱ ድጋፍ ከሚያገኙ ወላጆች አንዷ ናቸው፡፡ ባለቤታቸው የልብ ሕመምተኛ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ የማይሰሩ በመሆናቸው ልጆቻቸውን ለማስተማርም ሆነ ለማሳደግ እንደሚቸገሩ ይናገራሉ፡፡ ችግራቸውን ያየ የቀበሌያቸው አመራርም ከስለእናት በጎ አድራጎት ድርጅት ጋር እንዳገናኛቸው ይጠቅሳሉ፡፡ ድርጅቱ በየዓመቱ ለትምህርት የሚያስፈልገውን ወጪ የሚሸፍንላቸው ሲሆን፣ በየወሩም አራት መቶ ብር ድጎማ እንደሚያደርግላቸው ነው ያስታወቁት፡፡

ሌላዋ እናት ወይዘሮ ታደለች አየለም ሴት ልጃቸውን የሚያስተምርላቸው ይኸው ድርጅት እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ እሳቸው የአስም በሽተኛ በመሆናቸው እንደልባቸው መስራት አይችሉም፤ ባለቤታቸውም በሕይወት የሉም፤ በእዚህ ሁሉ የተነሳም ከፍተኛ ችግር ውስጥ ወድቀው እንደነበር ያስታውሳሉ፡፡ በድርጅቱ ድጋፍ ማግኘት ከጀመሩ ወዲህ ግን በተለይ ስለ ልጃቸው የትምህርት ወጪ እንደማይጨነቁ ያስረዳሉ።

እንደ እሳቸው በበሽታ ውስጥ ሆነው ብቻቸውን ልጆቻቸውን የሚያስተምሩ ወላጆች ድጋፍ በማጣታቸው ሳቢያ ልጆቸውም ሆነ እነሱ ወደጎዳና የሚወጡበት አጋጣሚ መኖሩን ጠቅሰውም ሌሎች አቅሙ ያላቸው ግለሰቦች እንደ ስለእናት ያሉ በጎ አድራጊ ድርጅቶችን በመደገፍ የሃገርን ሸክም እንዲያቃልሉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## የወጣቶች አዕምሮ ጤና እና የዲጂታል ሚዲያ ተጽዕኖ

ክብረአብ በላቸው



የአዕምሮ ጤና ሲቃወስ፤ የግለሰብን የየዕለት ተግባር በማዛባት፣ ከሰዎች ጋር ያለውን ግንኙነት እና የሰውነት ሁኔታ ላይም የሚያሳድረው ተጽዕኖ ከፍተኛ ስለመሆኑ የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልጻሉ፡፡ ዕድሜ፣ ጾታን፣ የገቢ ሁኔታን ወይም ዘር ሳይለይ ሁሉም ሰው ለአእምሮ ጤና መታወክ በሽታ የሚጋለጥበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

ማኅበራዊና የገቢ ሁኔታ፣ ጥሩ ያልሆኑ የልጅነት ልምዶች፣ አፈጣጠርና መሰረታዊ የጤና ሁኔታዎች የአንድን ሰው የአእምሮ ጤንነት ሊወስኑ እንደሚችሉም ነው የሚነገረው። አብዛኛው የአእምሮ ጤና መታወክ ያለባቸው ሰዎች በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ የጤና ችግር እንደሚኖርባቸውም መረጃዎች ይጠቁማሉ። እንደመረጃዎቹ የአእምሮ ሕመም ዓይነቶች ጭንቀት፣ የስሜት መለዋወጥ (መቃወስ) እና ስኪዞፍሬኒያ (ከእውነታው ዓለም መዛባት) ናቸው፡፡ ጭንቀት፥ የተለመደ የአእምሮ ሕመም እንደሆነም ይገለጻል፡፡ ይህ የአዕምሮ ጭንቀት ያጋጠማቸው ሰዎች ከአንዳንድ ነገሮች ወይም ሁኔታዎች ጋር የተያያዘ ከፍተኛ ፍርሃት ወይም ጭንቀት ያጋጥማቸዋል።

የጭንቀት ምልክቶች ከሚባሉት ውስጥ እረፍት ማጣት፣ ድካም፣ ትኩረት አለማድረግ፣ የጡንቻ ሕመምና የተቆራረጠ እንቅልፍ ይጠቀሳሉ፡፡ የስሜት መለዋወጥ (መቃወስ)፥ ከፍተኛ ደስታና ከፍተኛ ጭንቀት ሲፈራረቅ የሚስተዋል የአዕምሮ ሕመም ዓይነት ነው፡፡

በአዕምሮ ሕመም ተፅዕኖ በኢትዮጵያም ሆነ በመላው ዓለም ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዙት በአፍላ ዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ የማኅበረሰብ ክፍሎች እንደሆኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተሰሩ ጥናቶች ያሳያሉ። ከዓለም የቴክኖሎጂ ዕድገት ጋር ተያይዞ ዲጂታል ሚዲያው በአዕምሮ ጤና ላይ እያሳደረ ያለው ተፅዕኖ ከፍተኛ እንደሆነ ብዙዎች ያነሳሉ።

አቶ ሳሙኤል ቶሎሳ የአዕምሮ ጤና ባለሙያና በአማኑኤል ስፔሻላይዝድ የአዕምሮ ሕክምና ሆስፒታል የተመላላሽ ሕክምና ክፍል ኃላፊ ናቸው። እሳቸው እንደሚናገሩት፤ ዲጂታል ሚዲያው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዓለም አቀፍ ደረጃ በፍጥነት እያደገ እና ከፍተኛ ተቀባይነት ያገኘ በቢሊዮን በሚቆጠሩ የዓለማችን ሰዎች ጥቅም ላይ እየዋለ ነው። ይህ ማለት ደግሞ እራሱን የቻለ ማኅበራዊ፣ ስነልቦናዊና አዕምሮአዊ ከፍተኛ ጉዳት ይዞ የሚመጣ ነው ይላሉ።

በዓለም አቀፍ ደረጃ አምስት ቢሊዮን የሚሆን የዓለማችን ሕዝብ የዲጂታል ሚዲያ ተጠቃሚ እንደሆነ ጥናቶች ያመለክታሉ የሚሉት አቶ ሳሙኤል፤ በኢትዮጵያም ከፍተኛ ቁጥር ያለው ዜጋ የዲጂታል ሚዲያ ተጠቃሚ እንደሆነና ከሀገሪቱ የሕዝብ ቁጥር አብዛኛውን ድርሻ የሚይዘውና በዚህ የሚዲያ ተፅዕኖ ውስጥ የሚገኘው ወጣት መሆናቸውንና እንደ ሀገር ጉዳቱ ቀላል አለመሆኑንም አስረድተዋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ የአብዛኛው ወጣት የዲጂታል ሚዲያ አጠቃቀሙ ተቀራራቢ ወይም ተመሳሳይ መሆኑን የጠቀሱት ባለሙያው፤ ቴክኖሎጂ ይዞት የሚመጣው ጥሩ ዕድል እንዳለ ሆኖ የሚያሳድረው ተፅዕኖ የጎላ መሆኑን ጠቁመዋል።

‹‹ከጤና አንፃር ከ10 እስከ 19 ዓመት ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙት አዕምሮአቸው የሚያድግበት ግዜ ነው። ይህ ጊዜም ታዳጊዎች ነገሮችን ማየት የሚጀምሩበትና የአዕምሮ ክፍላቸውም የሚሰፋበት ወቅት ነው›› የሚሉት የአዕምሮ ሕክምና ባለሙያው አቶ ሳሙኤል፤ ስሜቶቻቸው፣ ከሰው ጋር ያላቸው መግባባት፣እያንዳንዱ ባህርያቸው የሚቀየርበት ወቅት እንደሆነና ትልቅ ጥንቃቄ የሚያስፈልግበት የዕድገት ደረጃ እንደሆነ አመልክተዋል።

``የወጣትነት ዕድሜ በውስጣችን ያለውን የሚሰማንን ነገር ሁለት ጊዜ ሳናስብ የምናወጣበት ወቅት ነው" የሚሉ አቶ ሳሙኤል፤ በባህርይ የእኔነት ወይንም የግለኝነት ስሜት የሚንጸባረቅበት፣ በትንሽ ነገር ቶሎ መደሰትና መበረታታት፤ በዛው ልክ ደግሞ በትንሽ ነገር መከፋት የሚስተዋልበት ዕድሜ በመሆኑ ይህንን ተረድቶ ማለፍ የሚያስፈልግ እንደሆነ አንስተዋል፡፡

የማኅበራዊ ሚዲያው የንግድ ሀሳብ ይዞ፣ ብዙ ሰዎች ይሳተፉበታል የሚለውን ከግምት ውስጥ በማስገባት የተመሰረተ እንደሆነ ይታወቃል የሚሉት አቶ ሳሙኤል ይህ በማኅበረሰቡ ውስጥ ግንዛቤ ሊያዝ ይገባል ብለዋል። የሚዲያው ዋና ዓላማ ገንዘብ ማግኘት እንደሆነና ለዚህም ተደራሻቸው ወጣቱ እንደሆነ አመልክተዋል።በአጠቃላይ የሚሰጠው ጥቅም እንዳለ ሆኖ የሚያስከትለው ችግርም ከፍተኛ እንደሆነ ይናገራሉ።

‹‹አንድ ወጣት በማኅበራዊ ሚዲያ ቀርቦ እያወራ ወይም ፎቶግራፉን እያጋራ በሚገኝበት ወቅት፤ ያለ ገደብ ማንኛውም ሰው ሊያየው ይችላል፡፡ በመሆኑም ተመልካቹ ያንን ሰው ሊያበረታታውም ወይንም ሊጎዳው የሚችልበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ለምሳሌ ሴት ብትሆን መልኳ ወይንም ሰውነቷ እንደማያምር አስተያየት ሊሰጣት ይችላል›› የሚሉት አቶ ሳሙኤል፤ ይህ ከፍተኛ መጨናነቅ፣ ድብርት፣ አለፍ ሲልም እራስን እስከማጥፋት የሚደርስ የስነ ልቦና ጫና ሊያስከትልባት እንደሚችል አስረድተዋል፡፡ ይህች ሴት ሁሌም ቆንጆ ሆና ለመታየት ከአቅሟ በላይ በሆኑ ነገሮች ላይ ግዜዋን እንድታጠፋ ሊያደርጋት ይችላል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

እንደ አቶ ሳሙኤል ገለጻ፤ ባደጉት ሀገራት ላይ የተሰሩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት አንዱ የድብርት ስሜት ነው። ይህም የሚፈጠረው የእኔን ፖስት ብዙ ሰው አየልኝ ወይም ወደደው፣ ወይም ብዙ ሰው አልተመለከተውም የሚለው ነገር ነው፡፡ ሁኔታው ወጣቶቹን በጣም ሊያስጨንቃቸውና ውድድር ውስጥም ሊከታቸው ይችላል፡፡ በመሆኑም የራሳቸው ማንነት ያልሆነውን ግን ሰዎች ሊወዱት ይችላሉ ብለው የሚያስቡትን ነገር ማሳየት ይጀምራሉ፡፡ ይህ ደግሞ ድባቴ ውስጥ በመክተት እራሳቸውን እንዲጎዱ ይገፋፋቸዋል፡፡ ለአእምሮ ጤና ችግርም ይጋለጣሉ፡፡

ወጣቶች አብዛኛውን ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት ኮምፒውተር እና የእጅ ስልካቸውን በመጠቀም ነው። ይህን እንደልማድ በመውሰዳቸው ምግብ ሲመገቡ እንኳን አያቋርጡም፡፡ በዚህ የተነሳም የአመጋገብ ስርዓት መዛባት እያስከተለባቸው ነው፡፡ ለከፋ የአዕምሮ ጤና ችግሮች ተጋላጭም እያደረጋቸው ይገኛል።

በዚህ ጊዜ ለረዥም ሰዓት እንቅልፍ ሳያገኙ የሚቆዩ ወጣቶች ቁጥርም ከፍተኛ እየሆነ ነው፡፡ ``አዕምሯችን በተፈጥሮ እንቅልፍ የሚተኛበት ሰዓት ጨለማ ወይም ብዙ ብርሃን በማይኖርበት ሰዓት እንደመሆኑ፤ ማኅበራዊ ሚዲያው ደግሞ አዕምሯችን መተኛት ባለበት ሰዓት ላይ ጠብቀን እንዳንተኛ ስለሚያደርገን ሕይወታችን እንቅልፍ ማጣትን ተከትሎ ለሚመጡ የጭንቀት፣ የስሜት መረበሽ፣ የሀዘን ስሜቶች ወይም ሕመሞች ተጋላጭ ያደርገናል›› ሲሉም አቶ ሳሙኤል አስረድተዋል።

በተጨማሪም ወጣቶች ለብዙ ሰዓት በአንድ ቦታ ተቀምጠው ስለሚውሉ የአካል እንቅስቃሴ አለማድረጋቸውን ተከትሎ በሚመጣ የጤና ችግርም እንደሚጋለጡ እና ይህም እንደ የልብ ሕመም አይነት በሽታዎች ተጋላጭ ይሆናሉ ብለዋል። እንደ አቶ ሳሙኤል ማብራሪያ፤ እንቅስቃሴ ካላደረግን ደም አይዘዋወርም። የአዕምሮአችንም አይነቃቃም። በዚህም ጫናዎች ተደራራቢ ይሆናሉ፡፡ የጤና ችግሩም በአዕምሮ ውስጥ ደም መፍሰስ ሊያስከትል የሚችልበት አጋጣሚ ይፈጠራል፡፡

> ወጣቶች አብዛኛውን ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት ኮምፒውተር እና የእጅ ስልካቸውን በመጠቀም ነው። ይህን እንደልማድ በመውሰዳቸው ምግብ ሲመገቡ እንኳን አያቋርጡም

በሌላ በኩል ወጣቶችና ሕፃናት አብዛኛውን ሰዓት ትምህርታቸውን ከማንበብ ይልቅ በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ስለሆነ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት፤ ትምህርት ቤት ሄደውም በተመሳሳይ በማኅበራዊ ሚዲያ ተፅዕኖ ስር ስለሚሆኑ ትምህርታዊ በሆነው ነገር ላይ የሚያሳልፉት ጊዜ ውስን ነው፡፡ ይህ እጅግ አደገኛ በመሆኑ የሚያስከትለው ጉዳት እንደ ሀገር በቀላሉ የሚታይ አይሆንም፡፡

የዲጂታል ሚዲያውን መቆጣጠር የምንችለው አይደለም የሚሉት የስነአዕምሮ ባለሙያው፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ ብዙ ሀገራት የሚቸገሩበት ጉዳይ ነው። ታዳጊ ሀገር ላይ ደግሞ ተፅዕኖው ከፍተኛ እንደሚሆን ተናግረዋል፡፡ ወላጆች ስለዲጂታል ሚዲያው ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ እንደሆነና ጉዳትና ጥቅሙን በትክክል የመገንዘብ ችግር የሰፋ ስለመሆኑ ያስረዳሉ፡፡

ይህንን ችግር ለመቀነስ እንደ ሀገር ፖሊሲ ሊኖር ይገባል የሚሉት አቶ ሳሙኤል፤ የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ፖሊሲ ኖሮ በተለይ ሕፃናት በቀላሉ እንዳይጠቀሙ ወይም ዕድሜያቸውን ባገናዘበ መልኩ መጠቀም እንዲችሉ እንደ ሀገር መመሪያዎች ያስፈልጋሉ ብለዋል፡፡ ከሌሎች ሀገራት ልምድ በመውሰድ ተደራሽ መሆን የሌለባቸው የዲጂታል ሚዲያ አማራጮች እንዲገደቡ መንግሥት ሀገር ተረካቢ ትውልድ እንዳይጠፋ መስራት አለበት ሲሉም ገልጸዋል።

እንደ አቶ ሳሙኤል ገለጻ፤ ቤተሰብ ወይም አሳዳጊ ከልጅ ጋር ስምምነት ላይ መድረስ ይኖርበታል። በተቻለ ጉዳቱን ማሳየት፣ ምን አይነት ችግር ይዞ እንደሚመጣባቸው ግንዛቤ ሊያዝ ይገባል፡፡ አደገኛ የሆነ በተለይ ማየት የሌለባቸውን ነገር ማየት እንዲችሉ ሆኖ ስለሆነ የተዘጋጀው በዚህ ረገድ ቤተሰብ የጋራ መግባባት በመፍጠር የቁጥጥር ስርዓት ማበጀት ይኖርበታል።

ዲጂታል ሚዲያው ስዎች በማንነታቸው፣ በቆዳ ቀለማቸው፣ በአፈጣጠራቸውና ባላቸው ተፈጥሮ የሚሰደቡበትና የሚንቋሸሹበት መድረክ በመሆኑ፤ ይህ ደግሞ ከፍተኛ የሆነ የስነልቦና ተፅዕኖ ያሳድራል። ይህንን ለመከላከል እንዲያስችል ሁለት ወገኖች ማለትም ወላጅ እና ልጅ በስምምነት ስለ ጉዳትና ጥቅሙ መወያየት አለባቸው፡፡ በዚህ መንገድ ቴክኖሎጂው የሚያደርሰውን ከፍተኛ የሆነ ዘርፈ ብዙ ጉዳት መቀነስ ይቻላል።

በስም ከሚታወቁ የማኅበራዊ ሚዲያዎች አማራጮች በተጨማሪ በይፋ የማይታወቁ ነገር ግን ኢትዮጵያን ጨምሮ በመላው ዓለም ከፍተኛ ቁጥር ያለው ተከታይ ያላቸው የበይነመረብ ሚዲያዎች አሉ። እነዚህ ሚዲያዎች የተቃኙት ሕፃናትና ወጣቶችን መሠረት በማድረግ ስለሆነ የሚለቋቸው የምስል፣ የድምፅና የቪዲዮ መረጃዎች ዕድሜን የማይመጥኑ ናቸው፡፡ ብዙ ሰዎች ያላቸው የሚዲያ አጠቃቀም ከቁጥጥር ውጭ የወጣና ለስነአዕምሮ ሕመም ተጋላጭ የሚያደርጋቸው ነው፡፡

በቤት ውስጥ በማኅበራዊ ሚዲያ ተገድቦ የሚኖር ልጅ ምን እየሰራ እንደሆነ ወላጆች አብረው ሆነው በየቀኑ በግልፅነት የሚያወሩበት ጊዜ ያስፈልጋቸዋል። ከዚህ ውጭ ወላጆች ልጆቻቸው በአካል ሄደው ከሰዎች ጋር ማውራት፣ መጫወት እንዲችሉ መንገድ መፍጠር አለባቸው፡፡ ከጎረቤት ልጆች ጋር ወይም ከትምህርት ቤት ጓደኞቻቸው ጋር አብረው ጊዜ እንዲያሳልፉም ማበረታታት ይኖርባቸዋል፡፡

በተጨማሪም ወላጆች ወጣት ልጆቻቸው በማኅበራዊ ሚዲያ ስለሚያጋጥሟቸው ነገሮች በግልፅ ከቤተሰብ ጋር እንዲያወሩ ማድረግ ይጠበቃል። ውይይቱ ታዳጊዎችንም ሆነ ወጣቶችን ካላስፈላጊ ነገር ለመታደግ ያግዛል፡፡ አሁን በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ዲጂታል ሚዲያን ተጠቅሞ የሚፈፀም ጥቃት እያደገ የሚሄድ እንጂ የሚቀንስ ባለመሆኑ በዚህ ረገድ መንግሥት የተለያዩ የሕግና የፖሊሲ ማዕቀፎችን በማውጣት ያሉትን ደግሞ በማጠናከር የተጠያቂነት ስርዓት እንዲኖር መስራት ያስፈልጋል ሲሉም ባለሙያው ምክረሀሳብ ሰጥተዋል፡፡ በሌላ በኩል ለሕፃናት ብቻ የሚሆኑ የማኅበራዊ ሚዲያ አማራጮች ሀገር ውስጥ በማበልፀግ አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ለማድረግ ሥራዎች ያስፈልጋሉ ብለዋል፡፡

‹‹ያለ አዕምሮ ጤና የለም›› የሚሉት ባለሙያው፤ ከዲጂታል ሚዲያው ጋር ተያይዞ የሚመጡ የአዕምሮ ሕመሞችን ቀድሞ ለመከላከልና እንደ ሀገር ወጣቱን ትውልድ ለማትረፍ በመጀመሪያ አሳዳጊ ወላጅ በተጨማሪም መንግሥትና የሚመለከታቸው አካላት በከፍተኛ ትኩረት መስራት እንደሚጠበቅባቸው አስገንዝበዋል።

# ተጠባቂው የድንጋይ ከሰል አምራች ፋብሪካ

**አስቴር ኤልያስ**

ኢትዮጵያ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ለኢንዱስትሪዎቿ የሚያስፈልጋትን የድንጋይ ከሰል ከፍተኛ መጠን ያለው የውጭ ምንዛሬ በመመደብ ከውጭ ስታስገባ ቆይታለች። ይህ ደግሞ ሲሆን የኖረው ሀገሪቱ በቂ የድንጋይ ከሰል ጥሬ እቃ ክምችት እያላት ነው:: መንግስት ለማእድን ዘርፉ የሰጠውን ትኩረት ተከትሎ የድንጋይ ከሰል በሀገር ውስጥ ለማምረቱ ስራ ትኩረት ሰጥቶ ሰርቶበታል፤ እየሰራበትም ይገኛል::

ይህን ተከትሎም ባለፈው ዓመት ሀገሪቱ የድንጋይ ከሰል ፍላጎቷን ማሟላት የቻለችው በሀገር ውስጥ የድንጋይ ከሰል ምርት መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ:: የድንጋይ ከሰል ፍላጎትን በሀገር ውስጥ የድንጋይ ከሰል ምርት ለመተካቱ ስራ መንግስት አሁንም ትኩረት ሰጥቶታል። የማዕድን ሚኒስቴር በተያዘው በጀት ዓመት መጀመሪያ ላይ ከሲሚንቶ እና ከድንጋይ ከሰል አምራች ኩባንያዎች ጋር ውይይት ባካሄደበት ወቅት የተጠቆመውም ይሄው ነው። በድንጋይ ከሰል ምርት ዕቅድ ላይ ሚኒስቴሩ ከአምራቾቹ ጋር ባደረገው ውይይት ወቅትም በዋናነት ሲጠቀስ የነበረው ከውጭ የሚገባውን የድንጋይ ከሰል ምርት ሙሉ በሙሉ በአገር ውስጥ ምርት የመተካት ጉዳይ ነበር::

በሀገሪቱ የድንጋይ ከሰል ሀብት በስፋት በሚገኝባቸው የተለያዩ አካባቢዎች የድንጋይ ከሰል ልማት እየተካሄደ ይገኛል:: የድንጋይ ከሰል ሀብት፤ ከሚገኝባቸው አካባቢዎች አንዱ ደግሞ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል የዳውሮ ዞን ይጠቀሳል:: የዚህን ሀብት መኖር ተከትሎ በዞኑ በታርጫ ዙሪያ ወረዳ የድንጋይ ከሰል ማበልጸጊያ ፋብሪካ ግንባታ እየተካሄደ ይገኛል::

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የጋዜጠኞች ቡድን፣ በዳውሮ ዞን ታርጫ ዙሪያ ወረዳ የካቲት 26 ቀን 2014 ዓ.ም የመሰረት ድንጋይ የተቀመጠለት ይህን የድንጋይ ከሰል ማበልጸጊያ ፋብሪካ በስፍራው ተገኝቶ ተመልክቷል:: ፋብሪካውን እያስገነባ ያለው የኢቲ ማዕድን ልማት አክሲዮን ማህበር የተባለው ኩባንያ ሲሆን፣ ግንባታውም ከ90 በመቶ በላይ ተጠናቅቋል፤ በቅርቡ ይመረቃል ተብሎም ይጠበቃል::

ከውጭ አገር የሚመጣውን የድንጋይ ከሰል ምርት በሀገር ውስጥ ምርት በመተካት አገሪቱ የድንጋይ ከሰል ከውጭ ስታስመጣ የምታወጣን የውጭ ምንዛሬ ከማስቀረት አኳያ የፋብሪካው ሚና የጎላ እንደሆነ ይነገራል:: በተለይም ኢትዮጵያ ያላትን ሀብት በመጠቀም ረገድም ሆነ በአካባቢው ለሚገኙ የስራ እድልን በመፍጠር በኩል የድንጋይ ከሰል ማበልጸጊያ ፋብሪካው ትልቅ ድርሻ እንደሚኖረው ታምኖበታል::


የኢቲ ማዕድን ልማት አክሲዮን ማህበር የድንጋይ ከሰል ማበልጸጊያ ፋብሪካ ግንባታ ፕሮጀክት ስራ አስኪያጅ ኢንጂነር በላይ አሰፋ ፋብሪካው ግንባታው ተጠናቅቆ ወደስራ ሲገባ በሰዓት 150 ቶን የድንጋይ ከሰል ማጠብ እና ማበልጸግ እንደሚችል ተናግረዋል:: በቀን 24 ሰዓት ከሰራ ደግሞ ሶስት ሺ 600 ቶን ማምረት እንደሚችል ገልጸዋል። ይህ አቅሙ በዓመት ሲሰላ ደግሞ አንድ ሚሊዮን ቶን የድንጋይ ከሰል የማጠብና የማበልጸግ አቅም እንደሚኖረው ተናግረዋል::

የፋብሪካ ግንባታ ፕሮጀክቱ ስራ አስኪያጅ፤ አትዮጵያ ለድንጋይ ከሰል ከ350 እስከ 400 ሚሊዮን ዶላር በዓመት ወጪ እንደምታደርግ ገልጸዋል:: የኢትዮጵያ የድንጋይ ከሰል ፍጆታ በጣም ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሰው፣ ፋብሪካው ይህን የሀገሪቱን የድንጋይ ከሰል ፍላጎት ያሟላል ተብሎ ይጠበቃል:: ይህ ማለት በአገር ውስጥ ትልቅ ፍላጎት እንዳለ የሚያመላክት ነው ብለዋል::

የዳውሮ ዞን በማዕድን ሀብት በከፍተኛ ሁኔታ የበለጸገ ቦታ መሆኑን አስታውቀዋል:: ከፍተኛ የማዕድን ክምችት እንዳለው በመታወቁ ነው የኢቲ ማዕድን ልማት አክሲዮን ማህበር በቢሊዮን ብር ኢንቨስት እያደረገ የሚገኘው::

የአክሲዮን ማህበሩ ተወካይ አቶ ወንድሙ ምትኩ ለኢፕድ እንዳሉት፤ ኢቲ በማዕድን ሚኒስቴር በ2014 ዓ.ም ከተመረጡ ስምንት ኩባንዎች አንዱ ነው:: ለፋብሪካው ግንባታ በዳውሮ ዞን ታርጫ ዙሪያ ወረዳ በ2014 ዓ.ም በወቅቱ የማዕድን ሚኒስትር የመሰረት ድንጋይ የተቀመጠለት ሲሆን፣ በወቅቱ ኢስት አፍሪካ የሚባለው ኩባንያ ለሚገነባው ተመሳሳይ ፋብሪካም በዚሁ በዳውሮ ዞን የመሰረት ድንጋይ ተቀምጦ ነበር። ይሁንና ኢስት አፍሪካ ኩባንያ እስካሁን ግንባታውን አልጀመረም::

የድንጋይ ከሰል ማበልጸጊያ ፋብሪካው የሚገኘው በዳውሮ ዞን፣ በተርጫ ዙሪያ ወረዳ፣ ላላ ገንጃ ቀበሌ ነው:: ኩባንያው ወደስራ የገባው አጠቃላይ አምስት ቢሊዮን ብር በጀት ይዞ ነው:: ፋብሪካው ለግብዓት ምልልስ ያመቸው ዘንድ መንገድ ጭምር ገንብቷል:: በእስካሁኑም ሒደት ለግንባታው ወደ አራት ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር ወጪ ወጥቷል ሲሉ ተወካዩ ተናግረዋል::



የኩባንያው ትልቁ ድርሻ የታጠበ የድንጋይ ከሰል ማቅረብ ነው የሚሉት የአክሲዮን ማህበሩ ተወካይ አቶ ወንድሙ፣ ይህ ፋብሪካ የተገነባውም ከውጭ አገር በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ወደ አገር ውስጥ የሚገባውን የድንጋይ ከሰል ምርት ለማስቀረት እንደሆነ ያስረዳሉ:: ወደስራ የተገባውም ከውጭ አገር ከሚመጣው የድንጋይ ከሰል 75 በመቶውን ኢቲ ማዕድን ልማት አክሲዮን ማህበር ኩባንያ ይሸፍናል ተብሎ ነው ብለዋል::

በዓመት አንድ ሚሊዮን ቶን የድንጋይ ከሰል ለሲሚንቶ ፋብሪካዎች ማቅረብ እንደሚችል ጠቅሰው፣ ፋብሪካውን የመገንባት ስራ ሙሉ በሙሉ መጠናቀቁንም አስታውቀዋል። የቀረው የኢንስታሊሽን ስራ ደግሞ ተጠናቅቆ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ለምረቃ እንደሚበቃ ጠቁመዋል::

አቶ ወንድሙ እንደሚሉት፤ በአካባቢው የድንጋይ ከሰል ክምችት መኖር ባለሀብቱን ወደስፍራው እንዲሳብ አድርጓል:: የባለሀብቶች ወደ አካባቢው መሳብ ለአካባቢው ማኅበረሰብ ብዙ እድሎችን ይዞ መጥቷል:: ለአብነትም ፋብሪካው ለላላ ገንጂ ቀበሌ ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ላሉ ወደ 900 የሚደርሱ ተማሪዎች ደብተርና እስክሪብቶ ልገሳ አደርጓል:: ይህም በብር ሲታሰብ አንድ ሚሊዮን 330 ሺ ብር ነው:: በተጨማሪ በሸባ ዮኒ ቀበሌ አንድ ጤና ኬላ ሰርቶ አስረክቧል:: በተመሳሳይ ላላ ገንጂ ቀበሌ ላይ የጤና ኬላ ግንባታ ተጀምሯል::

ሌላኛው ስራ ደግሞ የዳውሮ ዞን ሕዝብ ለሚጠቀምበት ሆስፒታል መድኃኒት ማስቀመጫ እና መሸጫ ለመገንባት ፋብሪካው እቃ እያስገባ ይገኛል:: የግንባታው የቅየሳ ስራ እያለቀ ሲሆን፣ ግንባታው ወደ ስድስት ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ብር ይፈጃል:: በሌላ በኩል ተጨማሪ የመማሪያ ክፍል እጥረት ያለበት ትምህርት ቤት በዞኑ ዋና አስተዳዳሪ ጥያቄ ቀርቦ ባለ አምስት የመማሪያ ክፍል ትምህርት ቤት ለመገንባት ቦታ ተረክቧል፤ እቃ ግዥ እያካሄደ ነው::

ፋብሪካው ከስራ እድል ፈጠራ ጋር ተያይዞ የድርሻውን እየተወጣ ሲሆን፣ አንዳንዴ ስራው ከፍ ሲል እስከ 420 ሰራተኞችን ያሰማራል፤ ይህ አሀዝ የስራው ሁኔታ በቀዘቀዘ ጊዜ ደግሞ ወደ 187 አካባቢ ይወረዳል:: ቋሚ ሰራተኞችን መቅጠር ገና እንዳልተጀመረም አቶ ወንድሙ ተናግረዋል::

ፋብሪካው የአካባቢ ብክለት እንዳያደርስ የሚጠበቅበትን እንደሚያደርግም ተወካዩ አስታውቀዋል። ፋብሪካው በአካባቢው ላይ ምንም አይነት ተጽዕኖ እንዳይኖረው ዘመናዊ የተረፈ ምርት መልሶ ማጣሪያ ቴክኖሎጂ የተገጠመለት መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህን ፋብሪካ ልዩ የሚያደርገውም አካባቢውን የማይበክል እና ራሱ የሚያወጣውን ተረፈ ምርት መልሶ ጥቅም ላይ እንዲውል የሚያደርግ መሆኑንም ይናገራሉ::

ፋብሪካው በጣም ዘመናዊ በሆነ ቴክኖሎጂ የተሰራ እንደሆነም ጠቅሰው፣ ፋብሪካውን የሰሩ ቱርካውያን ስራቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች አንድ ዓመት ድረስ ራሳቸውን ከስራው ጋር በአግባቡ እስከሚያለማምዱ አብረው ሲሰሩ እንደሚቆዩም ጠቅሰዋል።

የድንጋይ ከሰል ማበልጸጊያ ፋብሪካውን የተከለው የቱርኩ ቡካ ማሽነሪ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ እና ንግድ ኩባንያ ባለቤት ሊትፉ ዑዘር እንዳሉት፤ በዚህ ፋብሪካ ገጠማ ላይ ከ24 ዓመት በላይ ልምድ አላቸው:: ያንን ልምድ በመያዛቸውም ወደ ተለያዩ አገራት በመሄድ ፋብሪካዎችን ይገጥማሉ፤ የድንጋይ ከሰል ማበልጸጊያ ማሽኑ የተገጠመው ከዚህ ጥሬ የድንጋይ ከሰል ተወስዶ በድንጋይ ከሰሉ ይዘት መሰረት ነው::

ይህ በዳውሮ ዞን የተገጠመው ማሽን በተፈለገው አቅም ልክ እንዲሰራ ተደርጎ ነው:: ከዚህ ማሽን ገጠማ 95 በመቶውን ያካሄዱት እሳቸው በራሳቸው ዎርክሾፕ ውስጥ እንደሆነ ያስረዳሉ:: ማሽን በሚገጠምበትም ወቅት የፋብሪካው ባለቤት ምቹ ሁኔታ በመፍጠራቸው የገጠማቸው ችግር እንደሌለም ተናግረዋል:: የፋብሪካው ባለቤት እና ስራ አስኪያጆች ስራው እንዲቀላጠፍ በማድረጋቸውም ጊዜያችንን በአግባቡ እንድንጠቀም አስችለውናል ብለዋል::

እርሳቸው በሩሲያና ዮርዳኖስ በዚህ ማሽን ገጠማ ስራ ተሰማርተው ሰርተዋል:: በቱርክም በተለያየ ቦታ ማሽኖቹን ገጥመዋል:: በአፍሪካ ይህን ማሽን ሲገጥሙ ይህ የኢትዮጵያው የመጀመሪያቸው ነው:: ‹‹እዚህ መጥተን ስለሰራን በጣም ደስተኞች ነን:: ኢትዮጵያም ካሰብኳት በላይ ሆና አግኝቻታለሁ›› ሲሉ ገልጸዋል::

የቴክኖሎጂ ሽግግርን አስመልክተን ላነሳንላቸው ጥያቄ ፋብሪካውን የገጣጠመው ኩባንያ ባለቤት በሰጡት ምላሽ እንዳብራሩት፤ አሁን ባለው ሁኔታ ከቴክኒሺያኖቼ ጋር ያሉ ልጆች አምስት ያህል ናቸው። እነርሱም በደንብ እየለመዱ ነው:: የሚሰሩትን ሁሉ እያዩ እና አብረውን እየሰሩም በመሆኑ ልምድ እየቀሰሙ ናቸው:: እነዚህ ልጆች ስራውን አልቆ ሲወጡ በፋብሪካ ውስጥ የሚሰሩ ልምድ ያላቸው ሰራተኞች ይሆናሉ::

እንዲያም ሆኖ ማሽኑን ለተወሰኑ ጊዜ የሚያስቀጥሉ ሰዎች ከውጭ ይመጣሉ:: እነዚህ ሰዎች ማሽኑ ላይ ለሚሰሩ አካላት ስልጠና የሚሰጡ ናቸው:: ለስራው የሚያስፈልገው የሰው ኃይል የሚወሰነው እዚህ ቴክኖሎጂውን እየተከታተሉ በሚገኙት ሰዎች አቅም ላይ ነው:: ከእኛ ጋር እየሰሩ ያሉ ሰራተኞች የመስራት ፍላጎታቸው ከፍተኛና ስራውን በአግባቡም የሚከታተሉ ናቸው:: ማስተማር ያለብንን በሙሉ እያስተማርናቸው ነው:: ፋብሪካው ከአንድ ወር በኋላ ወደሙከራ ስራ ይገባል::

ፋብሪካውን የገጣጠመው ኩባንያ ባለቤት ሊትፉ ዑዘር ‹‹እኛ፣ የብረት ማበልጸጊያ፣ የብርና የወርቅ ማበልጸጊያ ማሽኖችንም እንሰራለን:: እስካሁን ኢትዮጵያ ውስጥ የማይገኝ ላቦራቶሪም ገጥመናል:: ይህ ላቦራቶሪ ከድንጋይ ከሰል ውጪ ያሉ ማእድናትን ለመፈተሽ አገልግሎትም ሊውል ይችላል›› ሲሉም አብራርተዋል::

ስንታየሁ መኩሪያ ጂኦሎጂስትና የኢቲ ማዕድን ልማት የላቦራቶሪ ባለሙያ ናቸው:: በላቦራቶሪው ለአገልግሎት የተዘጋጁት እቃዎች ከስድስት ሚሊዮን ብር በላይ እንደሚገመቱ ይጠቁማሉ:: ‹‹በሌሎች ፋብሪካዎች ያሉ ላቦራቶሪዎች ከሰሉ ከተቃጠለ በኋላ “ይህን ያህል ካሎሪ አለው” የሚለውን ብቻ የሚለዩ ናቸው፤ እንደ ኢቲ ማዕድን ልማት ላቦራቶሪ አይነት የድንጋይ ከሰሉን ጥራት አረጋግጦ የሚሰጥ ማሽን በኢትዮጵያ ውስጥ እስካሁን የለም ሲሉም ያብራራሉ:: በአሁኑ ወቅት የኢቲ ማዕድን ልማት፣ የድንጋይ ከሰሉን የካሎሪ መጠኑን፣ የአሽ ቫሊዩን ይለካል፣ መለካት ያለበትን ሁሉ መለካት ይችላል:: መረጃ የምንሰጠውም እያንዳንዱን መለካት ያለበትን ለክተን ነው በማለት ያስረዳሉ::

የላቦራቶሪ ባለሙያዋ ስንታየሁ የማዕድን ከፍተኛ ባለሙያ እና የስራ አስኪያጁ አማካሪም ጭምር ሲሆኑ፣ ላቦራቶሪው ገና የድንጋይ ከሰል ጥሬ እቃውን ሲቀበልም ሆነ ጥሬ እቃው ፋብሪካ ገብቶ ከወጣም በኋላ በላቦራቶሪው ፍተሻ እንደሚደረግበት ይናገራሉ:: በተለይም ከሰሉ ከታጠበ በኋላ ውጤቱ ምን አይነት ደረጃ ላይ ደረሰ የሚለውን እና ምን ያህል እሴት ጨመረ የሚለውም እንደሚፈተሽ አስታውቀዋል::

ላቦራቶሪው ዘመናዊ መሆኑን የገለጹት ባለሙያዋ፤ በአሁኑ ወቅት ለተቋቋመለት ፋብሪካ ይስራ እንጂ ለሌሎችም መስራት የሚያስችለው አቅም እንዳለውም አስታውቀዋል:: ለዚህ በምክንያትነት የጠቀሱት የተሰራበት ሌላው ጉዳይ አንዱ ገበያ ማስገኛም ጭምር ስለሆነ ነው በማለት አስረድተዋል::

ፋብሪካው በሳምንት ውስጥ የሚፈትሸው የድንጋይ ከሰል መጠን አንድ መቶ ሺ ቶን ይሁን እንጂ ላቦራቶሪው ግን የሚፈትሸው የድንጋይ ከሰልን ብቻ አይደለም ሲሉም ጠቅሰው፣ የአፈር ምርመራን ማድረግ እንደሚችልም ጠቁመዋል:: ‹‹ላቦራቶሪ ማለት ለዚህ ለድንጋይ ከሰል ፋብሪካው ዋና ጉዳዩ ነው:: እንዲያውም ፋብሪካው የሚመራው በላቦራቶሪው ነው ማለት ይቻላል:: የትኛውን የድንጋይ ከሰል ማስገባት እንዳለበትና የትኛውን ከሰል ማውጣት እንዳለበት ሙሉ ለሙሉ የሚያስተካክለው ላቦራቶሪው ነው ሲሉም ያብራራሉ::

መንግሥት በየዓመቱ የድንጋይ ከሰል ከውጭ አገር ለማስገባት የሚያወጣው ወደ 300 ሚሊዮን ዶላር እንደሆነ በ2014 ዓ.ም ከማድዕን ሚኒስቴር የወጣው መረጃ ያመለክታል:: ይህንንም የድንጋይ ከሰል የሚያስገባው ከተለያዩ አገራት እንደሆነም መረጃው ያመለክታል:: ይህን ከፍተኛ ወጪ ለማስቀረትና ከውጭ የሚገባውን የድንጋይ ከሰል ለማስቀረት የተለያዩ ውሳኔዎች ላይ ተደርሶ ወደ ትግበራ መገባቱ ይታወሳል::

በዳውሮ ዞን እየተገነባ ያለው የድንጋይ ከሰል ማበልጸጊያ ፋብሪካ ግንባታው ተጠናቅቆ ወደ ስራ ሲገባ ለብረት፣ ወረቀት፣ ሲሚንቶ፣ ሴራሚክ እና ሌሎች ፋብሪካዎች ግብዓት የሚሆን የታጠበ የድንጋይ ከሰል ማቅረብ ይችላል::

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ወዲያ ወዲህ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

በሕይወቴ የምቆጭባቸው ሁለት ነገሮች አሉ። የመጀመሪያው በነሶቅራጠስ ዘመን አለመወለዴ ነው። ሁለተኛው ደግሞ በእኔ ዘመን ሶቅራጠስን መሳይ ሰው አለመፈጠሩ ነው። የአሾና የሶቅራጠስ ስለሕይወት እይታ ይማርከኛል። ከእየሱስ ጋር አብረው ሕይወትን የፈጠሩ ይመስል «ሕይወት ማለት እንዲህ ናት»፣ «መኖር ማለት ይሄ ነው» ሲሉ በሰሚ ልቦና ውስጥ ጉጉት ይፈጥራሉ። ግን እንዴት ሕይወት ገብቶኝ ሱሰኛ ሆንኩ? ግን እንዴት ራሴን ማፍቀር አቃተኝ? ያልመላለስኩት ጥያቄዬ ነው።

አሁን አሁን ቁጭቴ ወደ ሦስት ከፍ እያለ መጥቷል። እየሱስ ምድር ላይ ሳለ ብኖር እላለሁ። በከብቶች በረት ሲወለድ፣ ውሃ ቀድቶና እንጨት ለቅሞ እናቱ ማርያምን ሲያገለግል፣ በጭቃ ህያው ወፍ ሲሠራ ባየሁት እላለሁ። ወደ ገሊላ ሲያቀና፣ በዶኪማስ ቤት ውሃውን ወደ ወይን ሲቀይር ብታደም እላለሁ። የቢታኒያ ድንጋዮች ሲያመሰግኑት፣ በበርሀ ውሃ ሲያፈልቅ፣ በደብረታቦር በብርሃን ባየው እመኛለሁ። መካኗን ሳራን ሲያስቅ፣ ፈርኦንን ሲቀጣ፣ ለአብረሃም ቃል ሲገባ፣ ኖህን ከጥፋት ውሃ ሲያድን ጎኑ ብሆን እላለሁ። በጌቴሴማንያ በአትክልቱ ስፍራ፣ በጥብሪያዶስ በባህሩ ዳር፣ በዳናው ጥላ በጌርጌሴኖን አብሬው ቆሜ ቢሆን፣ ጣሊታን ከሞት ሲያስነሳ፣ መቅደላዊት በእንባዋ እግሩን ስታጥብ፣ የሴራብታዋን ሴት ሲያነጋግር ሰምቼ ቢሆን። በአህያ ውርንጭላ ሲጓዝ፣ የማርያም እህት ማርታ መልካም እድልን መርጣ እግሩ ስር ስታርፍ፣ ዘኪዮስ ሊያየው ዛፍ ላይ ሲወጣ፣ ከተከተሉት ከአምስት የገበያ ሕዝብ አንዱን ብሆን። በዕለተ አርብ ዓሣ ካበላቸው አምስት ሺህ እንግዶች አንዱን ሆኜ ብሆን ያምረኛል። እንደዛች ለአስራ ሁለት አመት ደም እንደሚፈስሳት ሴት ቀሚሱን ዳስሼው ቢሆን፣ እንደ ጳርጠሚዮስ የናዝሬቱ እየሱስ ሆይ ብለው፣ እንደ ሀር ሻጪዋ ሊዲያ በድምጹ ልቦናዬ ቢከፈት እስባለሁ።

እያሱ ፀሐይን ሲያቆም፣ ኤሊያስ ዝናብን ሲገስጽ፣ ሙሴ ባህር ሲከፍል፣ ዳዊት ጎልያድን ሲጥል፣ ደሊላ ሳምሶምን ስትረታ፣ ቤርሳቤህ ከኦርዮን ስትሸሽ፣ ሄሮዲያዳ አንገት ስታስቆርጥ፣ አስቴር ሀማስን ስትሰቅል፣ ሜልኮል ስትዘባበት፣ አዚያ ሲቀሰፍ፣ ሩት ስትቃርም፣ ሶስና ከእደረበና ስትድን፣ አፎሚያ ሲከብር፣ እስቂያስ ሲያነባ፣ አጋር ስትሰደድ፣ አናኒያና ሰጺራ ሲዋሹ፣ አክአብ ሲዝት፣ ኤልዛቤል ሲያቅራራ፣ ዮሴፍ ሲሸጥ፣ አዳም ሲያንቀላፋ ሰው ሆኜ ኖሮ ስል እመኛለሁ። ቃየል በወንድሙ ላይ ሲነሳ፣ ሄዋን ሉድ እና ቅሌማን ስትወልድ፣ ታራ ጣኦት ሲያመልክ፣ ስምኦን ዓይኑን በወስፌ ሲያፈስ፣ ፊቮን ወደ ቆረንቶስ ስትላክ፣ ሀናና ፍናና ሲነቋቆሩ ባይና ብሰማ። ጴጥሮስ ሲክድ፣ ይሁዳ ሲያስመስል፣ በርባን ሲፈታ፣ ቬሮኒካ የጌታን ደም ስትጠርግ ሕይወት ኖሮኝ ቢሆን እላለሁ።

ጴጥሮስን ከቀራጭነት፣ ስሞንን ከዓሣ አጥማጅነት፣ ማቲያስን ከውንብድና ወዳጁ እንዳደረገ እኔንም ከሱሰኝኔ አውጥቶ ደቀመዛሙሩ ቢያደርገኝ ስል አይሆኑ እመኛለሁ። በዚህ ዓለም ላይ እየሱስን እንደመከተል ምን ጥበብ አለ? ግን እኮ በራሴ ዘመን ላይም እየሱስን መፍጠር እችላለሁ። ያን ማድረግ ለምን አቃተኝ? ያኔ ብቻ አይደለም እየሱስ ዛሬም ጌታ ነው። ለምን በራሴ ውስጥ እሱን መፍጠር ተሳነኝ? ሰው ከምኞት ወጥቶ ላመል ፈቀቅ እስካላለ ድረስ የትናንት ምርኮኛ ነው። ቅርቡ እየሱስ ርቆኝ በማይሞትበት ዓለም ላይ እየኖርኩ የተወለደበትን ዘመን እናፍቃለሁ። እሱ እኮ ዛሬም አዲስ . . ዛሬም ስለ እኛ ጎለጎታ ነው ብሎ የሚነግረኝ አማኝ አጣሁ። ለነገሩ ቢነግሩኝስ መች ሰምቼ። ክርስትና የተነሳሁበት የአርባ ቀን አጥቢያዬ አጠገቤ አይደል። ቄሱን ሳልሰማቸው መቼ ቀርቼ አውቅና። ያን በስብከቱ ጉድ የተባለለት ሰው ጆሮ ግንዴ ላይ አይደል? መች ከእውነቴ አራቁኝ። መች ከምኞቴ አሸሹኝ። መች ወደ እየሱስ አደረሱኝ። አውቆ የተኛን አሉ . .

መርፌ ሲለግም መች ቅቤ ይወጋና?

እንደልማዴ የማጨሰውን ሲጋራ በመሀል ጣቴ ሰክቼ፣ እንደ እኔ ግራ የገባት የምትመስለውን የከሰዓት ጀምበር ተከትዬ እግሬ ወደ ወሰደኝ ወደ ሆነ ቦታ ተራመድኩ። ሰው ግን ሃሳብ ይጠፋዋል? ድንገት መጥቶ ሃሳብ ይጠፋኛል። ሃሳብ ቢኖረኝ ኖሮ እግሬ እንደመራኝ አልሄድም ነበር። እየሱስን ያልደረስኩበት ያለ ሃሳብ እግሬ እንደመራኝ እየተጓዝኩ ይሆን? አዎ፣ እንደዛ ቢሆን ነው። እንደዚህ ካልሆነ ሌላ ምንም አይሆንም። አንዳንድ ልማዶች የአለመርባት አዲስ አሙቶች ናቸው። ሰው በሃሳብ እግሮቹን ካልመተረ መድረሻው የለውም አልኩ።

ብቻ እግሬን ተከትዬ ራቅ ብዬ ሄድኩ። የሲጋራዬ ዕድሜ አልቆ የመጨረሻ ጭሴን ወደ ሆዴ ስቤ ሌላ አቀጣጠልኩ። እየሱስን በእንደ እኔ ዓይነቱ ወንበዴ ውስጥ ፈልጎ ማግኘት ፓስፊክ ውቅያኖስን በማንኪያ ጨልፎ ማጉደል መስሎ ታየኝ። ማን ነበር ያ በትንሽ ጽድቅ ከማንም ቀድሞ ገነት የገባው? ማን ነበረች ያቺ ስትዘሙት ኖራ በእግዜር ጻድቅ ዓይኖች የታየችው? ገድለ አሪት . . ገድለ ሀዲሴን እንዳላበላሽ በሃሳቤ መሀል እየተሰነቀረ . . አንተ እኮ ማለት እያለ ያመጻድቀኝ ጀመር።

ያለሃሳብ መጓዝ በመኖር ውስጥ ያለ የሰው ልጅ ያልደረሰበት ምቹ የነፃነት ስፍራ መስሎ ታየኝ። ግን አይደለም እንደማሰብ ጉልበታምና ሞገሳም ነፃ ዓለም አላየሁም። ገብቶኝ እንኳን ልወዳጀው አቅም አጣሁ። አለማሰብ አለማወቅ ነው። ዝም ብሎ መኖር . . ዝም ብሎ መሞት። ሕይወትን የምናምርባት በማሰብ ውስጥ ነው። ሞትን የምንንቀው በስልሳሌ ውስጥ ነው።

ባለማሰብ ብዙ ተጉዤ መድረሻዬን አንድ ስፍራ አደረኩ። ሰፊ ግቢ ውስጥ በቅለው የግቢውን ውጪ አውራ ጎዳናውን ባጠሉ ዛፎች ስር። ጥላው ያምራል . . በተደራረቡና በተቃቀፉ ረጃጅም ዛፎች የተሠራ ጥላ ነው። የአስፓልቱ ግማሽ ድረስ ተወርውረው ጥላማ አድርገውታል። የግንቡን አጥር ተደግፋ አንዲት ሴት ቆማለች። አለማሰቤ ሃሳብ ጀመረ። ምንም እንኳን ተጉዤ ባልደርስበትም ከክርስቶስ ምክረ ሃሳብ ማፈንገጥ አልወድም። እንዲህ ስል ጻድቅ ነኝ እያልኩ ሳይሆን ቢሆንለት ለእውነት ቅድሚያ የሚሰጥ ሰው ነበርኩ እያልኩ ነው። ከጎለጎታ በፊትም ሆነ በኋላ የእየሱስ ሕገ ሥርዓት መነሻ ያደረገው ፍቅርን ነው። አቅም ኖሮኝ ብችል እንደ እየሱስ ጠላቶቹን ሁሉ በፍቅር የረታ መሆን እፈልግ ነበር። ግን አልቻልኩም . . የምችለው አንድ ነገር ነው አቅም አጥቼ እንዳልጠላ መሆን።

ፊት ለፊቴ አንዲት ጉብል የቆመችበት ጥላ . . ጥላው አማረኝ። ከፀሐይ ወደ ጥላ ልብ ላይ የሚያርፍ የሆነ መንፈስ አለው . .። ያ መንፈስ አረፈብኝ። ሲጋራዬን እያቦነንኩ ከወጣቷ አጠገብ ሄጄ ቆምኩ። ለትዝብት በሰሉ ዓይኖች ፊት ለፊት ጎዳናውን ትቃኛለች። ሃሳብ ብትዘራብኝ ስል ተደናብሬ ሄጄ ከሃሳቧ ላደናቅፋት ፈለኩ።

ያለውን የሰጠ ንፉግ አይባልም ስል ከሲጋራዬ አንድ ጊዜ ስቤ «እንኪ» ስል ዘረጋሁላት።

እንደዛ ቀን አልተገላመጥኩም። ለምላሹ ብዙ መልካም ነገሮች ነበሯት። እሷ ግን ግልምጫን አስቀድማ እንዳልነበረ አደረገችኝ።

አልተከፋሁም። «ከሌሎች ጋር ለመኖር ብዙ አማራጮች አሉን። እንደ መልካም አንደበት ግን ጥሩ አማራጭ የለንም» ስል ምንም እንዳልመሰለኝ እንድታውቅ በዚያውም እንድትማር ቃል ወረወርኩላት።

«የሰጠኸው እንደሚሰጥህ አታውቅም?»

«የሰጠሁሽ መጥፎ መሆኑን በምን አወቅሽ?»

«የሚረቡ ወንዶች ጣታቸው መሀል እስክሪፕቶ እንጂ ሲጋራ አይዙም» ብላ ወደ ትዝብቷ ተመለሰች።

ኩምሽሽ አልኩ። «እኔ ያለኝን ነው የሰጠሁሽ» ስል ድንጋጤዬን ለመደበቅ ሞከርኩ።

«ያሉን ነገሮች ሁሉ የማይጠቅሙን እንደሆኑ አታውቅም?»

«አልስማማም። ካጣናቸው እና ከሌሉን ነገሮች እንደሚበልጡ ነው የማውቀው።»

«እንደዛም ማሰብ ትችላለህ። ከሁሉም የሚበልጠው መልካም አንደበት ነው» ስትል የሰማሁ መሰለኝ . . ?

«አዎ ሰምተሀል . .! »

«እንግዲያውስ ከሁሉም የሚበልጥ ሌላ ነፃ አውጪ እውቀት እንዳለም ጨምርበት» ብላኝ ትታኝ ሄደች። ከጥላው ወጥታ ፀሐዩዋ ላይ ስትማገድ የሆነ ነገር ቅር ቅር አለኝ። በወጣችበት ቅጽበት ተሲያቷን ትታ ጀምበር እንደ ጌታ የስቅለት ቀን ጨላለመች።

ወደ እየሱስ ታደርሰኝ እንደሁ ስል ተከተልኳት። አስወጣችን እንጂ ከመች ጀምሮ ነው ሴት ወደ ገነት የምታስገባው? አንዱ ልቤ እንዲህ ይለኛል። ቢሆንም መራመዴን አላቆምኩም።

# ዓለም አቀፍ

## የሁቲ አማጽያን ቀይ ባሕርን ሲቀዝፍ የነበረ የአሜሪካ መርከብ መምታታቸውን አስታወቁ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የየመን ሁቲ አማጽያን ቀይ ባሕርን ሲቀዝፍ የነበረ አንድ የዩናይትድ ስቴትስ የንግድ መርከብ መምታታቸውን አስታወቁ።

አማጽያኑ የአሜሪካ ንብረት ነው ያሉት መርከብ መጠሪያው ኬኦኢ እንደሆነ ተሰምቷል።

የባሕር ጥበቃ ኩባንያ የሆነው አምብሬ፤ በየመን የኤደን ጠረፍ አቅራቢያ ፍንዳታ መስማቱን ይፋ ቢያደርግም ስለመርከቧ ምንነት ያለው የለም።

በተያያዘ ዜና ዩናይትድ ስቴትስ በየመን የምታደርሰውን ጥቃት የቀጠለች ሲሆን ሊወነጨፉ የተዘጋጁ 10 ድሮኖችን መደምሰሷ ተሰምቷል።

ሮይተርስ የዜና ወኪል እንደገለጸው ኬኦአይ በላይቤሪያ ባንዲራ የምትንቀሳቀስ፤ መቀመጫውን ዩኬ ባደረገ አንድ ኩባንያ የምትተዳደር መርከብ ናት።

በዚሁ ኩባንያ የምትተዳደረው ማርሊን ሉዋንዳ የተባለች ነዳጅ ተሸካሚ መርከብ ባለፈው ሳምንት ጥቃት እንደደረሰባት ይታወሳል።

የሁቲ አማጽያን የእሥራኤል፣ ዩናይትድ ስቴትስ እና የብሪታኒያ ንብረት የሆኑ መርከቦችን ዒላማ ማድረግ የጀመሩት በእሥራኤል እና ሐማስ መካከል ጦርነት ከተቀሰቀሰ በኋላ ነው።

ይህን ተከትሎ አሜሪካ እና ብሪታኒያ ዓለም አቀፍ ንግድን ለመጠበቅ በሚል የሁቲዎችን ሚሳዔል ማከማቻ መምታት ጀምረዋል።

የሁቲ አማጽያን የወታደራዊው ክንፍ ቃል አቀባይ የሆኑት ያህያ ሳሪያ ረቡዕ ዕለት እንዳሉት ቡድኑ «በርካታ ሚሳዔሎች ተጠቅሞ» የአሜሪካ ወታደራዊ መርከብ ላይ ጥቃት ሰንዝሯል።

አፈ ቀላጤው እንደሚሉት መርከቧ «በቁጥጥር ሥር ወዳለችው ፍልስጤም» እያመራች ነበር። «በቁጥጥር ሥር የምትገኘው ፍልስጤም» የሚለው መጠሪያ እሥራኤል ማለት



እንደሆነ ይነገራል።

ያህያ አክለው የመን «ለአሜሪካና ብሪታኒያን ጥቃት ምላሽ ለመስጠት አታመነታም» ብለዋል።

«ሁሉም የአሜሪካና የብሪታኒያ መርከቦች በቀይ እና በዐረቢያን ባሕር በኩል እስካለፉ ድረስ የየመን ታጣቂ ኃይሎች ዒላማ ናቸው። አሜሪካ እና ብሪታኒያ ሀገራችን ላይ የሚያደርሱት ጥቃት እስካልቆመ ድረስ ይህ ይቀጥላል።»

የአሜሪካ ማዕከላዊ ዕዝ ከየመን ሊወነጨፉ የነበሩት 10 ድሮኖች የአሜሪካ ወታደራዊና የንግድ መርከቦችን ለማጥቃት የተሰናዱ ነበሩ ብሏል።

ዩናይትድ ስቴትስ አክላ በየመን ባሕረ ሰላጤ ሦስት የኢራን ድሮኖችን እና አንድ የሁቲ ፀረ-መርከብ ባለስቲክ ሚሳዔል መትታ መጣሏን ተናግራለች።

የየመን አማጽያን ቀይ ባሕርን ለንግድ መመላለሻ የሚጠቀሙ መርከቦች ላይ እየወሰዱ ባሉት ጥቃት ምክንያት ዓለም አቀፍ ንግድ እየተጓተተ ሲሆን የአቅርቦት ችግር ሊያስከትል ይችላል የሚል ስጋት አለ።

ባለፈው ጥቅምት በእሥራኤል እና በፍልስጤሙ ሐማስ መካከል የተነሳው ግጭት በመካከለኛው ምሥራቅ እየተስፋፋ እንደሆነ ተንታኞች ይናገራሉ ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

## የቻይና መንግሥት የመረጃ ሰርሳሪዎች በአሜሪካ መሠረተ ልማት ላይ ማነጣጠራቸው ተነገረ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በቻይና መንግሥት የሚደገፍ የመረጃ መረብ ሰርሳሪ ቡድን እንደ ኃይል እና የውሃ መስመር ያሉ ቁልፍ የሕዝብ መሠረተ ልማቶች ላይ ያነጣጠረውን የጠለፋ ሙከራውን ማክሸፍ መቻሉን ኤፍቢአይ ተናግሯል።

የኤፍቢአይ ዳይሬክተር «ቮልት ታይፎን» የተሰኘውን ቡድን ለመዝጋት ዘመቻ መካሄዱን ለሕግ አውጭዎች ተናግረዋል።

ቡድኑ የአሜሪካ ንብረቶችን መረጃ ለማግኘት በመቶዎች የሚቆጠሩ የቆዩ የቢሮ ራውተሮችን ሰርጎ ገብቷል ሲሉ ክሪስቶፈር ራይ ተናግሯል። የቻይና መንግሥት ስለቀረበበት ክስ እስካሁን ምላሽ አልሰጠም።

ቻይና ቀደም ሲል በመንግሥት የሚደገፍ የሳይበር ስለላ በሌሎች ሀገራት ላይ ታካሂዳለች መባሉን ውድቅ አድርጋዋለች። ከዚህ ባለፈም ዩናይትድ ስቴትስን «የዓለም ትልቋ የመረጃ ጠላፊ ሀገር እና የዓለም አቀፍ የሳይበር ቀማኛ» ስትል ከሳታለች።

ራይ ረቡዕ ዕለት ለአሜሪካ ኮንግረስ ኮሚቴ እንደተናገሩት ቻይና ሆን ብላ ግጭት በሚፈጠርበት ወቅት የአሜሪካን ቁልፍ የመሠረተ ልማት ሥርዓቶችን ለማሽመድመድ ከወዲሁ መሠረት እየጣለች ነው።

«የቮልት ታይፉን» የጠለፋ ጥረት ለመጀመሪያ ጊዜ ይፋ የሆነው ባለፈው ግንቦት ወር በዩኤስ ውስጥ ሲሆን ቡድኑ የመንግሥት ኢሜል አካውንቶችን ሰብሮ መግባትን ጨምሮ በርካታ የሕዝብ መሠረተ ልማቶችን ኢላማ አድርጓል ሲል ማይክሮ ሶፍት አስጠንቅቆ ነበር።

ኤፍቢአይ ቡድኑ ያነጣጠረው እንደ የውሃ ማጣሪያ፣ የኃይል ማሰራጫ፣ የትራንስፖርት ሥርዓቶች፣ ነዳጅ እና ጋዝ ማስተላለፊያ እና ቴሌኮሙኒኬሽን አውታሮችን የመሳሰሉ የሀገሪቱን ወሳኝ መሠረተ ልማቶች ላይ ነው።

ራይ አክለውም በቻይና መንግሥት የሚደገፈው ቡድን ማልዌር (በመረጃ ሰርሳሪዎች የሚዘጋጅ መረጃ ለመሰብሰብ ጥቅም ላይ የሚውል ሶፍት ዌር) በመጫን እና ከመሠረተ ልማቶች ጋር የተገናኙ በመቶዎች የሚቆጠሩ አሮጌ እና ጊዜ ያለፈባቸው ራውተሮች ተቆጣጥሯል።

«የቮልት ታይፉን ማልዌር ቻይና በሌሎች ሀገሮች አሰሳ እና ወሳኝ በሆኑ መሠረተ ልማቶች ላይ የምትፈጽመውን የኔትወርክ ምዝበራ እንድትደብቅ አስችሏታል» ሲሉ በአሜሪካ-ቻይና ውድድር ዙሪያ ለኮንግረሱ ኮሚቴ ተናግረዋል።

ይህም መረጃ ሰርሳሪዎቹ «አደጋ ለመፍጠር እና በአሜሪካ ዜጎች ላይ ጉዳት ለማድረስ እየተዘጋጁ መሆናቸውን ያሳያል» ብሏል።

«ቻይናጊዜ እንደደረሰ ከወሰነች በፖለቲካዊ ወይም በወታደራዊ ኢላማዎች ላይ ብቻ አታተኩርም» ሲሉም አክለዋል።

የዩናይትድ ስቴትስ የሳይበር ደህንነት ባለሙያዎች ቻይና ግጭት ከተፈጠረ በሚል የግንኙነት መቆራረጥ ሊፈጠር የሚችል አቅም ለመገንባት መሠረተ ልማቶች ላይ ማነጣጠሯን ቀደም ሲሉ አስጠንቅቀዋል።

በዩኤስ እና በቻይና መካከል የሚካሄደውን ውድድር የሚመለከተው ኮሚቴ ረቡዕ ዕለት ባካሄደው ስብሰባ ላይ ሊቀመንበሩ ይህ «በአሜሪካ ድልድዮች እና የኃይል ማመንጫዎች ላይ ቦምቦችን ከማስቀመጥ ጋር የሚመጣጠን የሳይበር ጥቃት» ነው ብለዋል።

የሳይበር ጥቃት ውንጀላውን በሙሉ ውድቅ በማድረግ ቤጂንግ ኮሚቴውን ወቅሳለች። የቻይና መንግሥት ኮሚቴው «አድሎአዊ የሆነውን ርዕዮተ ዓለም እና የቀዝቃዛ ጦርነት አስተሳሰብን እንዲያስወግድ» ጠይቋል።

ለሳይበር ጥቃት የተዘጋጁ የቤጂንግ ሀብቶችን በዝርዝር የገለጹት ራይ፤ የቻይና መረጃ ምዝበራ ፕሮግራም «ከሌሎች ዋና ዋና ሀገራት ሁሉ የበለጠ» ነው ብለዋል።

የኤፍቢአይ የሳይበር ባልደረቦች በቻይና አቻዎቻቸው 50 ለ 1 የሆነ ብልጫ እንደተወሰደባቸውም አክለው ተናግረዋል። ዘገባው የቢቢሲ ነው።

# የሽልማቱ ፋይዳ የላቀ ነው

ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሽከታብ)

ከሰሞኑ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስተር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በምግብ ዋስትናና በተመጣጠነ የምግብ አቅርቦት ላሳዩት ቁርጠኝነትና የላቀ አመራርነት የተባበሩት መንግስታት የምግብና የእርሻ ድርጅት ‹ፋኦ› የአግሪኮላ ሽልማትን አበርክቶላቸዋል፡፡ በአይነቱ ለየት ያለው ይሄ ሽልማት በምግብ ራስን ለመቻል በሚደረግ ሂደት ውስጥ የመንግስትን ቁርጠኝነት ከሕዝባዊ ተሳትፎ ጋር መሳ ለመሳ አቁሞ አሁናዊና ዘላቂ የምግብ ዋስትናን ጥያቄ ውስጥ በማስገባት እንደመስፈርት የሚያስቀምጥ ነው፡፡

ሀገራችን ከመቼውም ጊዜ በላይ በኢኮኖሚ ራስን የመቻል ጥረት ውስጥ ናት፡፡ ጥረቱ ፍሬ እንዲያፈራ በመንግስት በኩል ሁሉንም አይነት እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል፡፡ ይሄን እውነታ ከሚመሰክሩ ሁነቶች ውስጥ የመጀመሪያው በግብርናው ዘርፍ በተለይም በበጋ ስንዴ ምርት ላይ እያሳየነው ያለው ለውጥ አንዱ ነው፡፡ ላለፉት ሶስትና አራት ዓመታት ውስጥ በአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ያሳየነውና ያመጣነው ሕዝባዊ ለውጥ ራስን በምግብ ለመቻል በምናደርገው እንቅስቃሴ ላይ አወንታዊ ጥላውን አጥልቶ አንድ ርምጃ አንፏቆናል፡፡

ያለማመንታት ያለፉት አምስት ዓመታት በግብርናው ዘርፍ ምርጦቻችን ነበሩ ማለት ይቻላል። በተለይ በአንክሮ እንዲሰራባቸው ይፋ በተደረጉት ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች፣ አምራች ኢንዱስትሪ፣ ቱሪዝም፣ ማዕድንና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂዎች ላይ ሰፋ ያለ ስራ በመሰራቱ የአሁኑን ሽልማት ጨምሮ ሌሎች በርካታ ለውጦችን እያስተናገድን እንገኛለን፡፡ ከዚህ የአምስት ዓመት ለውጥ ጋር ሊነሳ የሚችለው በግብርናው ዘርፍ የተሰሩ ተጨባጭ ስራዎች ናቸው፡፡

ቀደም ሲል ጾም ይውሉ የነበሩ፣ ካለጥቅም የተቀመጡ፣ በዳዋና በአረም የተዋጡ መሬቶች በማሻሻያ ትግበራው ምርት እንዲሰጡ የተደረገበት ሁኔታ የዚህ ተሀድሶ አንድ አካል ሆኖ የሚነሳ ነው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ድርቅን የሚቋቋሙና የውሀ ፍጆታቸው ቁጥብ የሆኑ ሰብሎችን የማምረት ስራው አበረታች ከመሆኑም በላይ በቀጣይነት በተስፋ ሰጪነቱ የሚነሳ ነው፡፡

በልዩ አትኩሮት እየተሰራባቸው ያሉ የስንዴ፣ የጤፍ፣ የበቆሎና የገብስ ምርቶች ገበያውን ከማረጋጋትና የውጪ ተረጂነትን ከማስቀረት አኳያ ሚናቸው የላቀ ነው፡፡ እኚህ የምርት ውጤቶች እንደውሀና ለም መሬት ያሉ የተፈጥሮ ሀብቶች በመጠቀም ያከናወናቸው ናቸው። በቀጣይም በተሻለ ቴክኖሎጂና በተማረ የሰው ኃይል ታግዘው የተሻለ ምርት እንዲሰጡ እየተደገ እንደሆነ በተለያዩ መግለጫዎች ላይ የሰማነው እውነታ ነው፡፡

ሌላው የዚህ ማሻሻያ አንድ አካል የሆኑት የወተት፣ የስጋ፣ የዶሮ፣ የአሳና የማር ምርቶች ናቸው፡፡ ከራስ ፍላጎት በላቀ ሁኔታ በኢኮኖሚ ግንባታ ላይ የራሳቸውን አስተዋጽኦ በማድረግ ጠጠር በማዋጣት ላይ ይገኛሉ፡፡ መጪውን ጊዜ በበጎ እንድንማትር የሚያደርጉ እንደሌማት ትሩፋት አይነት ወጪ ቀናሽ ስትራቴጂዎች ከጀመርነው ራስን በምግብ የመቻል ንቅናቄ ጋር አብረው ትግላችንን ፍሬአማ አድርገውታል፡፡

እኚህ ሁሉ እውነታዎች በአንድና ሁለት ቃል ቢገለጹ ‹የላቀ አመራርነት ከሕዝባዊ ተሳትፎ እና ቁርጠኝነት ጋር› የሚሉ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ለዓለም አቀፍ ሽልማትም አጭተውናል፡፡ በጥቂት ዓመታት ውስጥ በዚህ ደረጃ ራስን መቀየር በእውቀትና በቁርጠኝነት የታገዘ አመራርነት ካልሆነ ሌላ ምንም ሊሆን አይችልም፡፡

> **እርቅና ተግባቦትን ከፊት አስቀድመን ልዩነቶቻችንን አጥበን የጀመርነውን ልማት ማስቀጠል ቀዳማይ ጉዳያችን ነው**

ድህ ነን ብለን ስናወራ ዘመናት ተቆጥረዋል። በተረጂነትና በልመና ብዙ ዓመታትን ተሻግረናል። ዋናውና ሀገርን ሊቀይር የሚችለው በቁርጠኝነት የታገዘ ሁሉን አቀፍ ልማታዊ እንቅስቃሴ ነው። ስራ ጠልነትን ውድቅ ያደረገ በራስ እውቀት፣ በራስ ልጆች፣ በራስ የተፈጥሮ ጸጋ ራስን ከድህነትና ከተረጂነት ነጻ ማውጣት ማለት ይሄ ነው፡፡

የሕዝብ ቁጥር እና ፍላጎት ያልተጣጣመባት ሀገር ከአርምሞ ለመውጣት ጥበብ የታከለበት የአመራርነት ብቃት የማስፈለጉን ያክል ምንም አያስፈልጋትም፡፡ ድህ ነን ብሎ ከማውራት ይልቅ ከድህነት የሚወጡበትን መላ መፈለግ፣ አልችልምና አይሳካልኝም ብሎ እጅን አጣጥፎ ከመቀመጥ ሁሉንም ነገር መሞከር፣ በአንድነትና በሕብረት ለጋራ ክብር መረባረብ አንዱና ማንም እንዳይደርስበት የተደበቀ ሀገርን ከድህነት መታደጊያ መንገድ ነው፡፡ እኛም በመንግስታችን መሪነት በዚህ በኩል አልፈን ነው ራሳችንን ነጻ ከማውጣት እኩል ሽልማት እያገኘንባቸው ነው።

ያለፉት ጊዜ የሕዝብ ቁጥራችን ከፍላጎታችን ጋር ያልተጣጣመበት፣ የኤክስ ፖርት ምርታችን ወደሀገር ውስጥ ከምናስገባው ጋር አቻ የሌለው እንደነበር ይታወቃል፡፡ ከአፍሪካ የውሀ ገንቦነት በስተቀር የጣመ ስም ሳናተርፍ፣ ብዙ ለም መሬቶችን ከእልፍ የተፈጥሮ ጸጋዎች ጋር ይዘን፣ በሰው ኃይልና በወጣት ቁጥር ከፊት ቆመን ምንም አልሰራንም ነበር፡፡ እኚህ ሂደቶች ቀስ በቀስ ኢኮኖሚውን እንደሚያሳሱት የታመነ ነው።

ለእንደዚህ አይነቱ ችግር መፍትሄ ሆኖ ከፊት የሚመጣው ደግሞ የሀገር ውስጥ ምርትን ማሳደግ እና ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን መቀነስ በዋናነት ደግሞ በግብርናው ዘርፍ ላይ የማሻሻያ ርምጃዎችን መውሰድ ነው፡፡ በዚህ በኩል የተሳካ ለውጥን አስመዝግበናል፡፡ በተሻሻለው የግብርና አቅጣጫ ስንዴን ከውጪ ማስገባጥ አቁመን፤ የውጪ ገበያን ለመቀላቀል እያሟሟቅን ነው፡፡

በበጋ መስኖና በመኸር የአዝመራ ወቅት ሰፊ መሬቶች በስንዴ ተሸፍነው ያየንበት ጊዜ ሁሉ ሞልቶን ባለመቻል እጃችንን አጣጥፈን ለተቀመጥነው ለእኛ እንደብርቅ የሚነሳ ነው። ይሄ የሆነው እንግዲህ አምስት ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ ካለፈው ይልቅ የአሁኑ..ከአሁን ደግሞ መጪው ጊዜ የበረታ ተስፋን የሚሰጠን ነው፡፡

በእርዳታ ስንዴ የምትታወቅ ሀገር፣ የምታስገባው በዝቶ የኢኮኖሚ መዋዠቅ የተፈጠረባት ሀገር በአጭር ጊዜ ውስጥ በበረታ አመራርነት፣ ከመቀበል ወደመስጠት መሸጋገሯ እውን የማይመስል ግን ደግሞ እውን የሆነ ነገር ነው፡፡ እነዚህ ሂደቶች ናቸው በዓለም አቀፉ መድረክ ፊት በጠቅላይ ሚኒስትራችን በኩል ሀገራችን እንድትሸለም ያደረጓት፡፡

ሽልማቱ ሀገር የምትነሳበት፣ ሕዝብ የሚከበርበት ከሁሉ በላይ ደግሞ የድህነት ታሪካችን ቀለሙ የሚደበዝዝበት መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም፡፡ አንድ ሀገር ወይም አንድ ድርጅት ሽልማት ሲሰጥ በብዙ ግምገማ ውስጥ አልፎ ነው፡፡ የአሁኑ የጠቅላይ ሚኒስትራችን ሽልማት የአምስት ዓመት የአመራርነት ጥበብ፣ የዓመታት የሕዝብ እንቅስቃሴ፣ የብዙ ጊዜ ቅንጅትና ውህደት ውጤት ነው፡፡ ከዚህ ጋር አብሮ የሚነሳው ድህነትን ለማሸነፍና ተረጂነትን ለማስቀረት ምን ያክል ጠንክረን እየሰራን እንደሆነ ነው፡፡

ሽልማት የጠንካራ አእምሮና ልብ ውጤት ነው፡፡ ሰርተን በማሳየታችንና ተጨባጭ ለውጦችን በማምጣታችን እንሆ በዓለም አደባባይ ውጤቱን ተመልክተናል፡፡ በሽልማቱ ወቅት ንግግር ያደረጉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ራስን በምግብ ለመቻል እንዲሁም ለተመጣጠነ ምግብ ተደራሽነት ለሰራነው እና እየሰራነው ላለው ስራ እውቅና በመቸሩ ደስታ እንደተሰማቸው ከምስጋና ጋር ገልጸዋል፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ርሀብን ሙሉ በሙሉ ከማጥፋት ባለፈ የምግብ ተደራሽነትን በማረጋገጥ ሀገራዊ ብልጽግናን እውን ለማድረግ ጠንክሮ እየሰራ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ የተሰሩትን ወደፊትም የሚሰሩትን ከቁርጠኛ አመራርነትና ሕዝባዊ ተሳትፎ ጋር አዋህደው የተናገሩት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ፤ ለዚህ ለውጥ የበቃነው ያሉንን ተፈጥሮአዊ ጸጋዎች በአግባቡ በመጠቀም፣ ከጠንካራ አመራርነት ጋር ሙያዊ ማሻሻያዎችን በማድረግ ነው ብለዋል። በሽልማቱ ወቅት አጽንኦት ከተሰጠባቸው ንግግሮች መካከል በቀጣይ የላቀና የበረታ ስራ እንደሚሰራ ነው፡፡

ለዚህ ሽልማት መብቃት እንደሀገር ክብሩ ላቅ ያለ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ነው የተሸለመችው፡፡ ሕዝቡ ነው አክሊል የደፋው፡፡ በአንድ መሪ በኩል ሀገርና ሕዝብ ነው የሚነሱት፡፡ በአንድ በጎ ስራ በኩል ታሪክና ትውልድ ናቸው የሚንጸባረቁት ስለሆነም ሽልማቱ ትላንትን በመዘከር ዛሬን በማውሳት ለነገ ኃይል የሚሆን መሆኑ እሙን ነው፡፡ በጀመርነው መንገድ ለመቀጠላችን ዋስትና ከመሆን እኩል አደራ የሚሆንም ነው፡፡

በቁርጠኛ አመራርነት እና በሕዝባዊ ተሳትፎ በዓለም አቀፍ መድረኮች ፊት ስማችን ሲነሳ ይሄ ለብዙኛ ጊዜ ነው፡፡ የሰሞኑ የፋኦ ሽልማት ለየት የሚያደርገው በብዙ ተግዳሮትና ውጣ ውረድ ውስጥ ሆነን አመርቂ ድል መቀዳጀታችን ነው። የትንሳኤዎቻችን ምልክቶች በኢትዮጵያ ሰማይ ላይ ሲፈነጥቁ ማየት ከጀመርን ሰነባብተናል። በኢኮኖሚው፣ በዲፕሎማሲው ከቀጠናው ትስስር እስከ ዓለም አቀፍ ውህደት ድረስ ስማችንን የበረታበት ጊዜ ላይ ነን፡፡

ወደትላንት መለስ ስንል ደግሞ ስለሰላም ያገኘነውን ታላቅ ክብር እናገኛለን፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከዓመታት በፊት ስለሰላም በሰሩት ታላቅ ስራ ዓለም አቀፉን የሰላም የኖቤል ሽልማት በመውሰድ ለሰላም ያለንን ቁርጠኝነት ያሳየንበትን አጋጣሚ አንዱ ነው። ከትላንት እስከዛሬ ባለን የተግባቦትና የውይይት መርህ በእርቅና በይቅርታ እንዴት አብሮ መኖር እንደሚቻል ለዓለም ያሳየንበት ከክብራችን ትልቁን ነው፡፡

ስለሰላም በከፈልነው ዋጋ የሰላም ሀገር እና የሰላም ሕዝቦች ተብለን ኒሻን አጥልቀናል፡፡ ያ አጋጣሚ ከየትኛውም ሁነት በላይ የሀገርን ገጽታ በበጎ የሚያነሳ ነው፡፡ ስለኢትዮጵያ የተዘመረበት፣ የተዘፈነበት፣ የተነገረበት፣ የተወራበት ጊዜ ነው፡፡ ታሪክ ራሱን ተክቶ አሁን ደግሞ በሌላ ዓለም አቀፍ ሽልማት መጥተናል፡፡ ይሄኛውም እንደዛኛው ሁሉ በበጎ የምንነሳበት፣ እጆቻችን ለስራ፣ ሀሳቦቻችን ለተግባቦት የተዋሃዱበት በሀገር ገጽ ግንባታ ላይ ሰፊ ድርሻ ያለው ነው፡፡

ስለሰላም በእርቅና በተግባቦት ከወንድሞቻችን ጋር ታርቀን፣ ከጎረቤቶቻችን ጋር ተቃቅፈን አንድነትን የፈጠርንበት ያ ጊዜ የታሪካችን ደማቁ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ በልማቱም ሆነ በሰላሙ ጉዳይ አሁንም የሚቀሩን የቤት ስራዎች አሉ፡፡ እርቅና ተግባቦትን ከፊት አስቀድመን ልዩነቶቻችንን አጥበን የጀመርነውን ልማት ማስቀጠል ቀዳማይ ጉዳያችን ነው፡፡

ሰላምና ልማት ከየትኛውም ምድራዊ ኃይሎች በላይ እንዳይለያዩ ሆነው የተጣበቁ ናቸው፡፡ በአንድ ወቅት አሁን ላይ ርእሱን ባላስታወስኩት መጣፍ ውስጥ ‹ዓለም ከሰላም ውጪ ሁሉን አጥታ መኖር ትችላለች› የሚል አንብቤያለሁ። ይሄ ማለት ሰላም በምድር ላይ በምንም የማንደራደርበት ጉዳያችን እንደሆነ ነው፡፡

እንደ እድል ሆኖ በዓለም አደባባይ ፊት የተሸለምነው በሰላም እና በልማት ነው፡፡ በትንሽ ሰላም ውስጥ ለሽልማት የታጨንበትን ይሄን ያክል ብርቱ ስራ ከሰራን በእርቅና በይቅርታ፣ በውይይትና በተግባቦት ብንጸና ደግሞ ከዚህም በላይ መስራት እንደምንችል የሚያመላክት ነው፡፡

በዓለም አቀፉ መድረክ ፊት ስለሰላምም ሆነ ስለልማት ሽልማት ለመቀበል ራሱን የቻለ አስፈላጊ መስፈርት ያለው ነው፡፡ ከነዚህ ዘርፈ ብዙ መነሻዎች ውስጥ ቀጠናዊና አፍሪካዊ ፈቀቅ ሲልም ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያለው አስተዋጽኦ መኖር አለበት። የሰላም ኖቤል ሽልማት ስናገኝ እኚህ መስፈርቶች ታይተው ነው፡፡

በምግብ አቅርቦትና በተመጣጠነ ምግብ ዋስትና ተጨባጭ ለውጥ ማምጣታችንን ስናስመሰክር በእኚህ መስፈርቶች ተፈትሸን ነው፡፡ በቁርጠኝነት አሸንፈናል ወደፊትም ልናሸንፋቸው የሚገቡ በርካታ ተግዳሮቶች አሉብን፡፡ ሰላምን ለልማት..ልማትን ለሰላም በሚል መሪ ሀሳብ ተነቃንቀን አዲስ ታሪክ እንደምንጽፍ ባለሙሉ ተስፋ ነኝ፡፡ ላንቆም ላንዝል ከሽልማትና ከለውጦቻችን ጋር ወደፊት እንላለን ! ፡፡

# ወቅታዊ

# “ባለፉት ስድስት ወራት 15ሺህ 557 ሰዎች ኤችአይቪ/ኤድስ በደማቸው ውስጥ ተገኝቷል”

**- ዶክተር ደረጀ ዱጉማ**

**የጤና ሚኒስትር ዴኤታ**

**የ**ኢፌዴሪ ጤና ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ደረጀ ድጉማ በሀገራዊ የጤና ጉዳዮች ዙሪያ ትናንት ለጋዜጠኞች የሰጡትን ቃለ ምልልስ ሙሉ ቃል እንደሚከተለው ይዘን ቀርበናል ።


ፎቶ ሀዲስ አብርሀ

እየሩስ ተስፋዬ

**ጥያቄ፡- የሚኒስትር መሥሪያ ቤቱ የስድስት ወር የእቅድ አፈጻጸም? እንደ መነሻ የሦስት ወሩ አፈጻጸም ምን ይመስላል ?**

**ዶክተር ደረጀ፡-**የስድስት ወር ዕቅዳችንን በተመለከተ ባለፉት ስድስት ወራት የነበረውን አፈፃፀም እንደመነሻ እንዲታይ የተወሰኑ ጉዳዮችን ለመጥቀስ እፈልጋለሁ። አንደኛው፣ የጤናው ሴክተር መከላከልን መሠረት ያደረገና ለአቅመ ማዳን ትኩረት የሚሰጠውን ፖሊሲያችን መሠረት አድርጎ በየአምስት ዓመቱ የትራንስፎርሜሽን እቅድ ያዘጋጃል። በሱም ላይ መስማማትን በሁሉም ደረጃ፣ እስከ ጤና ኬላ ከፈጠርን በኋላ፤ ወደ አፈጻጸም እንገባለን። በዚህ ሂደት አሁን ላይ ሁለተኛ የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አራተኛ ዓመት ላይ ደርሰናል።

የስድስት ወሩ አፈጻጸም ከዚሁ የተቀዳ ነው። ያ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ በጤና ሴክተር ባላት ተሰሚነት የተለያዩ ስምምነቶችን እየፈረመች፤ ስምምነቶቹ ወደ ሥራ እንዲገቡ ተነሳሽነትን ወስዳ ስትሠራ ቆይታለች። ወደ ሥራ የምንገባው በርካታ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን፤ የፈረምናቸውን እና ቃል የገባናቸውንም ታሳቢ አድርገን ነው። ከነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ አንደኛው፤ የኤስዲጂ፣ ወይንም የዘላቂ ልማት ግቦችን በ2030 (በፈረንጆቹ) ለማሳካት የተቀመጡ አንኳር ጉዳዮች አሉ። እሱን እንደመነሻ ወስደን እንሠራለን። በመንግሥት ደረጃ ደግሞ የአስር ዓመት ዕቅድ አለ። እንደ ሴክተራችን ከዚያም የምንወስዳቸው አሉ።

ጤና ለሁሉ መሠረት ነው፤ ጤና ለብልጽግናችን መሠረት ነው። በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚሠሩ ሥራዎች ከሚመዘኑበት አንዱ ጤና ላይ ባመጡት ለውጥ ስለሆነ ከሌሎች ሴክተሮችም ጋር በጋራ እንሠራለን። ጤና ለሁሉም ይዳረስ ዘንድ “ሄልዝ ፎር ኦል" የሚል ትልቅ መርሕ አለን። በእያንዳንዱ ሴክተር ውስጥ ጤና እንዴት ነው የሚታየው የሚለውን መሠረት አድርገን፤ ዘርፈ ብዙ ምላሽ የሚሹ ጉዳዮች፣ ለምሳሌ ሥርዓተ ምግብ፤ ኤችአይቪ/ኤድስ ሊሆን ይችላል፤ ሌሎችም ላይ አብረን እንሠራለን።

ይሄን የሠራንበት ሕጋዊ ዓውድ በብዙ ተግዳሮቶች የተሞላ ነው። በተለይ በሰው ሠራሽና ከተፈጥሮ ጋር በተያያዘ በብዙ አካባቢዎች ላይ የድርቅ ችግር አለ፤ ይህ ደግሞ በጤና ላይ ብዙ አሉታዊ ጫና ያመጣል፤ ያም ብቻ ሳይሆን አለመረጋጋትና የፀጥታ ችግር ባለበት ቦታ ላይ ለመሥራትም በራሱ አዳጋች ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃም የሚታወቅ ኮቪዱና ሌሎች አደጋዎችም አሉ። ከውጭ ግብዓቶችን በጊዜ ለማምጣት የምንቸገርበትን ሁኔታ ነበር ። የጤና ባለሙያውም ተንቀሳቅሶ መሥራት ላይ ክፍተት አለ። የውጭ ድጋፎች መቀነስ አልፎ አልፎ በሴክተራችን ይታያል። እነዚህን ሁሉ ታሳቢ አድርገን የሠራናቸው ሥራዎች አበረታች ናቸው ማለት ይቻላል።

በእናቶችና በሕጻናት ጤና ላይ ሊሆን ይችላል፤ በወሊድ መቆጣጠር ላይ ሊሆን ይችላል፤ አቅርቦቶችን ከማሻሻል አኳያ የተለያዩ ግንባታዎች በጤናው ሴክተር ውስጥ የሚሠሩ ሥራዎች አሉ። እነዚህ አንኳር አንኳር ጉዳዮቻችን ናቸው። የጤና ሥራን መቆጣጠርም እንዲሁ፤ ከነበሩ ብዙ ተግዳሮቶች ጋር ስናነጻጽር ያለው የሥራ አፈጻጸም በቀጣይ የተሻለ ሥራ መሥራት እንደምንችል አመላካች ነው።

የኢትዮጵያ መንግሥት በጤናው ዘርፍ ትልቅ ትኩረት ከሚሰጣቸው አንዱና ዋነኛው የእናቶችና የሕጻናት ጤና ነው። እናቶችና ሕጻናት የማኅበረሰባችን ምሰሶዎች ናቸው። በተለይ እናት ቤተሰብን ትወክላለች። ሀገርን ትወክላለች። ስለዚህ ፖሊሲያችን እናቶችና ሕጻናት ላይ ትልቅ ትኩረት ያደርጋል። ካሉን ኢንቨስትመንቶች አብዛኛው በእነዚህ የማኅበረሰባችን ክፍሎች ላይ ትኩረት ያደርጋል። አጋር ድርጅቶቻችን ደግሞ በብዛት ያላቸው ድጋፍ እናቶችና ሕጻናት ላይ ነው።

ማኅበረሰባችን ለእናቶችና ሕጻናት ትልቅ ቦታ ነው የሚሰጠው። ከዚህ ጋር ተያይዞ ባለፉት ስድስት ወራት በርካታ ሥራዎችን ሠርተናል። ለዚህ አንዱ ማሳያ የቤተሰብ ዕቅድን ማስፋት ነው። የቤተሰብ አገልግሎት የእናቶችን ሞት በ40 ፐርሰንት የሚቀንስ፤ የጤና መሻሻል ብቻም ሳይሆን በአጠቃላይ ለማኅበረሰባችን ፈጣን የሆነው የኢኮኖሚም ለውጥ ለማምጣት፤ አምራችና ከፈጠራ አኳያ አቅም ያለው ማኅበረሰብ ለመፍጠር፤ በተለይ ደግሞ በአግባቡ፣ በሥርዓተ ምግብም፣ በትምህርትም ተኮትኩቶ የሚያድግ፣ አነስ ያለ፣ እንዲሁም የበለጸገ ቤተሰብ ለመፍጠር፤ የቤተሰብ እቅድ እጅግ ጠቃሚ እንደሆነ ይታወቃል። በዚህ ስድስት ወር እቅዳችን 80 ፐርሰንት በወሊድ እድሜ ውስጥ ያሉትን እናቶች በቤተሰብ እቅድ አገልግሎት እናዳርሳለን ብለን አቅደን 72 ፐርሰንት ላይ ደርሰናል።

ይህም ከባለፉት ዓመታት ጋር ሲነፃፀር እየተሻሻለ መጥቷል። ራቅ ያሉ እና የፀጥታ ችግር ያለባቸው ቦታዎች ላይ ቀነስ ያለበት ሁኔታ አለ። ከክልል ክልል ልዩነት አለው። በዚህ ደረጃ ግን መሻሻል እየታየ መሆኑን ማንሳት እፈልጋለሁ። ከዚህ ጋር ተያይዞ ሁለተኛው በጤና ተቋም የሚወልዱ እናቶች ጉዳይ ነው። ባለፉት ዓመታት የተወሰነ መቀንስን ቢያሳይም፤ በተለይ በዚህ 6 ወር መሻሻልን አሳይቷል። 63 ፐርሰንት እናቶቻችን በዚህ ሰዓት በጤና ተቋም እየወለዱ ነው። ሌሎቹም በቤት ውስጥ ናቸው ማለት አይቻልም። በተለይ ተፈናቃይ ዜጎቻችን እዚያ ጊዜያዊ አገልግሎት የሚያገኙበት አሠራር አለ ። በጤና ኤክስቴንሽን በኩል የጤና ባለሙያዎችን ድጋፍ ያገኛል ።

በተለይ ከሕጻናት ጋር ተያይዞ በሀገራችን ከ14 በላይ የክትባት አይነቶችን እየሰጠን እንገኛለን፤ ኢትዮጵያ በዓለም መድረክም በዚህ ላይ ዕውቅና አላት። ከዚህ ዋናው ፀረ አምስት የሚባለው ክትባት ነው። 100 ፐርሰንት እናደርሳለን ብለን በአሁን ላይ 95 ፐርሰንት ላይ ማድረስ ችለናል። አንዳንድ ቦታዎች ላይ ወደ ኋላ መቅረት አለ። እሱን በቀጣይ የምንሠራው ይሆናል። በአጠቃላይ 14 አይነት ክትባት የሚወስዱትን 98 ፐርሰንት ለማድረስ ታቅዶ 88 ፐርሰንት ላይ ደርሰናል ። አንዳንድ ራቅ ያሉ አካባቢዎች ጨምሮ ከተሞችም ውስጥ የተወሰነ የሸፋን ክፍተቶች አሉ። “ዜሮ ዶዝ ” የሚባለውን ክትባት ያላገኙ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ሕጻናት አሉ። እነርሱ ጋ ለመድረስ በርካታ ሥራዎችን እየሠራን እንገኛለን። በቅርብ የሚጀመር ሀገር አቀፍ ትልቅ ዘመቻ አለ፤ በተለይ የተወሰነ ዶዝ ብቻ ያገኙ ሕጻናትን የምንደርስበትን (የሚያገኙበትን) ዝግጅት እያደረግን እንገኛለን።

እናቶችና ሕጻናት ላይ በአጠቃላይ፣ በተለይም የምግብ መጠናቸው ዝቅ ያሉትን በመለየት ሕክምና መስጠት ላይ እየሠራን እንገኛለን። ሥርዓተ ምግብ ላይም እንደዛው፤ እንደሚታወቀው “ሰቆጣ ቃልኪዳን” የሚባል ባለፉት ሰባት ዓመታት ጀምሮ በሀገራችን የሚተገበር ትልቅ የምግብ ፕሮግራም አለ። በዓለም አቀፍ ደረጃም ትልቅ ዕውቅና አግኝቷል፤ በ200 አባወራዎች ላይ የሚያበረታታ ውጤት አግኝተናል። በዚህ 6 ወር ይሄንን ወደ 700 ወረዳዎች እያሰፋን እንገኛለን። ጥሩ ጅምር ነው።

ይሄን ቃልኪዳን ሰቆጣ ላይ በሥራ ላይ በማዋላችን የመቀንጨር ምጣኔ ቀንሷል፤ ከ10 ዓመት በፊት ከ55 ፐርሰንት በላይ ነበር። በዚህ ሰዓት ግን 39 ፐርሰንት ሆኗል። በአንድ ዓመት ብቻ ከ99ሺህ 80 በላይ ሕጻናትን ከመቀንጨር መታደግ ተችሏል። እንዲሁም ደግሞ ከ3ሺህ በላይ ሕጻናትን ከሞት መታደግ ተችሏል። ዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ይህንን ቃል ኪዳን በማስፋፋት ላይ ይገኛል። እነዚህ በርካታ በጤናው ዘርፍ የተገኙ ድሎች ናቸው ብሎ መውሰድ ይቻላል።

በወሊድ ወቅት የሚከሰት እናቶችን ሞት እጅግ መቀነስ ተችሏል። የዛሬ 15 ዓመት ኢትዮጵያ ውስጥ ከ100 ሺህ ነፍሰጡር እናቶች ከ700 በላይ የሚሆኑት በወሊድ ምክንያት ይሞታሉ። እኤአ ይህ አኃዝ 2020 ወደ 267 ቀንሷል፤ በቀጣይ በ2030 በዘላቂ ልማት ግቦች ላይ በተቀመጠው ግብ መሠረት 70 ለማድረስ እየሠራን ነው። ሥራው ቀላል አይደለም።

**ጥያቄ፦ በሽታን በመከላከልና በመቆጣጠር ረገድ የተሠሩ ሥራዎች 3 ምን ይመስላሉ ?**

**ዶክተር ደረጀ፡-** እንደሚታወቀው ሀገራችን ሦስት አይነት የበሽታዎች ጫና ነው ያለባት። ያደጉት ሀገራት አንድ፣ ወይ ሁለት ጫና ነው ያለባቸው። እኛ ጋ ሦስት አይነት ጫናዎች ናቸው። አንዱ የተላላፊ በሽታዎች ጉዳይ ነው፤ እጅግ ብዙ ስኬት የተገኘበት ዘርፍ ቢሆንም አሁንም ተላላፊ በሽታዎችን በተመለከተ ያልተወጣናቸው ችግሮች አሉ። ሁለተኛው ደግሞ አሁን እየበዛ ያለው ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ጫና ነው። ይህ ደግሞ በሀገራችንም፣ በሌሎችም የአፍሪካ ሀገራት እጅግ እየተስፋፉ ነው ።

ሦስተኛው ደግሞ የትራፊክ አደጋዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣት ነው። አሁን ላይ ማኅበረሰባችን ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረገ ነው። የትራንስፖርት አገልግሎት መስፋፋት አለ። እነዚህ ሁሉ የሦስት ጉዳይ፣ በሦስት ዘርፍ ጫና በሀገራችን ላይ እየመጣ እንደሆነ በተለያየ መንገድ ማየት ችለናል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ አንዳንድ የበሽታ መከላከል እና መቆጣጠር ጋር ተያይዞ ማንሳት የምፈልጋቸው ጉዳዮች አሉ። አንዱ እና ዋነኛው ትኩረት የምናደርግበት ቲቢን የመከላከል እና መቆጣጠር ተግባር ነው።

እዚህ ላይ እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ጥሩ ስኬት አላት ፤ይህንንም በዓለም አቀፍ መድረኮች ስታጋራ ቆይታለች። በተለይ ከመድኃኒት ጋር የተላመደ ቲቢ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ጫና ካሳደረባቸው 30 ሀገራት ውስጥ ነበርን፤ ከሦስት ዓመት በፊት ከዛ መውጣት ችለናል። በዚህም ኢትዮጵያ ውስጥ መድኃኒቱን የተላመደ ቲቢ እየቀነሰ መምጣቱን አይተናል፤ ይህ አንድ ጥሩ ስኬት ነው።

በዚህ ስድስት ወር ደግሞ የቲቢ ልየታ ላይ በርካታ ሥራዎች ተሠርቷል። 66ሺህ 387 ቲቢ ይኖርባቸዋል ተብሎ ከሚገመተው ማኅበረሰብ ውስጥ 81 ፐርሰንት ያህሉን መለየት ተችሏል። የቀሩትም በግጭት አካባቢ ያሉ ወረዳዎች እና ዞኖች ካልሆኑ በስተቀር ቤት ለቤት በመሄድ የቲቢ ምልክት የሚሳዩ ሰዎችን ለመለየት ትልቅ ሙከራ ተደርጓል። የተለዩትን ሙሉ በሙሉ ወደ ሕክምና ማስገባት እና መድኃኒት እንዲጀምሩ ማድረግ ተችሏል።

ሌላው በበሽታ መከላከል ላይ የምናነሳው የኤችአይቪ/ኤድስ ጉዳይ ነው። እንደሚታወቀው፤ ኤችአይቪ በሀገራችን ከፍተኛ ምጣኔ ከነበረበት እጅግ ዝቅ እያለ መጥቷል። ከአምስት ዓመት በፊት ያለው መረጃ/ ዳታ እንደሚያሳየው ከአንድ ፐርሰንት በታች ወይም የወረርሽኙ ቁጥጥር (ኢፒዴሚክ ኮንትሮል) በምንለው ደረጃ ውስጥ ገብቷል። ብዙ የአፍሪካ ሀገራት በዚህ ደረጃ አልመጡም። አሁንም ከ10 እና ከ20 ፐርሰንት በላይ ያላቸው የአፍሪካ ሀገራት አሉ። በእርሱ ላይ ትልቅ ርብርብ ተደርጎ መሻሻል ታይቷል።

ይሁን እንጂ በቅርብ ጊዜ የሚታይ ችግር አለ። በተለይ በከተማ አካባቢ ላይ በተወሰነው የማኅበረሰብ ክፍሎች ላይ ከፍተኛ የሆነ የኤችአይቪ ስርጭት ተስተውሏል። እርሱን ለመቀነስ በተለየ መንገድ ትልቅ ንቅናቄ ጀምረናል። ይሄንን ሁሉም ቦታ ለማድረስ ጥረታችን ይቀጥላል። በዚህ ስድስት ወር ውስጥ ትልቅ ትኩረት ያደረግነው በኤችአይቪ/ኤድስ ሦስቱ 95ዎቹን ለማሳካት ነው። ሁለተኛው እና ሦስተኛው 95 መድኃኒት መጀመር እና መድኃኒት ላይ ያሉት ደግሞ በአግባቡ መድኃኒቱ ውጤታማ ሆኖ መሥራቱን የምናይባቸው አመላካች ጉዳዮች ናቸው። በእነርሱ ላይ ከ95 ፐርሰንት በላይ አሳክተናል።

የመጀመሪያው 95 የሚባለው ኤችአይቪ በደማቸው ውስጥ እንዳለ የሚያውቀው የማኅበረሰብ ክፍል ላይ ገና ነን። ከ95 ፐርሰንት 84 ፐርሰንት ላይ ነን ያለነው። ስለዚህ ማኅበረሰባችን በደንብ እንዲመረመር፤ ወደ ጤና ተቋም እንዲመጣ በተለይ ደግሞ የበለጠ ተጋላጭ የሆነ የማኅበረሰብ ክፍል አለ። ሴተኛ አዳሪዎች፣ ረዥም መንገድ

ወደ ገጽ 15 ዞሯል

# ወቅታዊ

# “ባለፉት ስድስት ወራት 15ሺህ 557 ሰዎች ኤችአይቪ/ኤድስ ...

ከ14ኛው ገጽ የዞረ

የሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎች፣ እንዲሁም የቀን ሥራ የሚሠሩ፣ የተለያዩ ልማት አካባቢዎች ፕሮጀክቶች አካባቢ ላይ የሚሠሩ ወጣቶች የበለጠ ተጋላጭ ናቸው። እነርሱ ላይ ትኩረት አድርገን በዚህ ዓመት ብዙ ሠርተናል።

በዚህም በርካታ ሠዎችን መመርመር ችለናል። 15ሺህ 557 የሚሆኑ ሰዎች በዚህ ስድስት ወር ኤችአይቪ በደማቸው ውስጥ እንዳለ አይተናል። ይሄ አኃዝ ቀላል አኃዝ አይደለም። ሊተላለፍ የሚችል፣ በተለይ ደግሞ በደንብ ሳናውቀው አንዳንድ ከተሞች፣ አንዳንድ ቦታዎች ላይ በሚገርም ፍጥነት እየተስፋፋ እንደሆነ መረጃዎቻችን ያሳያሉ። በቀጣይም ትልቅ ርብርብ የሚደረግበት ነው።

ሌላው እንግዲህ ከተላላፊ በሽታዎች ስናልፍ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ለመከላከል ሰፊ ጥረት እየተደረገ ነው። በተለየ ስኳር፣ ግፊት፣ የልብ ሕመም ሌሎች ሕመሞች፤ በተለይ የካንሰር፣ የስኳር በሽታ ላይ ከየትኛውም ጊዜ በላይ የፖሊሲ ትኩረት ተሰጥቷቸው እየሠራን እንገኛለን። ከ85 ፐርሰንት በላይ እነዚህ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን መከላከል ይቻላል፤ እየተከላከልንም ነው። በጊዜ ከታወቁ፣ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ካደረግን፣ የአኗኗር ዘይቤያችንን፣ የአመጋገብ ሥርዓታችንን ከቀየርን መከላከል እንችላለን።

አክሞ ማዳን ውጤታማ አይደለም። ብዙ ወጪን ይጠይቃል። ለእኛ ሀገር ከባድ ስለሆነ። በእሱ ላይ ማኅበረሰባችንን ማስተማር ንቃተ ጤናው እንዲሻሻል ለማድረግ በሚዲያዎቻችን ተጠቅመን ብዙ እየሠራን እንገኛለን። ከዛ ውጭ ግን ተጋላጭ የሆኑ ማኅበረሰቦችን መመርመር ነው። ስለዚህ ከምርመራ ጋር ተያይዞ ተመርምረው፣ ራሳቸውን አውቀው ወደ ሕክምና እንዲገቡ ጥረት ተደርጓል፤ እየተደረገም ነው።

ለምሳሌ በዚህ ስድስት ወር ብቻ የስኳር ሕመምተኞችን ካየን ከአንድ ነጥብ 6 ሚሊዮን በላይ ስኳር የታመሙ ሰዎችን ለይተን ሕክምና እንዲጀምሩ አድርገናል። የደም ግፊት በደማቸው ውስጥ የተገኘባቸውን ከ98ሺህ በላይ የሚሆኑትን ለይተን ወደ ሕክምና አስገብተናል። ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከ25 ፐርሰንት በላይ የሚሆን የማኅበረሰብ ክፍል ግፊት አለበት ። ከወር ወር፤ ከዓመት ዓመት ብዙ ሰዎች ለሕክምና ይመጣሉ። መድኃኒታቸውን ወስደው በአግባቡ እየተጠቀሙ እንደሆነም በጥናት እያረጋገጥን እንገኛለን፤ ይሄም ይቀጥላል።

ሌላው ከካንሰር ጋር የተጀመረው ርብርብ እልህ አስጨራሽ ቢሆንም በርካታ ርቀቶችን መጥተናል። ርብርቡ አንድም ማኅበረሰባችን ስለ ካንሰር በደንብ እንዲያውቅ ፤ አውቆም በቅርብ ወዳለው ጤና ተቋም በመምጣት አገልግሎት እንዲያገኝ ነው። አሁን ላይ በ28 ጤና ተቋማት (በቅርብ የተወሰኑ የተጨመሩ አሉ) የካንሰር ታማሚዎች የኬሞ ቴራፒ ሕክምና የሚያገኙበት ሁኔታ ነው። በእነዚህ 28 ተቋማት ላይ ተጨማሪ መድኃኒቶችን፣ የሰው ኃይልን በማሰማራት ሕክምና እንዲሰጡ እያደረግን ነው።

የጨረር ሕክምና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ ነው። ቀደም ሲል በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ብቻ ይሰጥ የነበረው የጨረር ሕክምና አሁን ላይ ወደ ሰባት ማዕከላት ለማሳደግ ጥረት እያደረግን እንገኛለን። ሦስቱ ሐረማያ፣ ጅማ እና ጥቁር አንበሳ እየሠሩ ነው። አራቱ ደግሞ በቅርብ ጊዜ ወደ ሥራ ይገባሉ ።

ከካንሰሮች ውስጥ ደግሞ በጣም አንገብጋቢና እናቶቻችንን እየነጠቀን ያለው የማሕጸን በር ጫፍ ካንሰር (cervical cancer) ነው። ከአንድ ሺህ 300 በላይ ጤና ተቋማት በሽታውን የመለየት አቅም አላቸው። ተቋቱ የመለየት አቅም እንዲያጎለብቱ አድርገናል። በሁሉም ወረዳዎች ቢያንስ አንድ ጤና ተቋም የማሕፀን በር ጫፍ ካንሰርን መለየት ይችላል። ለይቶም እዛው ሕክምና መስጠት ይችላል። ገና በጅምር ያለ ከሆነ፤ ካልሆነ ደግሞ ወደሚቀጥለው ጤና ተቋም ሪፈር ማድረግ የሚችልበትን አግባብ ፈጥረናል። በዚህ ስድስት ወር ብቻ ከ264 ሺህ በላይ የማሕፀን በር ጫፍ ካንሰር መለየት ተችሏል። ችግር ያለባቸውን ወደ ሕክምና እንዲሄዱ ተደርጓል።

አሁን ላይ ተላላፊ ካልሆኑ በሽታ ጋር ተያይዞ በዓለማችንም በሀገራችንም እየበዛ ያለው የአዕምሮ ጤና ነው። የአዕምሮ ጤና ጥናቶች እንደሚያሳዩት በተለይ በተለያዩ ሀገራት፤ በኛም ሀገር ባለው ነባራዊ ሁኔታ የኑሮ ጫናም ሊሆን ይችላል፤ በግጭት የሚፈጠሩ ሊሆኑ ይችላሉ ማኅበረሰባችን ውስጥ የአዕምሮ ጤና መታወክ እየበዛ፤ እየተበራከተ መቷል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ወደ ጤና ተቋም ለመሄድ መገለል ይኖራል በሚል ፍራቻ አለ። በዚህ ዙሪያ በስፋት ለመሥራት እየታቀደ ነው። እስካሁን ባለውም በርካታ ጤና ተቋማት በዚህ ላይ ሥራ እንዲሠሩ አድርገናል። የመድኃኒት ግብዓቶችና ጤና ሙያተኞችን በዚህ ላይ ከማሠልጠን ጋር ተያይዞ ሰፊ ሥራ እየተሠራ ነው መሻሻሎች እየታዩ ነው። ነገር ግን በርካታ ሥራዎች ይቀሩናል ።

ከመከላከልና መቆጣጠር ሥራ ጋር ተያይዞ በመጨረሻ የማነሳው ትኩረት የሚሹ ”ሀሩራማ በሽታዎች” የሚባሉ በሀገራችን የሚታዩ አሉ። ለምሳሌ አንዱ ትራኮማ ነው። ትራኮማን ከኢትዮጵያ ለማጥፋት በርካታ ሥራዎች እየሠራን እንገኛለን። አንዱ እንግዲህ የመድኃኒት እደላ ነው። የትራኮማ መድኃኒት በብዙ ቦታዎች ላይ እያዳረስን እንገኛለን። ከእቅዳችን 80 በመቶ በላይ ወረዳዎች የመድኃኒት እደላ እያደረግን ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የአይን ቆብ መቀልበስ (ከትራኮማ ጋር ተያይዞ የሚመጣውን) የጤና ችግር በቀዶ ሕክምና ለማስተካከል በርካታ ጥረት እየተደረገ ነው። በዚህ ስድስት ወር ብቻ 35 ሺህ በላይ የሚሆኑ የቀዶ ሕክምናዎችን አድርገናል። በሁለት ዓመት ውስጥ ሙሉ በሙሉ የአይን ቆብ መቀልበስ ያለባቸውን ዜጎቻችንን ከዚህ በሽታ ነፃ እንደምናደርግ እቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው ያለው ።

በአጠቃላይ ስናይ ተላላፊም ይሁን ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች መከላከሉ ላይ በስፋት እየተሠራ ነው። ሕክምና አሰጣጥ ሥርዓት ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን እያረመን፤ ጤና ተቋማት በነዚህ ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ፤ እኤአ በ2030 ብዙ በሽታዎችን ጨርሶ ለማጥፋት (by elimination) የታቀዱ ጉዳዮች አሉ። በእነሱ ላይ የበለጠ ትኩረት እያደረግን እንደምንሠራ ለማንሳት እፈልጋለሁ።

**ጥያቄ፡- ድንገተኛ ሕክምናን በተመለከተ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ምንድን ናቸው?**

**ዶክተር ደረጀ፡-** በሀገራችን ብሎም ደግሞ በዓለም አቀፍ ደረጃ በእያንዳንዱ ሀገር ድንገተኛ ምላሽ የሚያስፈልጋቸው ወይም ደግሞ የማኅበረሰብ ድንገተኛ የጤና አደጋዎች እየተበራከቱ ናቸው። ኮቪድ 19 አንዱ ነው። በጋራ ሁላችንም ስንረባረብበት የነበር ነው። ከዛ ውጭ ግን በርካታ ችግሮች ሀገራችን እየተከሰቱ ነው። አንዱ የወባ ወረርሽኝ ነው። የወባ ወረርሽኝ ባለፉት ዓመታት እጅግ ስኬት ያገኘንበት፤ ወረርሽኙም ዝቅ ያለበት ነው። ባለፉት ሁለት ዓመታት ግን በተለየ መንገድ ከዓመት ዓመት እየጨመረ ነበር። በዚህ ስድስት ወር በርካታ የወባ ሕሙማንን መለየት ተችሏል። ለዚህም በርካታ ምክንያቶች ይኖራሉ። ከነዚህ ውስጥ አንዱ የአየር ንብረት ለውጥ ነው። ከዛም በተጨማሪ በድርቅ የተጎዱ አካባቢዎች ላይ በእጅጉ ስርጭቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ መምጣቱን አይተናል።

አሁንም በርካታ ችግር ያለበት ወረርሽኝ መሆኑን አይተናል። ከዚህም ጋር ተያይዞ የተሠሩ ሥራዎችን ለዋቢነት ያህል ጥቂት ለመጥቀስ፤ ከ20 ሚሊዮን በላይ የሚሆን የአልጋ አጎበር ማኅበረሰባችን እንዲጠቀም ከባለፈው ዓመት ጀምሮ እያሰራጨን እንገኛለን። የተሰራጩትንም ማኅበረሰቡ በደንብ እንዲጠቀም እየሠራንበትም ነው። ስርጭቱን ሌሎች ቦታዎች ለማዳረስ እየተሠራን ነው። ለተፈናቀሉ ወገኖችም ጭምር ለማዳረስ ጥረት ተደርጓል። የወባ ሕመም ባጭር ጊዜ ውስጥ ሊጎዳ የሚችልና አንድ ሰው ሕክምና ካገኘ ደግሞ በቀላሉ የሚድን ስለሆነ ማኅበረሰባችን ወደ ጤና ተቋም እንዲመጣና ቶሎ ሕክምና እንዲያገኝ፤ የጤና ተቋማት በግብዓቶች እንዲሟሉ፤ የቤተ-ሙከራ (laboratory) አቅርቦትም እንዲሻሻል ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው። ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻሎች አሉ። አሁንም ከአየር ንብረት ለውጡ ጋር ተያይዞ ወባን እንደ አደጋ ነው የምናየው። ችግሩን ለመከላከል ማኅበረሰባችን መረባረብ ይኖርበታል። ባለፉት ዓመታት በተገኘው ድል በአመራሩም ሆነ ማኅበረሰቡ “ወባ ጠፍቷል” የሚል ትክክል ያልሆነ ግንዛቤ ተይዟል። ይሁን እንጂ ይሄ መዘናጋት መልሶ ለሌላ ችግር እያጋለጠን፤ ዋጋ እንዳያስከፈለን ስለሆነ፤ ሁላችንም ወባ ላይ መረባረብ አለብን።

ሌላው የጤና አደጋ ለማኅበረሰባችን እያመጣ ያለው የኮሌራ ወረርሽኝ ነው። የኮሌራ ወረርሽኝ ከዚህ በፊት ገልጸነዋል፤ የኮሌራ ወረርሽኝ ከ300 ወረዳዎች በላይ ተቀስቅሷል። በዚህ ስድስት ወር በተለየ መንገድ እቅድ አቅደን ስንሠራ የነበረው የኮሌራ ወረርሽኝን ለመቆጣጠር ነው። በዚሁ መሠረት ወረርሽኙ ከተከሰተባቸው 300 ወረዳዎች ውስጥ በዚህ ሰዓት ላይ 47 ወረዳዎች ላይ ብቻ ነው ሪፖርት እየተደረገ ያለው። ሌላውን ግን ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር ችለናል።

ከነዚህ 47 ወረዳዎች ውስጥም ከትናንት በስቲያ ሪፖርት ያደረጉት ስምንት ወረዳዎች ብቻ ናቸው። ሌሎቹ ነፃ እስኪሆኑ 40 ቀን እንጠብቃለን። ከዛ በኋላ ነፃ እንላቸዋለን። ምክንያቱም ዳግም ሊመጣ ስለሚችል እስከ 40 ቀን ነፃ እስኪሆኑ እንጠብቃለን። ይህንንም በአጭር ጊዜ ውስጥ የምንቆጣጠረው ወረርሽኝ ይሆናል። የበሽታዎች ወረርሽኝ በጎረቤት ሀገራት ኬንያ እና ሱማሌ ላይ በጣም የሚታይ በመሆኑ በጋራ ለመሥራት ጥረት እየተደረገ ነው። እሱም አንድ ትኩረት የምናደርግበት ጉዳይ ነው።

ሌላው ኩፍኝ ነው። ከ200 ወረዳዎች በላይ በኩፍኝ ወረርሽኝ ተጠቅተዋል። በተለይ ባለፉት ሦስት ወራት ላይ በትኩረት ነው እየሠራን ነው። በዚህ ሰዓት ላይ 70 ወረዳዎች ብቻ ነው ኩፍኝን ሪፖርት እያደረጉ ያሉት። እነርሱም ቢሆኑ የተወሰነ ቁጥር ነው ሪፖርት እያደረጉ ያሉት። በባለፈው አንድ ወርም በነዚህ ወረዳዎች ላይ ሁሉን አቀፍ ክትባት ሰጥተናል። የፀረ ኩፍኝ ክትባት ሙሉ በሙሉ በሁሉም ቦታ ላይ ደርሰን ክትባት ተሰጥቷል። ይሄ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ሙሉ በሙሉ እንድንቆጣጠረው የሚያስችል አቅም ነው ብለን እናስባለን ።

ከድንገተኛ ሕክምና አሰጣጥ ሥርዓት ጋር ተያይዞ በግጭት የተጎዱ አካባቢዎች፣ በሰው ሠራሽ እንዲሁም ደግሞ በተፈጥሮ የተለያዩ ክስተቶችን ያስተናገዱ አምስት ክልሎች (ትግራይ፣ አፋር፣ አማራ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝና ኦሮሚያ) ላይ ትኩረት አድርገን እየሠራን እንገኛለን። በዚህ ችግር ውስጥ እያለፉ ያሉ የተወሰኑ ወረዳዎችና ዞኖች አሉ። በተለይም ደግሞ በእነዚህ አካባቢዎች ላይ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የተፈናቀሉ ዜጎች አሉ። እነርሱንም ማዕከል ያደረገ ምላሽ እየሰጠን ነው። አንደኛው የሕክምና መሣሪያዎችንና መድኃኒቶችን በተቻለ መጠን ማድረስ ነው። በመኪና ማድረስ ያልተቻለበትን በአየር ትራንስፖርት እያደረስን ነው። ለአብነት በተለይ ቤኒሻንጉል በዚህ መልኩ ያደረስንበት ቦታ አለ ነው። እኛ ብቻ ሳንሆን አጋር ድርጅቶቻችን እኛ መድረስ የማንችልባቸው ቦታ ላይ ገብተው ሕክምና እንዲሰጡ ጥረት እየተደረገ ነው ።

ከ200 በላይ የሚሆኑ ጊዜያዊ ክሊኒኮችን በተንቀሳቃሽ የጤና ቡድን በመመራት ብዙ የማኅበረሰብ ክፍላችን ተጠልለው ባሉበት ካምፕ ውስጥ አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል። በእነዚህ ክልሎች በግጭት የወደሙ የጤና ተቋማትም አሉ። ጤና ጣቢያዎች፣ ጤና ኬላዎች፣ ቤተ-ሙከራዎች፤ ደም ባንኮች፣ ሆስፒታሎች የመሳሰሉ የተጎዱ አሉ። እነዚህን በደንብ ለይተን በርካታ ጤና ተቋማትን ከግጭቱ ጋር ጎን ለጎን ምላሽ ለመስጠት ጥረት እየተደረገ ነው። አብዛኛው እየተሠራ ነው። ችግሩ ጊዜና አቅም የሚጠይቅ ስለሆነ ቀሪ ሥራዎች አሉ። ነገር ግን በአብዛኛው እነዚህ ጤና ተቋማት ወደ ሥራ እየተመለሱ ነው ። ወደ ሥራ ተመለሱ ስንል ግን ሁሉ ነገር ተሟልቶ አይደለም። አንዳንድ ቦታ ላይ ከቤተ-ሙከራ ጋር፤ ከኤክስሬይ ጋር ተያይዞ የሚቀሩ ሥራዎች አሉ። ይሁን እንጂ ወሳኝ የሚባሉ ጤና አገልግሎቶች በአብዛኛዎቹ ጤና ተቋማት እንደተጀመሩ በመረጃዎቻችን ወርደንም መድረስ የምንችልበት ቦታ ላይ ምልከታችን ይህንን ያሳያል።

ከላይ ከጠቀስኳቸው ወረርሽኞች ወባም ሊሆን ይችላል ኩፍኝም፣ ኮሌራም በተቀሰቀሱበት አካባቢ ዳግም እንዳይነሳ ፤ ከተነሳም እንዳይስፋፋ ቶሎ ምላሽ ለመስጠት በእጅጉ ትኩረት አድርገን ስንከታተልበት የነበረበት ሁኔታ አለ። በዚህ ደረጃ ባንከታተል በተለይ በግጭትና በተለያዩ ጉዳዮች የተጎዱ አካባቢዎች በጤና አደጋዎች ብዙ ሕጻናትን፣ እናቶችን እናጣ ነበር። ግን በትኩረት ስለተሠራ የሞት ምጣኔና በእነዚህ በሽታዎች የሚጎዱበትን ምጣኔ በእጅጉ መቀነስ ተችሏል። ይህ ትልቅ ርብርብ የተደረገበት እንደሆነ ማሳያ ነው።

**ጥያቄ፡- የጤናውን ዘርፍ ለማሻሻል የመሠረተ ልማት ግንባታዎች እና ከአቅርቦት ጋር በተያያዘ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ምንድን ናቸው?**

**ዶክተር ደረጀ፡-** ከቁጥጥርና ከመድኃኒት ሕክምና መሣሪያ አቅርቦት ጋር ተያይዞ መግቢያ ላይ እንደተነጋገርነው በተለይ ከግብዓት ጋር ተያይዞ ትልቁ ፈተናችን ነው። ይህን በሚመለከት መጨረሻ ላይ እናነሳዋለን። ያም ሆኖ ግን ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመነጋገር የመድኃኒት አቅርቦቶች እንዲሻሻሉ በዚህ ስድስት ወር ከፍተኛ ርብርብ ተደርጓል። የተፈጠረው ጫና በጤና ተቋማት ውስጥ መድኃኒቶች እንዳይገኙ እስከ ማድረግ የደረሰ ቢሆንም በተለያየ መንገድ ጫናውን አሳልፈናል። በተለያዩ ሥራዎች ችግሮቹን ለማሸነፍ ጥረት ተደርጓል። በአጠቃላይ በዚህ ግማሽ ዓመት በመደበኛ በጀት የሚገዙ መድኃኒቶች አሉ። እነርሱን በ3 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር ተገዝቶ ወደ ጤና ተቋም እንዲሰራጩ ተደርጓል።

በአጋር ድርጅቶች የሚደገፉ የተለያዩ ፕሮግራሞች አሉ። ከላይ እንደገለጽኩት በነፃ የምናከፋፍለው የኤች አይቪ፤ የቲቪ የመሳሰሉት በጣም ትላልቅ ብር ወጪ

ወደ 16ኛው ገጽ ዞሯል



# “ባለፉት ስድስት ወራት 15ሺህ 557 ሰዎች ኤችአይቪ/ኤድስ ...

ከ15ኛው ገጽ የዞረ

የምናደርግበት ነው። ይህንን በ9 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር በአጠቃላይ 13 ነጥብ 1 ቢሊዮን ብር የሚያወጡ መድኃኒቶች፣ የላብራቶሪ ኤጀንቶች፣ ሕክምና መሣሪያዎችን በዚህ ስድስት ወር ብቻ ገዝተን ለማከፋፈል ተችሏል። ይህ “በጣም በትልቅ ጫና ውስጥ ተሆኖ የተሠራ ነው” ብዬ ማስቀመጥ እችላለሁ። ይህ ብቻ ሳይሆን የሀገር ውስጥ አምራቾችንም ለማበረታታት በዚህ ዓመት ከፍተኛ ውሳኔ ተላልፏል። እንደሚታወቀው እስከ 50 በመቶ የሚሆኑ መድኃኒቶችን የሀገር ውስጥ አምራቾች እንዲያቀርቡ ተፈቅዷል።

እንደሚታወቀው ሀገራችን ውስጥ ወደ 13 የሚሆኑ የመድኃኒት ፋብሪካዎች አሉ። ግብዓታቸውን ከውጪ የሚያመጡ ቢሆንም እዚህ ሀገር ውስጥ ወሳኝ የሆኑ መድኃኒቶችን ማምረት ይችላሉ። ስለዚህም እነርሱ የውጪ ምንዛሪ እንዲያገኙ ተመቻችቶላቸዋል። እየሠሩ ነው። የምናወጣቸው ጨረታዎችም ውስጥ በጣም እየተወዳደሩ ነው ያሉት። በጅምር ላይ ያለ ቢሆንም ለእነርሱ ጥሩ ማሻሻያ ተሠርቷል ማለት ይቻላል። ይህንን በማድረጋችን በአጠቃላይ አቅርቦት በጤና ተቋም ውስጥ ስናይ በፕሮግራም መድኃኒቶች ለቲቪ፣ ለኤች አይቪ፣ ለወባ ... ለሌሎችም በሽታዎች ለአጋር ድርጅቶቻችንና እኛም ጨምረን የምናቀርበው 87 በመቶ ላይ ደርሷል። ከዚህ በፊት እስከ 95 በመቶ ከፍ ያለ ቁጥር ነበር። በዚህ ወር እንግዲህ ቅድም ባልኩት መልኩ 87 በመቶ ላይ ነው ያለው። በቀጣይ ግን በብዛት ወደ ሀገር እየገቡ ስለሆነ በዓመቱ መጨረሻ ላይ እንደሚሻሻል ለማሳወቅ እፈልጋለሁ።

በሌሎች መደበኛ መድኃኒቶች ደግሞ 70 በመቶ ላይ ነው ያለነው። ይህም ዝቅ ያለ ምጣኔ እንደሆነ ይገባናል። ማኅበረሰባችን የመድኃኒት እጥረት እንዳለ በየቀኑ የሚናገረው ነው፤ ይህም ትክክል ነው። በእርግጥ ወሳኝ የሚባሉና ሕይወት አድን የሚባሉ መድኃኒቶች በተቻለ መጠን እንዲኖሩ እናደርጋለን። ከዚያ ባለፈ አንዳንድ መድኃኒቶች ላይ አሁንም እጥረት እንዳለ ይታወቃል። ይህን ለመቅረፍ እንግዲህ በርካታ ጥረቶችን እያደረግን እንገኛለን። ከነዚህም አንዱ የውጭ ምንዛሪ የማግኘት ምጣኔያችንን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻሻልን ነው። የሆነ ጊዜ ላይ ችግር ሆኖብን ነበር፤ አሁን በጥሩ መንገድ ድጋፍ እያደረገልን ይገኛል። ከታወቁ ካምፓኒዎች ጋር የሦስት ዓመት ውል በመግባት በየዓመቱ የሚቀያየረውን የግዢ ሁኔታ በሦስት ዓመት በማድረግ የተሻለ ግብዓት እንዲኖር ጥረት እየተደረገ ነው። ትልቁ ግን ሀገር ውስጥ መድኃኒት እንዲኖር ማድረግ ነው። ስለዚህ የመድኃኒት ፋብሪካዎቻችንን የበለጠ ማጠናከር እንደ አንድ ትልቅ ነገር ታይቷል።

ከግብዓት ጋር በተያያዘ ሌላው ትልቁ ጉዳይ የደም ግብዓት ነው። ደም ከሌለ ድንገተኛ አደጋዎችን ሕክምና ለመስጠት ፣ የተለያዩ የኦፕሬሽን አገልግሎቶችን መስጠት በጣም ከፍተኛ ችግር ስለሚፈጥር እዚህ ላይ ትልቅ መሻሻል እየታየ ነው። በዚህ ስድስት ወር 202 ሺህ 509 ዩኒት ደም ለመሰብሰብ ታቅዶ 168 ሺህ 611 ወይም 83 በመቶ መሰብሰብ ተችሏል። በአብዛኛው በትምህርት ቤትና በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ያሉ ወጣቶች እየተሳተፉበት የሚገኝ ነው። ከዚህ አንጻር ማኅበረሰባችንም ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻል እያሳየ ነው ።

ይህም በሆኖ አሁንም ገና ነው። ማኅበረሰባችን ከደም በላይ የተለየ ስጦታ እንደሌለ አውቆ መሳተፍ መቻል አለበት። ስለዚህ በቀጣይነት የያዝነው ትልቁ ጉዳይ በበጎ ፈቃደኝነት በየሦስት ወሩ መጥተው ደማቸውን የሚሰጡ ወይም የሚለግሱ በርካታ የማኅበረሰብ ክፍሎች እንዲኖሩን ማድረግ ነው። ስለዚህ የደም ፍላጎታችን የዚህን ሁለትና ሦስት እጥፍ ነው ። በተለይ አሁን በሀገራችን ከሚከሰተው የተለያየ ችግር (የትራፊክ ወዘተ) ጋር ተያይዞ እንዲሻሻል እንጠብቃለን። እስከ አሁን ግን ያለው አፈጻጸም የሚያበረታታ እንደሆነም በዚሁ ማንሳት እፈልጋለሁ። ይህን ብዬ እንግዲህ ሌሎችም ከግብዓት ጋር የሚያያዙ በርካታ ነገሮችን በእቅዳችን ውስጥ አስገብተን እየሠራን መሆኑን ማንሳት እፈልጋለሁ። ,

ከቁጥጥራችን ጋር ተያይዞ እንደጤና ሴክተር ትልቁ ትኩረት ከምናደርግበት ጉዳይ ውስጥ የጤና ቁጥጥር ነው። የጤና ቁጥጥር ስንል ሦስት ነገሮችን ነው የምናየው። አንዱ ጤና ሙያተኞቻችንን የምንቆጣጠርበት ሥርዓት ነው። ጤና ሙያተኞቻችንን በሁለት አይነት መንገድ ነው የምንቆጣጠረው፤ አንደኛ ከዩኒቨርሲቲ ተመርቀው ሲወጡ እንፈትናለን። እንደሚታወቀው ከ200 በላይ የጤና ባለሙያዎች እንዳሉ ይታወቃል፤ ከነዚህ ውስጥ ከግማሽ በላይ የጤና ሙያተኛ ባለባቸው 13 ሙያዎች ላይ ፈተና እንሰጣለን። በነዚህም ላይ በጣም ስኬት እያመጣን ነው፤ የማለፍ ምጣኔውም ከ50 እስከ 60 በመቶ ነው። ያልተሳካላቸውን ደግሞ ከሦስት ወር በኋላ እንደገና ሥልጠና በመስጠት እንፈትናቸዋለን።

እንግዲህ እኛ የምንፈትነው በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ያላቸውን እውቀት ብቻም ሳይሆን ባሕሪያቸውንም ጭምር ነው። ከተግባርም ጋር ተያይዞ የተለያዩ ፈተናዎችን ጨምረን ነው የምንፈትነው። ትምህርት ሚኒስቴር እውቀት ላይ ብቻ ትኩረት አድርጎ የሚፈትነው የመውጫ ፈተና (exit exam) እንዳለ ሆኖ ከዚያ ውጭ ሁለተኛ ፈተና እንፈትናለን፤ ይሄም አንዱ ነው። በዚህ በየአምስት ዓመቱ በሲፒዲ (Continuous Professional Development) መሠረት የሠሩትን ሥራና የወሰዱትን ሥልጠና በማየት፤ በአጠቃላይ በሥራ ላይ ያላቸውን መሻሻል እያየን ፈቃዳቸው ይታደሳል።

ከዚያ ውጭ እንደሚታወቀው፤ በጤና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ጤና ሙያተኞቻችን ላይ የሚስተዋሉ ችግሮች አሉ፤ ማኅበረሰቡ የሚያነሳቸው። በርካታ የጤና ሙያተኞች ራሳቸውን ሰጥተው ቀን ከሌሊት የሚሠሩ እንዳሉ ሁሉ የሚያጠፉም ደግሞ አሉ፤ በየቦታው፤ ችላ ባይነት ይኖራል። በተወሰኑት የጤና ባለሙያዎች ላይ ችላ ባይነት ይታያል። እነሱም እንዲማሩ ማድረግ ላይ እየተሠራ ነው፤ በሙያ ሥነምግባሩ በኩልም አስተማሪ የሚሆን እርምጃ እንዲወሰድ እየተደረገ ነው። በቀጣይ ትልቁ ትኩረታችን የሚሆነው በጤና ሙያተኞቻችን ሥነምግባር ላይ መሥራት ይሆናል። ይህን የማስተካከሉን ሥራ አንዱ ትኩረታችን አርገን እንሠራለን።

ሌላው ሥራ መድኃኒት እና ምግብ ከውጭ የሚያስገቡትን መቆጣጠር ነው። በዚህ በኩል ፍቃድ መስጠት ላይ ትልቅ ጥንቃቄ ይደረጋል። ፍቃድ ለመስጠት ብቻ ሳይሆን አሠራራቸውንም በደንብ በመከታተል ይሠራል። አብዛኛዎቹ የመድኃኒት እና የምግብ ተቋማት ዘንድ ደርሰን ኢንስፔክሽን /ፍተሻ/ እናደርጋለን። እነዚህ ፍተሻዎችም በአብዛኛው ድንገተኛ /ሳይዘጋጁ የሚደረግ/ ናቸው። በዚህ ላይ በመመሥረት በተከናወነ ሥራም በርካታ ጤና ተቋማት ላይ እርምጃም ተወስዷል።

ከእነዚህ የመድኃኒት እና የምግብ ተቋማት ውጪ የግል ጤና ተቋማትም በጤና ሚኒስቴር እና በክልል ጤና ቢሮዎች በኩል ቁጥጥር ይደረግባቸዋል፤ በዚህም በዓመት ሁለት ጊዜ ቁጥጥር እናደርጋለን። በዚህ ዓመትም በአብዛኛዎቹ የመድኃኒት እና የምግብ ተቋማት ዘንድ ሄደን ቁጥጥር አድርገናል። በእነዚህ የግል ጤና ተቋማት ውስጥ የታዩ መልካም ተሞክሮዎች አሉ፤ ሊሻሻሉ የሚገባቸው በርካታ ጉዳዮችም ይስተዋላሉ፤ በተለይ ከፍተኛ ዋጋ ማስከፈል፣ አላስፈላጊ ሕክምናና ላቦራቶሪዎችንና መድኃኒቶችን ማዘዝ በበርካታ ተቋማት ዘንድ ተስተውሏል። ይህንንም ችግር ከማኅበራቸው ጋር በመሆን በቀጣይነት እየፈታን መሄድ እንደ ጤና ሚኒስቴርም ጠበቅ ያለ እርምጃ መውሰድ፤ መልካም የሚሠሩትን መደገፍ እንደ አሠራር ተቀምጧል። በዚህ ላይ በቀጣይነት እንደምንሠራ እዚሁ ለማንሳት እወዳለሁ።

**ጥያቄ ፡- በሰው ኃይሉ እና የአገልግሎት አሰጣጡ ላይ የተከናወኑ ተግባሮች ምን ይመስላሉ?**

**ዶክተር ደረጀ፡-** ከግንባታ ጋር ተያይዞ እንደሚታወቀው ጤና ሚኒስቴር ከሌሎች ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች በተለየ በጤና ተደራሽነት ላይ በርካታ ሥራዎችን ይሠራል። ይህን ተከትሎም የጤና ተደራሽነቱ የተሻሻለ ቢሆንም፣ አሁንም ክፍተቶች እንዳሉበትም ይታወቃል። ስለዚህ የጤና ተቋማትን በየጊዜው መገንባትና ማሻሻል ያስፈልጋል። አንድ ጤና ተቋም ለ25 ሺህ ሰው እንዲያገለግል ይጠበቃል፤ እንደሚታወቀው፤ በሀገሪቱ የሕዝቡ ብዛት በየዓመቱ ከሦስት ሚሊዮን በላይ እየጨመረ ነው። በመሆኑም ይህንን ማዕከል ያደረገ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል። በተለያዩ ችግሮች ደግሞ የወደሙና ያረጁ ጤና ተቋማት አሉ። እነዚህን መገንባት እና ማስተካከል ላይ ትኩረት እናደርጋለን።

እንደ ጤና ሚኒስቴር በቅርቡ ትላልቅ ኢንቨስትመንቶችን እያካሄድን ነው፤ ኢትዮጵያን የሚመጥኑ ለአፍሪካ ምሳሌ የሚሆኑ ትላልቅ ግንባታዎች ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ ይገኛል። አንዱ በአህሪ (አርማወር ሀንሰን የጥናት ኢንስቲትዩት) ሲካሄድ የቆየው ደረጃውን የጠበቀ የላቦራቶሪ እና የማስተማሪያ ግዙፍ ሕንፃ ግንባታ በቅርቡ ተጠናቋል። ይህ ትልቅ ስኬት ነው።



በዚህ ዓመት ያጠናቀቅነው እና ወደ ሥራ እየገባ ያለው ይህ ሕንጻ በዓለም አቀፍ ደረጃም ሆነ ለሀገራችን ትልቅ አቅም የሚፈጥር ኢንቨስትመንት ነው።

ሌላው አለርት ሆስፒታል እንደሚታወቀው በድንገተኛ ሕክምና ላይ ትልቅ ትኩረት የሚያደርግ ነው። አሁን እየሰጠ ያለው አገልግሎት በቂ አይደለም፤ ይህን ታሳቢ በማድረግም ግራውንድ ሲደመር ሰባት ግዙፍ ዘመናዊ ሕንጻ ግንባታ እየተካሄደ ይገኛል። ሕንጻው ሙሉ በሙሉ የትኛውንም አይነት ድንገተኛ ሕክምና ማከም የሚችል ለየት ያለ ግንባታ እየተከናወነ ነው ያለው። ግንባታው በፍጥነት እንዲሄድ ጥረት እየተደረገ ነው። አማኑኤል ሆስፒታል ላይ ትልቅ የማሻሻያ እና የስታፍ መኖሪያ ግራውንድ ሲደመር 12 እየተሠራ ይገኛል። እነዚህ ሁሉ በአጠቃላይ በመንግሥት በተመደበ በአንድ ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር ነው ግንባታቸው እየተካሄደ የሚገኘው።

የላቦራቶሪ ሥርዓታችንን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፤ በኮቪድ-19 ባገኘነው ተሞክሮ መሠረት ኢትዮጵያ በቀጣይ በአፍሪካም ደረጃም በተለየ እነዚህን ወረርሽኞችን ለመከላከል ጠንካራ የጤና ሥርዓት እንዲኖራት ትፈልጋለች። ስለዚህ በዓለም ባንክ እና በተለያዩ ድርጅቶች ድጋፍ ትልልቅ ግንባታዎችን ለኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት እያደረግን እንገኛለን። ለአብነትም ባለ 11 ወለል “ባዮ ባንክ እና የላብ ማረጋገጫ ናሙና ማምረቻ” የሚባል በዓለም አቀፍ ደረጃ በተወሰኑ አገራት ብቻ የሚገኝ ተቋም ግንባታ የዛሬ ሦስት ወር አካባቢ ተጀምሯል፤ ይህም ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካም እንዲሁም ለሌሎች ሀገራትም ሊሆን የሚችል የትልቅ ላቦራቶሪ ይሆናል።

በቀጣይነት ደግሞ ከመቶ ሚሊዮን ዶላር በላይ ወጪ የምናደርግበት ትልቅ ደረጃ/ሌብል/ 3 ላቦራቶሪ የሚባል በተወሰኑ ሀገራት ብቻ ያለ፣ ለአፍሪካም ማዕከል የሚሆን ግንባታም በቅርቡ ይጀመራል። ላቦራቶሪው ደቡብ አፍሪካ ውስጥ ካለ አንድ ላቦራቶሪ በስተቀር በዚህ ደረጃ አቅም ያለው ላቦራቶሪ አፍሪካ ውስጥ የለም። ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ለአፍሪካ ተብሎ የሚሠራ ነው። ከአፍሪካ በሽታ መቆጣጠሪያ ማዕከል CDC (African Disies Control Center) እና ከዓለም ባነክ ጋር የተጀመረ ትልቅ ግንባታ ነው። የዚህ ግንባታ አካል የሆኑ ላቦራቶሪዎችም ግንባታዎችም ኢትዮጵያን ከጎረቤት ሀገራት ጋር በሚያዋስኗት የመውጫና መግቢያ በሮች ላይ እየተካሄዱ ናቸው። ላቦራቶሪዎቹ በጣም ዘመናዊ ሲሆኑ፣ ሰዎች በድንበር አካባቢዎች ሲያልፉ ወረርሽኞችንና ሌሎች በሽታዎችን ይዘው እንዳይገቡ፣ ከእኛም ወደ ሌላ ቦታ ሲሄዱ ተመርምረው እንዲሄዱ ለማስቻል የሚገነቡ ናቸው። በአጠቃላይ ወደ አንድ ቢሊዮን ብር የሚጠጋ ወጪ ተመድቦላቸው እየተሠሩ ናቸው።

በመድኃኒትና ምግብ ቁጥጥር ላይም የሚሠራ ዘመናዊ ላብራቶሪም ያስፈልገናል። አሁን በሙሉ አቅም ሳይሆን በተወሰነ አቅም ነው የምንሠራው። ወደ አገራችን የሚመጣ እያንዳንዱ መድኃኒት ምን አለው፣ ምን ያህል ይሠራል፣ ፈዋሽነቱና ደህንነቱ ምን ያህል የተረጋገጠ ነው የሚለውን በተወሰነ ደረጃ ነው የምናውቀው። በተጨማሪም በሀገራችን ያሉት ምግቦች ምን ንጥረ ምግቦች አሏቸው፣ ከሌላው በምን ይለያሉ፣ ለማኅበረሰባችን ምን ያህል ምቹ ናቸው የሚሉትን ለመለየት አቅም ያስፈልጋል። እነዚህንና ሌሎች ነገሮችን ሊለይ የሚችል፣ ለአፍሪካም ማዕከል የሚሆን፣ G+10 የሆነ የመድኃኒትና የምግብ ቁጥጥር የልኅቀት ማዕከል እየተገነባ ይገኛል። ይህ ትልቅ ስኬት ነው። በተለያዩ ቦታዎችም የክልላዊ ላብራቶሪዎች ግንባታዎችን እናከናውናለን።

በአጠቃላይ በስድስት ወራት ከ300 በላይ የሚሆኑ የተለያዩ ግንባታዎችን ጨርሰን አስረክበናል። ከእነዚህ ግማሾቹ በፌዴራል ደረጃ የተገነቡ ናቸው፤ የተቀሩት ደግሞ በክልል የተገነቡ ናቸው። በክልሎች ጤና ጣቢያዎችን ለማስፋፋትና ለመገንባት የሚከናውነውን ተግባር እየደገፍን ነው። ለጤና ተቋማት ውሃና መብራት የምንሠራቸው ሥራዎችም አሉ። የኦፕሬሽን አገልግሎት በጤና ጣቢያዎች እንዲጀመር ትልቅ ጥረት አድርናል። ከ400 በላይ በሚሆኑ ጤና ጣቢያዎች እናቶች እዚያው እንዲወልዱ ለማድረግ የተጀመረ ፕሮጀክት አለ። ከእነዚህ መካከል ግማሾቹ በዚህ ስድስት ወራት ውስጥ በቅርቡ ወደ ሥራ ገብተዋል፤ ከዚህ ውስጥ 106 የሚሆኑት ጤና ጣቢያዎች የኦፕሬሽን አገልግሎት መስጠት ይችላሉ። እናቶች ለኦፕሬሽን የግድ ወደ ሆስፒታል መሄድ አይጠበቅባቸውም። ይህን ማድረጋችንም ትልቅ ስኬት ነው ብለን እናምናለን።

ጤና ኬላዎችን ማሻሻል ሌላው ሥራ ነው። ጤና ኬላ ሲባል ከዚህ ቀደም የሚታወቀው ትንሽ ብሎክ ነው፤ ሁለት የጤና ኤክስቴንሽን ናቸው የሚሠሩበት። የማኅበረሰባችን ፍላጎት ግን ከዚያ አልፏል። ጤና ኬላዎችን ሰፋ በማድረግ በጤና ጣቢያ ደረጃ የሚሰጡ አገልግሎቶች በጤና ኬላዎች እንዲሰጡ የማድረግ እቅድ አለን። በስድስት ወራት ውስጥ ከተከናወኑ ተግባራት መካከል 76ቱ ጤና ኬላዎች (Comprehensive Health Posts) ወደ ሥራ መግባታቸው ይጠቀሳል። ይህ በመሆኑም እነዚህ ተቋማት ትልቅ አቅም ይሰጣሉ፤ ማኅበረሰቡ የጤና አገልግሎቶችን በአቅራቢያው ያገኛል፤ መከላከል ብቻ ሳይሆን ሕክምና

ወደ 17ኛው ገጽ ዞሯል

# ወቅታዊ

# “ባለፉት ስድስት ወራት 15ሺህ 557 ሰዎች ኤችአይቪ/ኤድስ ...

**ከ16ኛው ገጽ የዞረ**

ጭምር የሚሰጡ የጤና ባለሙያዎችን (ነርሶች፣ ጤና መኮንኖች፣ አዋላጆች...) በቦታው ሆነው እንዲሠሩ እየተደረገ ይገኛል። ይህንንም በቦታዎቹ ተገኝተን ዐይተናቸዋል፤ ማኅበረሰቡም እያመሰገነ ነው፤ ይህ ተግባር ይቀጥላል።

ይህ ሁሉ የጤና ተቋም ወደ ሥራ ገብቶ የሚሰጠው አገልግሎት ካልተሻሻለ ችግር ይሆናል። ይህን እኛም በደንብ እየተገነዘብን መጥተናል። የጤና መድን አገልግሎት በሀገር አቀፍ ደረጃ ወደ ሥራ ገብቷል። በ10 ዓመት ጉዞ ውስጥ ከአራት ወረዳዎች የሙከራ ትግበራ ተነስተን በአሁኑ ወቅት አንድ ሺ 22 ወረዳዎች ሙሉ በሙሉ ማለት ይቻላል የጤና መድን አገልግሎት ጀምረዋል። 54 ሚሊዮን የሚሆኑ ዜጎች (አብዛኛው አርሶ አደርና አርብቶ አደር) የዚህ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል። የጤና መድን አባል መሆን ለማኅበረሰባችን በጣም ትልቅ ስኬት ነው፤ ኅብረተሰቡ የጤና መድን መታወቂያውን ልክ እንደ ባንክ ደብተሩ ያየዋል። በሪፈራልም እስከ ጥቁር አንበሳና ጳውሎስ ሆስፒታሎች በመምጣት በብዙ መቶ ሺ የሚሆኑት በነፃ የታከሙ ዜጎች አሉ። ስለዚህ ይህም ትልቅ ስኬት ነው።

በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ግን ማኅበረሰባችን ጥያቄ እያነሳ ነው። የጤና አገልግሎት ይሻሻል የሚል ጥያቄ አለ፤ ትክክል ነው። የጤና አገልግሎት ይሻሻል ሲባል የጤና ባለሙያዎቻችን ሙያዊ ሥነ-ምግባርን በጠበቀ መልኩ ማኅበረሰባቸውን በአግባቡ ማገልገል አለባቸው ማለት ነው፤ በዚህ ረገድ ክፍተቶች እንዳሉ ይታወቃል። በርካታ ስኬቶች እንዳሉ ሁሉ ክፍተቶችም አሉ፤ በዚህ ላይም በቀጣይነት ሰፊ ርብርብ እናደርጋለን።

የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልገው ሌላው ጉዳይ ግብዓት ነው። በግብዓቶች ላይም ቅድም ባልኩት መሠረት መሻሻል የታዩበት ሁኔታ አለ። ይህም በቀጣይ ትልቅ ፈተና እና ርብርብ የሚጠይቅ ጉዳይ ነው። ከዚያ ውጪ ሌላው ጉዳይ ደግሞ የአስተዳደር ሥርዓታችን ነው፤ ከላይ እስከ ታች ያለው አመራር የጤናን አጀንዳ ቅድሚያ አጀንዳው አድርጎ ድጋፍ እያደረገ መሄድ ይኖርበታል፤ በዚህም ላይ ይሠራበታል። በአጠቃላይ ከጥራት ጋር ተያይዞ የሚነሱ ጉዳዮችን በተለየ እይታ እንመለከታለን።

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በአብዛኛው ተደራሽነት ላይ ትኩረት አድርገናል። አሁን ግን ከትላልቅ ተቋማት ጀምሮ እስከ ጤና ኬላዎች ድረስ ጥራትን ከማምጣት ጋር ተያይዞ ለመሥራት የተለያዩ ፕሮጀክቶችን እየነደፍን እንገኛለን። ቅድም ያልኳቸው ፕሮጀክቶች ወደ ሥራ ሲገቡ ጥራት ላይ የራሳቸው የሆነ ተጨማሪ ሚና ይጫወታሉ። ጤና ባለሙያተኞቻችንን ስናሠለጥናቸው፤ ስናበቃቸው፤ ስንከታተላቸው ጥራት ላይ የራሳቸውን አስተዋፅዖ ያደርጋሉ፤ የጥራት አጀንዳ ተጀምሯል፤ ፍኖተ ካርታውን አስቀምጠናል፤ በርካታ ርብርቦች እንደሚያስፈልጉ ግን በዚህ አጋጣሚ መግለፅ እፈልጋለሁ።

**ጥያቄ፡- በመጨረሻ በቀጣይ ስድስት ወር ሲፈቱ የሚገባቸው ችግሮች ምንድን ናቸው?**

**ዶክተር ደረጀ ፡-** እንግዲህ እንደሚታወቀው በዚህ ስድስት ወር ውስጥ የተሠሩ ሥራዎችን በተለያየ መንገድ ለመከታተል፤ ለመደገፍና ችግሮችን ለመለየት ጥረት ስናደርግ ቆይተናል። በክትትልና ድጋፍ ሥርዓት በኩል የጤናው ሴክተር የተሻለ ነው ብለን ማስቀመጥ እንችላለን። መረጃ ከጤና ኬላ ጀምሮ እስከዚህ ይመጣል። መረጃ ላይ መሠረት በማድረግ የት ክልል ላይ፤ የትኛው ጤና ኬላ ምን ችግር አለበት የሚለውን ማወቅ ይቻላል። የመረጃ ሥርዓታችንን የበለጠ ለማሻሻል ከማኑዋል ወደ ወረቀት አልባ ሥርዓት ለመግባት ጥረት እየተደረገ ነው። በተለይ በአዲስ አበባ ሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎቻችን ላይ ስኬቶችን እያየን እንገኛለን።

ይሄ ችግሮቻችንን በደንብ እንድንለይና የተጠያቂነት ሥርዓትን ለማምጣት ይጠቅማል። እንግዲህ እንደ ችግር በአጠቃላይ የተገነዘብነው አንዱ በየቦታው የግብዓቶች እጥረት ማጋጠሙን ነው። በየትኛውም ጤና ተቋም ላይ ይሄ ክፍተት አለ። ለእዚህም የተለያዩ ምክንያቶችን ልናነሳ እንችላለን። ግን ማኅበረሰባችን ግብዓት ተሻሽሎለት ጤና አገልግሎት በደጃፉ በበቂ መንገድ በጊዜ ማግኘት ይፈልጋል። በዚህ ዓመት የግብዓት ችግርን እንደ ትልቅ አይተናል። ሁለተኛው ከፀጥታ ችግር ጋር ተያይዞ ያለው ችግር ነው፤ በዚህ ችግር ሳቢያ መደበኛ የጤና አገልግሎትን በሁሉም ቦታ ላይ በተፈለገው መንገድ ማስኬድ አልተቻለም። የፀጥታ ችግር ያለበት ቦታ ላይ ወረድ ብሎ ኅብረተሰቡን መደገፍ፣ ማስተማር፤ ተቋማት የሚፈልጉትን ግብዓት አግኝተው አገልግሎት መስጠት ላይ ክፍተት አለ። እዚህ ላይም ትልቅ ችግር አይተናል።

ከዚያ ውጪ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዞ የተለያዩ ወረርሽኞች የተበራከቱበት ሁኔታ ታይቷል፤ በተለይ ወባን እንደትልቅ ስጋት ነው አሁንም እያየን ያለነው። ሌሎችም ወረርሽኞች ከአየር ንብረቱም ጋር ብቻ ሳይሆን ተዛማጅ ችግሮች ጋር ተያይዞ ትልቅ ፈተና ሆነው ቀጥለዋል። ጤና ሙያተኞችም በሚፈለገው ስብጥር ያለመኖር ሌላው ተግዳሮት ነው፤ በተለይ ራቅ ባሉና የፀጥታ ችግር ባለባቸው ቦታዎች ላይ የጤና ሙያተኞች ቆይቶ ያለመሥራት ችግር ይታያል፤ ዋና ዋናዎቹ ችግሮች እነዚህ ናቸው። የመፍትሔ አቅጣጫ ብለን ያስቀመጥነው አንዱ የጤና ሴክተር ያለግብዓት ምንም አለመሆኑን ነው። ግብዓቶቻችን ደግሞ በአብዛኛው ከውጭ ነው የሚመጡት። እነዚህን ቶሎ ወደ ሀገር ለማስገባት ከተለያዩ ተቋማት ጋር በተለይ ውጭ ሃገር ካሉት ጋር ሰፊ ውይይቶች ስናደርግ ነበር።

ሌላው ደግሞ የውጭ ምንዛሪ ማግኘት ላይ በጣም በርካታ ጥረቶች ተደርገውልን ተሻሽሏል። በተለይ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ላይ ከፍተኛ ችግር እንደሆነ ይታወቃል። በአብዛኛው እሱን መፍታት ተችሏል። ከዚያ ውጭ የተለያዩ ግብዓቶች በጊዜ እንዲመጡ የትራንስፖርት ሠንሠለቱን እስከ ጤና ሚኒስቴር ለመጠበቅ ጥረት አድርገናል። መድኃኒቶች ወደ ሀገር ውስጥ መግባት ብቻ አይደለም ያልቻሉት፤ ወደ ጤና ተቋማት በጊዜ እንዲሄድ ማድረግ፣ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚመጡ የሌብነት አባዜዎች ታይተዋል። ለእዚህም ለስርቆት የሚጋለጡ አሠራሮችን ለመፈተሽ ጥረት እየተደረገ ነው። ስርቆት በታየባቸው ቦታዎች እርምጃ የተወሰደባቸው ጤና ተቋማትና አመራሮች አሉ። ይህ እርምጃ ተጠናክሮ ይቀጥላል።

ከዚህ ውጭ መንግሥት ደርሶ ሕክምና መስጠት የማይችልባቸው አንዳንድ ቦታዎች አሉ። አጋር ድርጅቶች ወደ እነዚህ አካባቢዎች አልፈው እንዲሄዱ በማድረግ በተለይ ደግሞ ተፈናቃይ ዜጎቻችን ጋር በሰፊው ደርሰው አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ላይ ድጋፍ እንዲያደርጉ እየተደረገ ነው። ተጨማሪ የፋይናንስ ድጋፍ በማድረግ የተለያዩ ግብዓቶችን በራሳቸው እንዲያመጡ አልፎ ደግሞ በተለያየ መንገድም የሕክምና ግብዓት ለማድረስ ጥረት ተደርጓል። ይህ በቂ ነው ማለት አይቻልም። በቀጣይነት ተጠናክሮ መቀጠል አለበት። በአጠቃላይ ችግሮቻችን ለመፍታት ባለድርሻ አካላትን ይህ ሲባል ማኅበረሰባችንን በተለያየ መንገድ አሳትፈን ውይይት አድርገናል። በየደረጃው ካሉ የክልል እና የዞን አካላት ጋርም ውይይቶችን አድርገናል።

ከክልሎች ጋር የጠበቀ ግንኙነት አለን። ጤና ሚኒስቴርን ለየት የሚያደርገው ከክልሎች ጋር የተሻለ ቁርኝት ያለው መሆኑ ላይ ነው፤ ከላይ እስከ ታች የተናበበ ሥርዓት ለመፍጠር ተሞክሯል። እነዚህ ሥርዓቶች በማጠናከር በተለይ አጋር ድርጅቶች የበለጠ ትኩረት እንዲያደርጉ በማድረግ የተሻለ አገልግሎት እንዲመጣ ተደርጓል። በቀጣይነት ስድስት ወራትም ትላልቅ ጉዳዮችን ለመሥራት አስበናል። በተለይ የእናቶችና የሕጻናት ጤና አገልግሎት ለነገ የሚባል ጉዳይ አይደለም። የእናቶች ሞትን ለመቀነስ ተጨማሪ ከዓለምአቀፍ ተቋማት የተማርናቸው እና እዚህ ያሉ አዋጭ የሆኑ ተሞክሮዎችን በመጠቀም በጣም ትልቅ ጥረት እናደርጋለን። እናቶቻችን በጤና ተቋማት አገልግሎት እንዲያገኙና ጤና ተቋማት ለእናቶችና ለሕጻናት ምቹ እንዲሆኑ አገልግሎቱ የበለጠ እንዲሳለጥ ጥረታችንን እንቀጥላለን።

ሌላው ሥራ በሚመጡት ወራት ወረርሽኞችን መቆጣጠር ይሆናል። በተለይ በሚመጡት ሦስት ወራት የኮሌራ በሽታን ሙሉ ለሙሉ እንቆጣጠራለን። የኩፍኝ በሽታንም እንዲሁ በዚህ ዓመት እንቆጣጠራለን። የወባ በሽታንም ሙሉ ለሙሉ መቆጣጠር ባንችልም ግን በአብዛኛው ቦታዎች ላይ ጫናውን በእጅጉ እንቀንሳለን። በዓመቱ መጨረሻ ላይ ቁጥሩን አሁን ካለው ከግማሽ በታች እናደርጋለን ብለን እየሠራን ነው። ሌሎች ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች አንገብጋቢ የሆኑ ጊዜ የማይሰጡ በተለይ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ብዙ ዜጎችን እየጎዱ ነው ያሉት። ይህም የመከላከሉንና ሥራና የሕክምና ሥርዓቱንም ማሻሻልን ይጠይቃል።

በተለይ የጨረር ሕክምና በሚሰጠባቸው ሦስት ተቋማት በሙሉ ወደ አገልግሎቱ እንዲገቡ ከፍተኛ ርብርብ በማድረግ እንሠራለን። ለዚህ ዘርፍ ግብዓቶች በጣም አስፈላጊ ናቸው። ግብዓት ላይ መሠረታዊ ለውጥ እናመጣለን። አንዱ መፍትሔ ግብዓቶቹን ሀገር ውስጥ ማምረት ነው። እንደምታስታውሱት ከተወሰኑ ቀናት በፊት ሀገራችንን ‹ኢንፊልድ ባክስ› በሚለው ሀገር ውስጥ ክትባት ለማምረት በጠቅላይ ሚኒስትራችን ድጋፍ ሰፊ ንቅናቄ ተደርጓል። ለእዚህም የመሠረት ድንጋይ ተቀምጧል። በዚህም ሀገራችን በአጭር ጊዜ ውስጥ ክትባት ማምረት የምትችል ከአፍሪካ ውስጥ ሦስተኛ ወይም አራተኛ ሀገር ልትሆን ትችላለች። ለዚህ ደግሞ የሚያስፈልገው ትልቅ ገንዘብ ነው። የቴክኖሎጂ ሽግግሩም ቀላል የሚባል አይደለም። ለሁሉም ከተለያዩ ተቋማት ጋር እንሠራለን።

ከዚህም ሌላ መድኃኒት የሚያመርቱ ድርጅቶችን የበለጠ ማጠናከር ያስፈልጋል። ሀገር ውስጥ የሚመረቱት መድኃኒቶች ከውጭ ከምናመጣ ይልቅ ዋጋቸው ከፍተኛ ሊል ቢችልም መጠቀም ያስፈልጋል። መደጋገፍ ያስፈልጋል። እነዚህ በቀጣይነት የሚታዩ ጉዳዮች ናቸው። እንደጤና ዘርፍ የቁጥጥር ሥርዓታችን መሻሻል አለበት። በአብዛኛው የቁጥጥር ሥርዓታችን የላላ ነው። ምክንያቱም የምንከተለውም የነፃ ገበያ በተለይ የግል ጤና ተቋማት ላይ የሚፈለገውን ሁሉ ለማድረግ የምንቸገርበት ነው። የግል የጤና ተቋማት ገንዘብ የሚያገኙበት እንዳለ ሆኖ ለትርፍ ነው የሚሠሩት ፤ያም ሆኖ ጤና የሰብዓዊነት ሥራ ነው።

ማኅበረሰቡን አስመልክቶ መታየት ያለባቸው ጉዳዮች አሉ። የመክፈል አቅምን መሠረት ያደረገ ጥራት ያለው፤ ትክክለኛ እና አግባብ ያለው ሕክምና መስጠት ያስፈልጋል ፤በዚህ ላይ በሚቀጥሉት ጊዜያት የተሻለ ሥራ እንሠራለን ብለን እናስባለን።፣ ከዚያ ውጭ ግን በሀገራችንም በዓለም አቀፍም ደረጃ እየተከሰቱ ያሉ በጣም ተለዋዋጭ የሆኑ ጉዳዮች አሉ። ይህንን ያነበበ ጠንካራ የእቅድ ሥርዓትና በየጊዜው ለዚህ ምላሽ የሚሰጥ የጤና ሥርዓት እንዲኖር በጥብቅ እንሠራለን። በተለይ ለችግሮች የማይበገርና ከችግሮች የሚማር የጤና ሥርዓት በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲገነባ የጤና ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ ይሠራል።

**አዲስ ዘመን፦ ከጤና ባለሙያዎች ጋር በተያያዘ በአንድ በኩል የባለሙያ እጥረት በሌላ በኩል ባለሙያዎች ሥራ አጥ ሆነው የሚታዩበት ሁኔታ ይታያል ሁለቱን ለማስታረቅ ምን እየተሠራ ነው? በተጨማሪም ባሕላዊ መድኃኒት ላይ የተለያዩ ጥናቶችና ምርምሮች እንደሚደረጉ ይታወቃል። በዚህስ ላይ ምን የሚሉት ነገር አለ?**

**ዶክተር ደረጀ፡-** አንደኛው በተለይ ከጤና ሙያተኞቻችን ጋር ተያይዞ በራሱ በየአምስት ዓመት የሚሠራ የጤና ሙያተኞች እስትራቴጂ አለን። ዋናው ከጤና ሙያተኞች ጋር ተያይዞ ያለው በቁጥርም በስብጥርም በሚፈለገው ደረጃ እንዲኖሩ እንፈልጋለን። ባለፉት ዓመታት በርካታ ኢንቨስትመንቶችን አድርገናል። የባለሙያዎቻችን ቁጥር ከ270 ሺህ በላይ ሆኗል።

ከግብርና ሴክተር ቀጥሎ ትምህርት ከዚያም ሦስተኛ የጤና ሴክተር ይመጣል። መንግሥት በርካታ ኢንቨስትመንት አድርጓል፤ በዚህ ላይ ከፍተኛ ቁርጠኝነት እንዳለው ለማንሳት እፈልጋለሁ። ባለፉት ዓመታት የትኛውም የጤና ሙያተኛ ተመርቆ ሲወጣ ወደ ሥራ ይገባል። ከአምስት ዓመት ወዲህ ግን የተወሰነ ክፍተቶች እየታዩ ነው። የሚመረቁ የጤና ሙያተኞችን ወዲያውኑ ወደ ሥራ ለማስገባት ችግሮች አጋጥመውናል። ቁጥሩ በቂ ስለሆነ አይደለም።

የዓለም ጤና ድርጅት በሚያስቀምጠው መስፈርት በተለይ ከሰሐራ በታች ባሉት አፍሪካ ሀገራት አሁንም ኢትዮጵያ ገና ብዙ እንደሚቀራት ይታወቃል። በተለይ ከፍተኛ ባለሙያዎችን፣ እስፔሻሊስቶችን እንዲሁም ሌሎችም ገና በጅምር ያሉ የሙያ ዘርፎች አሉ። እዚህ ላይ በርካታ ሥራዎች መሥራት እንዳለብን ይታወቃል።

ከዚያ ውጭ ግን ከነርስ ጋር፣ ከሚድዋይፍ ጋር፣ ከጤና መኮንኖች ጋር ተያይዞ የተሻለ ደረጃ ላይ ነን፤ በቂ ነው ባይባል የሚቀረን አለ። እንግዲህ እኛ እንደጤና ሚኒስቴር በርካታ የጤና ሙያተኞች ቢመደቡ ደስታችን ነው፤ እንፈልጋለን። ግን የአቅም ጉዳይ ደግሞ ውስንነትን ፈጥሯል። ፌዴራል መንግሥት በፌዴራል ስር ባሉ የጤና ተቋማት ውስጥ እየመደበ ነው ፤ ያን ያህል ክፍተት የለም።

በክልል ደረጃ ግን የክልል መንግሥታት በሚፈለገው ያህል በጀት ያለመያዝ ክፍተት ነው። ከዓመት ዓመት የተወሰነ ይይዛሉ ግን የሚፈለገውን እና የምናስመርቀውን የጤና ሙያተኛ ሙሉ በሙሉ ወደ ሥራ የሚያስገባ የበጀት አቅም አለመኖር ትልቁ ክፍተት ነው። ይሄንን ክፍተት ለመሸፈን ከክልል አመራሮች ጋር ተደጋጋሚ ውይይት አድርገናል። እነሱ የተወሰነ እንዲጨምሩ እኛም ደግሞ ፕሮጀክቶችን እንድናመጣ፤ እንግዲህ መንግሥት ያለበት ሁኔታ ሁላችንም እንረዳለን። በሚፈለገው ደረጃ ሁሉንም ሰው ማስቀጠር የሚችል አቅም የለም።

በሌላው ሴክተር ውስጥም እንደዚህ ዓይነት ነገር የለም። በተለይ ሐኪሞች/ በርካታ ሐኪሞች ግማሽ እኛ ከፍለን ግማሽ ደግሞ ለፕሮጀክት የሚመጣውን ገንዘብ ተጠቅመን እየቀጠርን እንገኛለን። ከዚህ ጋር ተያይዞ ያለው ትልቁ ችግር ጤና ሙያተኛው በአብዛኛው ከተማ ላይ በአዲስ አበባና የተወሰኑ ከተሞች ላይ መሥራት መፈለጋቸው ነው። ወጣ ብሎ መሥራት ላይ አሁንም ክፍተት አለ። በጤና ሙያተኞቻችን መሻሻል ያለበት ነው። እውነት ነው እኛም ልናሻሽላቸው የሚገቡ ጉዳዮች ይኖራሉ። እሱ መታየት አለበት።

መፍትሔው በቀጣይነት ግን የፋይናንስ አቅማችን ማጠናከር ነው። ለዚህ ደግሞ እኛም እንደመንግሥት አጋር ድርጅቶች እንዲሳተፉ እናደርጋለን። ከዚያ ውጭ ግን እያንዳንዱ የጤና ሙያተኛ ወጥቶ በግልም እንዲሠራ ሁኔታዎች እያመቻቸን ነው ። የፍቃድ አወጣጥ ሥርዓታችን ሁኔታ ተሻሽሏል። በአጭር ጊዜ የአገልግሎት ፍቃድ አውጥተው እንዲሠሩ እየተደረገ ነው ፤ እሱንም እናጠናክራለን። ከዚያ ውጭ የሥራ ፈቃዳቸውን / ላይሰንሳቸውን በጊዜ እንዲወስዱና በግልም ሊሆን ይችላል NGo ውስጥ ገብተው በተለያዩ ሴክተሮችም ገብተው የሚሠማሩበትን የሙያ መስክ እያሰፋን እንደምንሄድ በዚሁ መግለጽ እፈልጋለሁ። ትክክል ነው ክፍተት አለ።

ከዚያ ውጭ ግን ኮቪድ ሲገባ አብዛኛውን እነዚህ ሥራ አጥተው የተቀመጡ ለማሳተፍ ጥረት አድርገናል። አሁንም በተለያየ መንገድ ፕሮጀክትን እየቀረጽን የምንሄድ ይሆናል። ጤና ተቋማትም እንደድሮው እየገነባን አይደለም። እሱንም ከክልሎች ጋር በመሆን ተጨማሪ ጤና ተቋማት እንዲገነቡና ጤና ሙያተኞችን በስፋት ወደ ሥራ እንዲገቡ ጥረት እናደርጋለን።

ከዚያ ውጭ ባሕላዊ ሕክምና ላይ እውነት ነው። በሀገራችን በርካታ አቅምና ምሳሌ የሚሆን ሥራ መሥራት እንደምንችል እናምናለን። በባሕላዊ ሕክምና ላይ ማኅበረሰባችን ውስጥ ትልቅ ጥበብ አለ። በአብዛኛው ዜጎቻችን አሁንም ባሕላዊ ሕክምና የሚጠቀሙ ናቸው። እሱን ማዘመን ላይ የተጀመሩ ሥራዎች አሉ፤ በሚፈለገው ፍጥነት አልሄደም። የሚቀሩ ሥራዎች አሉ። በቅርብ እንደምታውቁት ሀገራዊ ኤግዚቢሽን አካሂደን ነበር።

እዚያ ኤግዚቢሽን ላይ አንድ እራሱን የቻለ ትልቅ የባሕላዊ ስፍራ አዘጋጅተን አሳይተናል። አንዳንዶቹ ጥሩ እየሄዱልን ነው። በተለይ የተለዩና በባሕላዊ ሕክምና ውስጥ ወደ ገበያ መውጣት የሚችሉ በጥናት ደረጃ የተረጋገጡ የተወሰኑ አሉ። እሱን ማኅበረሰባችን እንዲያውቀው እንዲጠቀመው በቀጣነት የሚሠራ ይሆናል። በአጠቃላይ ግን በዚህ ላይ ጥናት ያስፈልጋል።

በዚህ ዘርፍ ላይ ተመራማሪዎች ማምጣት ያስፈልጋል። ከተለያዩ ሀገራት በተለይ ከቻይና፣ ከታይላንድም ከሕንድም ጥሩ ልምድ ካላቸው ሀገራት ተሞክሯቸውን እየወሰድን እንገኛለን። አሁን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በአዲስ መልክ እየተደራጀ ነው። ይሄ ዘርፍ ቀደም ሲል በኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ስር ነበር፤ አሁን አሐዱ በሚባለው ተቋማችን ስር በአዲስ መልክ ተደራጅቷል። እሱን በቀጣይነት በደንብ የምንሠራው ሥራ ይሆናል።

የተወሰኑ ጫፍ ላይ የደረሱ ብዙ ጥናቶች አሉ። እሱን ከስር በስር ወደ ገበያ የሚሄዱትን ተጨማሪ ጥናት የሚያስፈልጋቸውን ለይተን የምንሠራበት ይሆናል። በአጠቃላይ ግን ዘርፉ በቀጣይነት ትልቅ ኢንቨስትመንት የሚያስፈልገው ነው። ቅድም እንዳልኩት ክትባትን በሀገር ውስጥ ስናመርት ብዙ እውቀት እናገኝበታለን። ክትባትን ማምረት ትልቁ ሥራ ነው። ያን ካደረግን ሀገራችን ውስጥ ያሉትን ባሕላዊ ሕክምናዎችን ማዘመን እንደምንችል ትልቅ ማሳያ ስለሆነ ከዚያ የምናገኘውን ትምህርት አያይዘን የምናሳድግ ይሆናል።

ለዚህም አሐዱ የሚባለውን ተቋማችንን በተለየ መንገድ እያደራጀን ነው። ለሱ የሚሆኑ ግብዓቶችንም እያደራጀን ነው። እንዲሁም ከውጭም የሚደግፉን አካላት እያስገባንበት ስለሆነ በሚቀጥሉት ዓመታት ትልቅ ለውጥ እናመጣለን። ባሕላዊ የሕክምና ዘርፉ አማራጭ የሕክምና ዘዴ እንደሆነ በፖሊሲያችንም በደንብ አስቀምጠናል፤ በእቅዳችንም አስቀምጠናል።

**አዲስ ዘመን፡- በጣም እናመሰግናለን**

**ዶክተር ደረጀ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ስፖርት





## የአፍሪካ ዋንጫው በአጓጊ የሩብ ፍጻሜ ጨዋታዎች ዛሬ ይደረጋሉ

ብርሃን ፈይሳ

በኳታሩ የዓለም ዋንጫ እስከ ግማሽ ፍጻሜ በመጓዝ ድንቅ ቡድን መገንባቷን ያስመሰከረችው ሞሮኮን ጨምሮ በዓለም ዋንጫው አፍሪካን የወከሉ፣ እንዲሁም በወቅታዊው የፊፋ ሃገራት ደረጃ መሰረት ከአፍሪካ ቀዳሚ ቡድኖች መካከል ከአንድ እስከ አምስት የተቀመጡትን ታላላቆቹን ቡድኖች በጊዜ ያሰናበተው 34ኛው የአፍሪካ ዋንጫ፤ የሩብ ፍጻሜ ጨዋታዎቹን ዛሬና ነገ ያከናውናል። በካሜሮኑ የአፍሪካ ዋንጫ ከሩብ ፍጻሜ መድረስ ያልቻሉት ቡድኖች ኮትዲቯር ላይ ዋንጫውን የግላቸው ለማድረግ የሚያደርጉት ፍልሚያ ውድድሩን እጅግ አጓጊና የማይገመት አድርጎታል፡፡

የእግር ኳስ ቤተሰቡን ባስደመመው ጥሎ ማለፍ የተመዘገቡ ውጤቶች ከአፍሪካ ዋንጫው መጀመር አስቀድሞ በቡድን ስብስባቸው የተፈሩ ቡድኖችን እያንጠባጠበ ወደ ሌላኛው ልብ አንጠልጣይ ደረጃ ተሸጋግሯል፡፡ በዓለም ዋንጫ ታሪካዊ ፉክክር ያስተናገደችው ሞሮኮ፣ ከሁለት ዓመት በፊት ዋንጫውን የወሰደችው ሴኔጋል፣ የአፍሪካ ዋንጫን ለ7 እና 5 ጊዜ በማንሳት ተከታትለው የተቀመጡት ግብጽ እና ካሜሮን በፕሮፌሽናል ተጫዋቾች የተገነባ ቡድናቸው ባልተጠበቀ ሁኔታ ነው የተገኙት፡፡ በአንጻሩ የውድድሩ አዘጋጅና እድለኛዋ ኮትዲቯር ወደ ፉክክሩ ተመልሳ ከዋንጫው ተፋላሚ ሃገራት መካከል አንዷ መሆኗ የእግር ኳስን አይገመቴነት የሚያሳይ ሆኗል፡፡ ብዙም ግምት ያላገኙት ኬፕ ቬርዴ፣ አንጎላ፣ ጊኒና ደቡብ አፍሪካም ከስምንቱ ቡድኖች መካከል ተገኝተዋል፡፡




ከሁለት ቀናት እረፍት በኋላ ዛሬ እና ነገ በሚከናወኑት ጨዋታዎች ደግሞ ሩብ ፍጻሜውን አልፈው ለግማሽ ፍጻሜው ጨዋታ የሚደርሱ አራት ቡድኖች ይለያሉ። የዛሬ ምሽቱ ቀዳሚ ጨዋታም በናይጄሪያ እና አንጎላ መካከል በፌሌክስ ሆፌት ቡዋኜ ስታዲየም የሚከናወን ነው፡፡ ይሆናሉ ተብሎ በማይጠበቁ ክስተቶች የተሞላው ይህ ውድድር በአፍሪካ ዋንጫ ታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ረጅም ርቀት መጓዝ የቻለችው አንጎላ በአስደናቂነቷ ትቀጥላለች ወይስ ዋንጫውን ለመጨረሻ ጊዜ ከወሰደች 10 ዓመታትን ያስቆጠረችው ናይጄሪያ በዋንጫ ፉክክሩ ትጸናለች የሚለውን ይለያል፡፡ በቁጥር በተቀመጡት ቅድመ ግምት መሰረት የአሸናፊነት ሚዛኑ ለናይጄሪያ ያዘነበለ ቢሆንም፤ ምድቧን እየመራች ከሩብ ፍጻሜ የደረሰችው አንጎላ ቀላል ተፎካካሪ ልትሆን እንደማትችል ግልጽ ነው፡፡

ሌላኛው የዕለቱ ጨዋታ ደግሞ አቢጃን በሚገኘውና 60ሺ ሰዎችን የመያዝ አቅም ባለው አላሳኔ ኦታራ ስታዲየም የሚከናወነው የዴሞክራቲክ ኮንጎ እና ጊኒ ጨዋታ ነው፡፡ ከአፍሪካ ኃያል ቡድኖች መካከል አንዷ የሆነችውን ግብጽን ከጨዋታ ውጪ በማድረግ ለሩብ ፍጻሜው የበቃችው ኮንጎ በምርጥ ሶስተኛነት ዳግም ለተፋላሚነት ከበቃችው ጊኒ ጋር የሚኖራቸው ግጥሚያ በእርግጥም ድራማዊ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡ ሁለት ጊዜ ዋንጫ ማንሳት የቻለችው ኮንጎ የተሻለ የውድድር ታሪክ ያላት ሲሆን፤ በዛሬው ጨዋታም በርካቶች የአሸናፊነት ግምቱን ሰጥተዋታል።

ነገ በሚኖረው መርሃ ግብር ማሊ ከውድድሩ አዘጋጅ ሃገር ኮትዲቯር ጋር የምትጫወት ሲሆን፤ ዕድለኛዋ ኮትዲቯር ወይስ እምብዛም ፉክክር ያልታየበትን ምድብ አምስትን ስትመራ የቆየችው ማሊ ትረታ ይሆን የሚለው የስፖርት ቤተሰቡን ቀልብ ይዟል። ዋንጫውን በሀገሯ ታስቀራለች በሚል ስትጠበቅ የቆየችው ኮትዲቯር እንደ አዘጋጅ ሃገር ከምድብ ያለማለፏ ዜና አነጋጋሪ ነበር፡፡ ነገር ግን ምርጥ ሶስተኛ በመሆን ወደ ፉክክሩ በመመለስ ጠንካራዋን ሴኔጋልን ጥላ ማለፍ ችላለች፡፡ ሆኖም ቡርኪና ፋሶ ላይ ድል የተቀዳጀችውና ሳይገመት ጠንካራ ሆና የተገኘችው ማሊ ፈተና እንደምትሆንባት ይጠበቃል፡፡

የመጨረሻው የሩብ ፍጻሜ ጨዋታም ደቡብ አፍሪካን ከኬፕቨርዴ ጋር የሚያገናኝ ነው። ደካማ አጀማመር አሳይቶ ወደ ጠንካራ ብቃቱ የተሸጋገረው የደቡብ አፍሪካ ቡድን በጥሎ ማለፉ ጨዋታ ሳይጠበቅ ጠንካራዋን ሞሮኮን 2 ለምንም የሆነ ፍጹም የበላይነትን መቀዳጀቱ የሚታወስ ነው። ሳትገመት ውጤታማ ጉዞ እያደረገች ያለችው ደሴቲቷ ሃገር ኬፕቨርዴ በአፍሪካ ዋንጫው ጠንካራ በተባለው ምድብ ሁለት ነበር የተደለደለችው፡፡ የአራት ጊዜ የአፍሪካ ዋንጫ አሸናፊዋን ጋናን 2 ለ 1 በማሸነፍና ከሰባት ጊዜ የውድድሩ ዋንጫ ባለቤት ግብጽ ጋር አቻ በመለያየት፤ እንዲሁም ሞዛምቢክን 3 ለምንም በማሸነፍ ነበር በሰባት ነጥብ የምድቡ ቁንጮ ሆና ነው 16ቱን የተቀላቀለችው፡፡ በጥሎ ማለፉ ጨዋታም ሞሪታኒያን በመርታት በአፍሪካ ዋንጫ ተሳትፎዋ ስኬታማ የተባለውን ጉዞዋን በማድረግ ላይ ትገኛለች። በዛሬው ጨዋታም ከሁለቱ ቡድኖች ጠንካራ ጨዋታ ይጠበቃል፡፡